# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ (ኢዴኅአን)

# ETHIOPIAN DEMOCRATIC HIBREHIZB UNITY MOVEMENT (EDHUM)

**የት ላይ ነን? ወዴት እያመራን ነው? ምንስ መደረግ ይኖርበታል?**

**የአገራችን አሳሳቢ ሁኔታ እና የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ የአንድነት ንቅናቄ አቋም፤**

**ለኢዴኅአን ብሔራዊ ሸንጎ ጉባዔ ለውይይት የቀረበ፤**

**ማውጫ፤**

1. መቅድም ገጽ 3

2. አጠቃላይ ገጽ 4

3. የድርጅታችን መሠረታዊ እምነቶች ገጽ 11

4. የአገራችን መሠረታዊ ችግሮች ገጽ 14

5. ምን መደረግ አለበት? ገጽ 18

- መሠረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ገጽ 24
- የድርጅቶች ትብብር አስፈላጊነት ገጽ 25
- ዴሞክራሲያዊ የሽግግር ሂደት ገጽ 27

6. ማጠቃለያ ገጽ 31

# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ (ኢዴኅአን)

**ETHIOPIAN DEMOCRATIC HIBREHIZB UNITY MOVEMENT (EDHUM)**

## የት ላይ ነን? ወዴት እያመራን ነው? ምንስ መደረግ ይኖርበታል?

## የአገራችን አሳሳቢ ሁኔታ እና የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ የአንድነት ንቅናቄ (ኢዴኅአን) አቋም፤

### I. መቅድም፤

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ የአንድነት ንቅናቄ (ኢዴኅአን) በሰኔ ወር ፪ ሽህ ዓ/ም የብሔራዊ ሸንጎ ጉባዔውን የሚያደርገው የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ አገራችንን በጎረቤት አገር በሶማሌ ውስጥ ጣልቃ በማስገባት ውሉ በጠፋ ጦርነት የአገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት አባላት መስዋዕት እየሆኑ ባሉበት፣ በዚኸም ጣልቃ-ገብነት ምክንያት አገራችን ለውጭ ፀረ-ኢትዮጵያና ለውስጥ ፀረ-አንድነት ኃይሎች ዓላማ አመች ሁኔታ እንዲፈጠርና እንዲመቻች በሆነበት፣ በመሆኑም አገራችንና ሕዝባችን ለላቀ አደጋና ጥቃት በእጅጉ እንዲጋለጡ በተደረገበት፣ አሳፋሪ የረሃብ አዙሪት ዳግም ተከስቶ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ለጠኔ በተጋለጡበት፣ በሱዳን በኩል ወሰናችን ተጥሶ መሬቶቻችን በሱዳን ይዞታ ሥር እንዲወድቁ እና ንፁኀን ዜጎች ታፍነው በባዕዳን በተወሰዱበት፣ ሕዝባችን ለአጠቃላይ መጠኑን የሳተ የኑሮ ውድነት በተጋለጠበት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በግንቦት ወር ዘጠና-ሰባት ዓ/ም ያስመዘገባቸው ድሎች ተቀልብሰውና እንዳልነበሩ ሆነው ትግሉ የኋሊት ሄዶ አፈናና ሰቆቃ አዘቦታዊ በሆኑበትና በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች የፖለቲካ ውጥረት አይሎ ባለበት፣ የተቃዋሚው ጎራ በሚያሳዝንና በሚያሳፍር መልኩ ብጥቅጥቁ በወጣበት፣ ወዘተ... በአጠቃላይ አገራችን ኢትዮጵያና ሕዝቧ ላይ ከፍተኛ ሁል-አቀፍ ችግሮች በሚያንዣብ-ቡበት የከፋ የውጥረት ሁኔታ ነው:: ስለሆነም ይኸ ጉባዔ የሚደረገው አገራችን የምትገኝበት የኅልውና ማጣት አደጋና ሕዝባችን ጫንቃ ላይ የተጫኑ ችግሮች እንዲወገዱ ድርጅታችን የሚያደርገውን ትግል በአዲስ ቅኝትና ቁርጠኝነት ለመቀጠል ባለ የላቀ ብሔራዊ የኃላፊነት ስሜትና የጋለ መንፈስ ነው:: (ከዚኸ ጉባዔ ምን እንደሚጠበቅ በሌላ አባሪ ሰነድ ከዚህ ጋር ተያይዞ ቀርቧል:: )

## II. አጠቃላይ፤

በአገራችን ያለው የፖለቲካ የቀውስ ሁኔታ አገሪቱ ከምትገኝበት የማኅበረሰብ (ሶሻል) እና የምጣኔ ሃብትና ኑሮ (ኢኮኖሚ) የቀውስ ሁኔታ ተለይቶ የማይታይና የተጣመረ ቢሆንም፣ ይኸ የድርጅታችን አጭር ቅኝት አሁን ሁሉንም ኢትዮጵያዊ እያስጨነቁና እረፍት እያሳጡ ባሉትና አሳሳቢ በሆኑት ተዛማጅ ዓቢይ ጉዳዮች ማለትም በኢትዮጵያችን አንድ አገር ሆኖ የመቀጠል አለመቀጠል መሠረታዊ የኅልውና ማጣት አደጋ እና የዴሞክራሲ ሂደት አቅጣጫውን እየሳተ በመሄዱ ምክንያት ሕዝባችን ለአጠቃላይ የመብቶች መረገጥና አፈና መዳረጉ ያስከተለው ከፍተኛ ችግርና የውጥረት ሁኔታ ሲሆን፣ መሥመር የሳተው የዴሞክራሲ ሂደት አቅጣጫውን አስተካክሎ የፍትኅ፣ የእኩልነትና በዜጎች ሁለንተናዊ መብቶች መከበር ላይ በሚመሠረት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ የምጣኔ-ሃብት (የኢኮኖሚ)፣ የማኅበራዊ (የሶሻል) እና የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ትገኛለች፡፡ ባለፉት አርባ ዓመታት የተለያዩ መንግሥታት ቢፈራረቁባትም፣ የአገሪቱን ዋና ዋና ችግሮችና የሕዝቡን መሠረታዊ የፖለቲካ ጥያቄ መመለስ አልቻሉም፡፡ በዚህም ምክንያት ሰላምና የተረጋጋ የፖለቲካ ሥርዓት እንዲሁም የምልአተ-ሕዝቡን ኑሮ የሚያሻሽልና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ውድ አገራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ ለሄደ የአንድነት መናጋትና እንደ አንድ አገር ያላት ኅልውና ጥያቄ ውስጥ ሊገባ የሚችልበት እጅግ ፈታኝ፣ አሳሳቢና አስጊ ሁኔታ ውስጥ እየገባች መገኘቷ ብዙዎችን እያስጨነቀና በጣሙን እያሳሰበ የሚገኝ ጉዳይ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ምንም እንኳ አገራችን እንደ አገርና ሕዝባችንም እንደ ሕዝብ ከፈተናና ከችግር የተላቀቁበትና እፎይታን አግኝተው የሚያውቁበት ወቅት ብዙ ባይኖርም፤ በውጭና በውስጥ የሚደረጉ የተቀናበሩ ጫናዎችና ግፊቶችን ስንመለከት ምናልባት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጋራ ኅልውናችን ላይ የሚያንዣብበው አደጋ እንደ አሁኑ የከፋ ሆኖ የታየበት ጊዜ የለም የሚያሰኝ ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን፡፡

በአሁኑ ጊዜ በሥልጣን ላይ ያለው የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ከአሥራ-ሰባት ዓመታት በፊት ያለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ፈቃድና ይሁንታ ሥልጣን በጉልበት ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ የአገራችን ብሔራዊ አንድነት የተናጋበትና ሕዝባችን የናፈቀው፣ የታገለለትና መስዋዕትነት እየከፈለበት ያለው መብቱንና ጥቅሙን የሚያስከብርበት የአዲስ ሥርዓት ፍላጎቱና ተስፋው እየመከኑ ያሉበት ሁኔታ ውስጥ መሆናችን የሚያጠያይቅ አይሆንም፡፡
አምባ-ገነንና ኢ-ዴሞክራሲያዊ የአገዛዝ ሥርዓቶች ባራመዷቸው ኋላ-ቀርና ብልሹ አስተዳደሮች ምክንያት የዜጎች እኩልነት ያልተከበረበትና ሰብአዊ መብቶች የተጣሱበት ሁኔታ አገራችንን ለዘመናት እንደተጠናወታት ይታወቃል፡፡ በዚህ የሰብአዊ መብት ጥሰትና የእኩልነት አለመከበር ምክንያትም በተለያዩ ጊዜዎችና የአገሪቱ ክፍሎች ሃቀኛ የሕዝብ ብሶት የወለዳቸው እንቅስቃሴዎች ተከስተዋል፡፡ ይሁንናም ይኸንን የሕዝብ ብሶት ምክንያት አድርገውና ተንተርሰው የተነሱ እንቅስቃሴዎች በአብዛኛው በአገሪቱ የቅርብም የሩቅም የውጭ ጠላቶች እየተጠለፉና አቅጣጫ እየሳቱ የእነዚኸን ኃይሎች ኢትዮጵያን የማዳከምና የመከፋፈል የቆየ ዓላማ (አጀንዳ) በተግባር ተርጓሚ መሣሪያና መጠቀሚያ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ይኸ አጥፊ ጥረት አሁንም በልዩ ልዩ መልክ ቀጥሎ አገራችንን አካባቢያዊ ብቻ ሳይሆን ዓለም-አቀፋዊ ይዘት ባለው ከፍተኛ ውጥረት፣ ፍጥጫና ሁከት ውስጥ እንድትገኝ ማድረጉን እናያለን፡፡

በውድ አገራችን በኢትዮጵያ በግንቦት ሰባት ቀን ፺፯ ዓ/ም የተደረገው ምርጫ ተራና አዘቦታዊ ምርጫ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም፡፡ ይኸ ምርጫ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በስፋት የተሳተፈበትና ለዝንታለም እጅ ከወርች ጠፍረው የያዙትንና ለአጣ-ለነጣ ድህነት የዳረጉትን አዙሪቶች የሰበረበት ዓቢይ እንቅስቃሴ ነበር፡፡ በዚያ 'ዳግም አድዋ' ተብሎ ሊቆጠር በሚገባው የግንቦት ሰባት ምርጫ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከልዩነትና ከመከፋፈል

አንድነትን፣ ከአምባ-ገነኖች የሥልጣን ቅብብሎሽና የአመፅ ሥርዓት መቀጠል ይልቅ ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ ሂደትን እንደሚፈልግ በማያወላዳና በግልጽ ሕዝበ-ውሳኔ የሰጠበት ታሪካዊ ግኝትና የረጅም ጊዜ ትግሉ መቋጫ ክስተት ሆኖ ሊቆጠር ይገባል::

ይኸንን ሕዝበ-ውሳኔ ማንም ኃይል እንደፈለገውና እንዳሻው እንዳይሽረው መንከባከብና ድሉንም ማስከበር የማንኛውም አገር-ወዳድና ዴሞክራት ለውጥ ፈላጊ ታጋይ ክፍል ተቀዳሚ ኃላፊነት ሊሆን ይገባው እንደነበር የሚያጠያይቅ አይሆንም:: ለዚኸ በሕዝብ ከፍተኛ መስዋዕትነት የተገኘ ድል መቀልበስ ከላይ በጉልህ ሲታይ ዋነኛ ተጠያቂው ገዥው ፓርቲ መሆኑ ባያጠያይቅም፣ ጉዳዩን ጠለቅ ብለን ካየነው የተቃዋሚው ክፍል ድርጅታዊ ጥንካሬ ጉድለትና የሕዝቡን የግንቦት ድሎች ለማስጠበቅ ዋስትና ሰጭ የሆኑ የሲቪክና የሙያ ማኅበራትና ሌሎች ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ አውታሮችና መዋቅሮች ሥር በሰደደና በተጠናከረ መልክ አለመኖራቸው እንደሆነ እንገነዘባለን:: ድኅረ-ግንቦት የምንረዳው ሃቅ ደግሞ ይባስ ተብሎ እነኝኸ በከፍተኛ ተጋድሎና መስዋዕትነት ዳዴ ሲሉ የነበሩና በማቆጥቆጥ ላይ የነበሩ የቀጨጩ እሴቶች እንዲከስሙ ተዘምቶባቸዋል:: እንደ ነፃ ኅትመትና ስርጭት (ፕረስ) የመሳሰሉት ክፍሎች በአስተማማኝ ሁኔታ በሌሉበት አገር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እገነባለሁ ብሎ ማሰብ ደግሞ እጅና እግርን ታስሮ ለመዋኘት ወይም ዓይንን ጨፍኖ (ተጋርዶ) በሊማሊሞ መኪና ማሽከርከር እንደመሞከር ይቆጠራል::

ገዥው ፓርቲና መሪዎቹ በሕዝብ ድምፅ ለመዳኘት ፈቃደኝነትም ይሁን ዝግጁነት እንደሌላቸው ምርጫ ዘጠና-ሰባትን ተከትሎ የታየው ክስተት አረጋግጧል:: የአቶ መለስ አገዛዝ በወሰደው እርምጃም ገዥው ፓርቲ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሆድና ጀርባ እንዲሆንና አንዳንድ ደጋፊዎቹን ሳይቀር ያስደነገጠ ችግር ውስጥ እንዲገባ እንዳደረገው ግልጽ ነው:: ያ ድኅረ-ምርጫ የታየ የሕወሓት/ኢሕአዴግ ባህሪም በገሃድ ያረጋገጠው የድርጅቱን ጥንካሬና ብስለት ሳይሆን ከአሥራ-አራት ዓመታት በኋላ ተመልሶ ጫካ እንዲገባ የሆነበትን ከፍተኛ ድክመቱን ብቻ ነው::

በአኳያው በምርጫው የተሳተፉም ይሁን ያልተሳተፉ ተቃዋሚ ድርጅቶች በገዥው ፓርቲ የተወሰደውን አምባ-ገነናዊ እርምጃ ለመቋቋም የሚያስችል ድርጅታዊ ብቃትም ሆነ ዝግጅት እንደሌላቸው በገሃድ አጋልጧል:: ቆራጡና አስተዋዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይኸ ሁኔታ ሊደርስ እንደሚችል በቅድመ-ምርጫ እንቅስቃሴዎች ወቅት ስጋቱን ለተቃዋሚ ድርጅቶች ማሳወቁ አይረሳም:: ለዚህም ነበር በዚያ ምርጫ ሂደት ወቅት ሕዝቡ ለተቃዋሚው የሰጠው ድጋፍ ከወደ መጀመሪያው አካባቢ ይልቅ በመጨረሻዎቹ ሁለት ወራት ይበልጥ ጉልህ፣ ግልጽና አደባባይ በወጣ መልኩ ጎልቶ የታየው:: ሆኖም ሕዝቡ ያየውን ስጋትና ጥርጣሬ ብዙ ድርጅቶች አይተውታል ማለት አይቻልም:: በእርግጥም እስከዚያን ጊዜ ድረስ የሕወሓት/ኢሕአዴግን አካሔድና ተግባሮች በተግባር የተመለከተው የኢትዮጵያ ሕዝብ ገዥው ፓርቲና መሪዎቹ በሕዝብ ፍላጎት ያለመገዛት አቋም እንደሚኖራቸውና የሰጠው ድምፅ ሊቀለበስና ሊሰረቅ እንደሚችል ሊጠረጥር የማይችልበት አንዳችም ምክንያት አልነበረውም::

የኢትዮጵያ ሕዝብ የግንቦት ድሎቹን ላለማስነጠቅ ያደረገው ትንንቅና እሱን ተከትሎ በገዥው ፓርቲ (ሕወሓት/ኢሕአዴግ) የደረሰበትን ሁል-አቀፍ ግፍና መከራ ለመቋቋም ከዳር እስከዳር በተደራጀ መልክና ቀጣይነት ሊኖረው በሚችል መልክ ባይሆንም ባመቸው ሰላማዊ መንገድ ሁሉ ታግሏል:: ሆኖም በረጅም ጊዜ ትግሉና በከፈለው ከፍተኛ መስዋዕትነት ያስገኛቸውን የግንቦት ድሎች በቁርጠኝነት ለማስከበር ቀርቶ የታሰሩ መሪዎቹን ለማስፈታት እንኳ ሥርዓት ባለውና በተቀናበረ መልክ የሚከፍለውን መስዋዕትነት በሚመጥን ደረጃ የሚመራው ሁነኛና ብቁ ድርጅት እንዳላገኘ በቁጭት የሚታወስ ነው:: ይኸ በመሆኑም ሕዝቡ የናፈቀው፣ የታገለለትና መስዋዕት የሆነበት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንዳሰበውና እንደተመኘው ሳይሆን በገዥው ክፍል የጊዜ ሰሌዳና እንዳሻው እንዲቀጥል መደረጉን በሃዘኔታና በትዝብት ተመልክቶታል::

ምርጫ ዘጠና-ሰባትን ተከትሎ ገዥው ፓርቲ በወሰዳቸው እርምጃዎችና እነኝህን አምባ-ገነን እርምጃዎች ለመቋቋም ተቃዋሚው ክፍል አንድነቱን አጠንክሮ ሕዝብን ማዕከል ያደረገና የተቀናበረ ጠንካራ ትግል የማድረግ ብቃት አለመኖር ተረዳድተውና ተደጋግፈው፤ በአንድ በኩል የሕዝቡ የተሻለ ሥርዓት የማግኘት የቆየና የጋለ ፍላጎቱ ህልም ሆኖ እንዲቀር፣ ተስፋው እንዲጨልም እየተደረገ፣ ከእጁ የገባው ድል ዓይኑ እያየ ሲነጠቅ በሕጋዊ ትግል በተለይም በምርጫ ፖለቲካ ላይ ያለው እምነት እየሟሸሸ እንዲሄድ፣ ለአንድ ሕዝብ ተቻችሎ፣ ተግባብቶ፣ ተከባብሮና ተደጋግፎ እንደ ሕዝብ የወደፊት ዕድሉን በጋራ እንዳይመክር ጠንቅ የሆኑ ጥላቻ፣ እርስ በርስ መጠራጠር አለመተማመንና ፍራቻ፣ ቅስም መሰበር፣ ወዘተ... ተመልሰው እንዲሰፍኑ እየተደረገ ይገኛል:: እነኝህ አሉታዊ ክስተቶች እንዲቀጥሉና ሥር እንዲሰዱ ዕድል ከተሰጣቸው ሕዝቡ ለአምባ-ገነን አገዛዝ ይበልጥ እንደሚጋለጥ የታወቀ ነው:: ቅስሙ የተሰበረ ሕዝብ ደግሞ ለአምባ-ገነኖች ግፍ የተመቸ መሆኑ የታወቀ ነው:: ይሁንናም የኢትዮጵያ ሕዝብ በግንቦት ዘጠና-ሰባት ቁርጠኛ እርምጃው ላይመለስባቸው በመወሰን አሽቀንጥሮ የጣላቸው የመከፋፈል፣ የፍራቻ፣ አምባ-ገነን ሥርዓትና በአመፅ ላይ የተመሠረተ የገዥዎች የሥልጣን ዝውውር ተመልሰው በራሱ ላይ እንዳያንሰራፉ በቻለው መንገድ ሁሉ መታገሉንና መስዋዕት መክፈሉን ግን አላቆመም፣ አያቆምምም::

ሕዝባችን በመራር ትግሉ በትእግስት ቀስ በቀስ እየገነባቸው የመጡ መሠረታዊ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዋስትና የሚሆኑ መዋቅሮችም በገዥው ፓርቲ ኃላፊነት የጎደለውና አርቆ ያላዬ እርምጃ በሚያሳዝን መልኩ እንዲከስሙ ተደርጓል:: ይኽ አድራጎት የሕዝቡን ትግል በብዙ ዓመታት ወደ ኋላ እንደወሰደውና የብሩኅ ተስፋ ጉዞውንም እንዳደበዘዘው አሌ የሚባል አይደለም:: ይኽም ክስተት በአገራችን መደረግ ያለበትን የእርቅና የሰላሙን ሂደት የበለጠ እንዳወሳሰበው ለድርጅታችን ግልጽ ነው::

በአሁኑ ጊዜ በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፈው ክፍል ቅድመ-ምርጫ ያለው በአደባባይ የሚታይ አንፃራዊ ጥንካሬ የለውም:: እንደሚታወቀው አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሦስት ኃይሎች አማካይነት ተሰባስቦ ነው ወደ ምርጫው የፖለቲካ ትግል የገባው:: እነዚህ ሦስት ኃይሎች ማለት ገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግና በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፉት ቅንጅትና ኅብረት ወደ ምርጫ ፺፯ ሲገቡ የአደረጃጀት፣ የአሠራርና የአገራችንን ችግሮች በመፍታቱ እረገድ የአቋምና የእምነት ልዩነቶች ነበሯቸው:: ሦስቱን አንድ የሚያደርጋቸው ሁሉም የድርጅቶች ስብስቦች መሆናቸው ነው:: ሆኖም ግን ኢሕአዴግ በአባልነት ያቀፋቸው ድርጅቶች በብሔረሰብ (በጎሣ) የተደራጁ ሲሆኑ በቅንጅት በኩል በተቃራኒው አባል ድርጅቶቹ በኅብረ-ብሔረሰብ የተደራጁ ናቸው:: እንዲያውም በብሔረሰብ (በጎሣ) የተደራጀ የቅንጅት አባል ሊሆን እንደማይችል መሪዎቹ ግልጽ ማድረጋቸው ይታወሳል:: ስለሆነም ሁለቱም ማለት ቅንጅቱና ኢሕአዴግ በተወሰነ መልክ ብቻ ለተደራጁ ክፍሎች ክፍት የሆኑ ወይም የተከለሉ (Exclusive Clubs) ናቸው ማለት ይቻላል:: የኅብረቱ አደረጃጀት ከሁለቱ የተለየ ወይም ሁለቱንም ያቀፈና አግላይነት የሌለበት ማለት በኢትዮጵያ አገራዊ አጀንዳ ሥር በብሔረ-ሰብም ሆነ በኅብረ-ብሔረሰብ መልክ ለተደራጁ ሁሉ ክፍት በመሆኑ በዴሞክራሲ ሂደት ግንባታ ትግሉ መሠረተ-ሰፊ እንቅስቃሴ ለማድረግ የተሻለ ዕድል ነበረው ማለት ይቻላል::

እነዚህ ሦስት ኃይሎች በተለያየ መልክ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ቅድመ-ምርጫ የነበራቸው ጥንካሬም ሆነ ይዞታ ላይ አይደሉም:: በእርግጥ ገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግ የሕዝብ ድምፅ በአደባባይ ቀምቶ የመንግሥትን ሥልጣን በጥሬ ጉልበት መያዙን ቀጥሏል:: ይኽንን ዓይን ባወጣ መልክ ሥልጣን የጨበጠው ግን በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ብቻ ሳይሆን በዓለም-አቀፍ ደረጃም ጭምር እራሱን አጋልጦና የተአማኒነት ካባውን አውልቆና እርቃኑን ቀርቶ ነው:: ምንም እንኳ የመንግሥት ሥልጣን መጨበት የሚያስገኘውን ሁለንተናዊ አቅሞች በመሣሪያነት በመጠቀምና ያለ የሌለ ኃይሉን አሰልፎ ሕዝብን በማስፈራራት፣ በመደለልና ውለታን ለመግዛት በመሞከር ጠንካራ ሆኖ ለመታየት ቢሞክርም፣ (በቅርቡ

በተደረገው “የአካባቢ፣ የወረዳና የማሟያ ምርጫ” አራት ሚሊዮን ተወዳዳሪዎች አሰለፍኩ ብሎ እንደፎከረው)፣ ሃቁ ግን በዚያ ምርጫ ዘጠና-ሰባትን ተከትሎ በወሰደው ጨካኝ እርምጃና ባሳየው ባህሪ ኢሕአዴግ ቅድመ-ምርጫ የነበረችውን አነስተኛ ተቀባይነት ጨርሶ ያጣበትና ከሕዝብ ጋር የበለጠ የተቃቃረበት ሁኔታ ውስጥ መሆኑ ግልጽ ነው።

በአጠቃላይ ሲታይ በሚከተሉት ምክንያቶች ከግንቦት ዘጠና-ሰባት ታሪካዊ ኩኔት ከተቃዋሚው ክፍል ይበልጥ ገዥው ፓርቲ ብዙ ትምሕርት ቀስሟል ማለት ይቻላል።

1. ከደርግ አገዛዝ መወገድ ጀምሮ ሙሉ በሙሉ በገዥው ፓርቲ ይሁንታና ድጋፍ ባይሆንም በተፈጠረው አንፃራዊ ክፍተት በመጠቀም ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ የሲቪክና የሙያ ማኅበራትና ተቋማት በመንግሥት በኩል የሚደረግባቸውን ከፍተኛ ጫና ሁሉ ተቋቁመው ማቆጥቆጣቸው ይታወቃል። በዚህ ረገድ በተለይም የነፃው ፕረስ በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው። በዚህ ክፍል (ነፃው ኅትመትና ስርጭት- ፕረስ) የተሰለፉ ቆራጥ ዜጎች እየታሰሩ፣ እየተፈቱ፣ አይቀጡ ቅጣት እየተቀጡ፣ እየወደቁና እየተነሱ ባደረጉት ትግል ሕዝባችን በአገራችን የቆየውን የመንግሥት ሥልጣን በያዘ ክፍል ላይ ግልጽ ወቀሳና ትችት የማድረግን “የነውርነት” ጭምብል ቀስ በቀስ የገፈፈና በውስጡ የተዳፈነ የለውጥ ፍላጎቱንና ስሜቱን አንገቱን ቀና አድርጎ በይፋ እንዲገልጽ በማስቻሉ ለግንቦት የሕዝብ ድሎች ቀጥተኛ አስተዋጽዖ እንዳደረገ ገዥው ክፍል በሚገባ ተረድቷል።

2. ሕዝቡ ድምፁን በነፃ ለመግለጽ ዕድሉን ካገኘ ማንም በሚያደርገው የተለመደ የጥቅም ድለላም ሆነ ማስፈራራት፣ አልፎም እስራት፣ ግርፋትና ግድያ፣ በተለይም ደግሞ ገለልተኛ ታዛቢ ባለበት ሁኔታ፣ በብቸኝነት የሚሰጥን ድምፅ ሊያስቀይር ወይም ሊለውጥ እንደማይቻል የኢሕአዴግ ቁንጮዎች በደንብ ተገንዝበዋል።

3. እንዲሁም የዜጎችን ቀልብ በሳበ መልክ ለአገርና ለሕዝብ የሚጠቅሙ የተሻሉ አማራጮችን ለሕዝብ የሚያቀርብ የተደራጀ የአንድነት ኃይል ዕድሉን አግኝቶ ከተሰለፈ ሕዝብ አመኔታውን ሊጥልበት፣ ሊከተለውና ሊደግፈው ብቻ ሳይሆን አብሮት ሊቆምና መስዋዕት ሊሆን እንደሚችልና እንደተዘጋጀ አገዛዙ ጠንቅቆ ተረድቷል።

4. እ.አ.አ. ከመስከረም አሥራ-አንድ ሁለት ሽህ አንድ ዓ/ም ወዲህ በተቀየረው የዓለም ፖለቲካ እንዲሁም በአካባቢው የዋለለና አሳሳቢ የውጥረት ሁኔታ ምክንያት ከደጋፊዎቹና ከእርዳታ ለጋሽ አገሮች በኩል አንፃራዊ ወታደራዊ ጥንካሬና ለሚጠየቀው ትብብር ሁሉ ዝግጁና ታዛዥ እስከሆነ ድረስ እንዲሁም ተቃዋሚው በተበተነ መልክ እስከቀጠለ ድረስ በራሱ ሕዝብ ላይ በሚወስዳቸው እርምጃዎች እንኳን ግንኙነትና እርዳታ ማቋረጥ ብዙ ጫናና ይፋዊ ኩነና እንደማይደርስበት አገዛዙ በሚገባ አውቋል።

**ስለሆነም ገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግ፤ ምናልባትም የአመራር ለውጥ ወይም አሁን ባሉት መሪዎች ዘንድ እጅግ ከተአምር የሚቆጠር መሠረታዊ፣ የምርና ከልብ የተደረገ የአስተሳሰብ ለውጥ ከሌለ በስተቀር፤ ከአሁን በኋላ ያ በአቶ መለስ አነጋገር “የተሰላ ምናልባታዊ አደጋ” (Calculated risk) የሚወሰድበት ሁኔታ ዳግም ተመልሶ ይመጣል የሚል ግምት ሊኖር አይችልም። ገዥው ፓርቲ ከግንቦት ሰባት ዘጠና-ሰባት ማግስት ጀምሮ በአንድ በኩል ያ ሁኔታ እንዳይደገም እነዛን ተቋማት እንዳልነበሩ ለማድረግ፤ ሕዝቡም በራሱ ተመክቶ፣ በተቃዋሚ ድርጅቶች ተማምኖ፣ አንገቱን ቀና አድርጎና በድምፁ ኃይል የሚፈልገውን ለውጥ ለማምጣት እምነቱና ድፍረቱ እንዳይኖረው ቅስሙ እንዲሰበር በማድረግ፣ በሌላ በኩል ተቃዋሚው በማንኛውም የአገሪቱ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ የሚኖረው ሚና እራሱ ገዥው ፓርቲ ባሰመረለት ተቃዋሚ አለ ለማሰኘት ለይስሙላ ያኽል ከአጃቢነት ባልተለዬ ቀጭን መሥመር ብቻ እንዲወሰንና በማንኛውም ምርጫ በተባለ ጉድ ከላይ እስከ ታች እሱና ተባባሪዎቹ ብቻ “በአቸናፊነት” የሚሰየሙበት ሁኔታ እንዲመቻች ለማድረግ ያለ የሌለ ኃይሉን በማረባረብ ላይ ተሰማርቶ ቆይቷል። ውጤቱም ከስሊቱ ውጭ እንዳልሆነ**

**በአጠቃላይ ከምርጫ ዘጠና-ሰባት ወዲህ በተከተላቸው ሂደቶችና በተለይ በቅርቡ በተደረገው "የማሚያ፣ የወረዳና የቀበሌ" ምርጫ በማያሻማ ሁኔታ በደንብና በግልጽ ታይቷል።**

በአጠቃላይ ሲታይ ገዥው ፓርቲ በተለይ ከምርጫ ዘጠና-ሰባት ወዲህ የሚያደርጋቸው ድርጅታዊ እንቅስቃሴዎች የሚያመላክቱት በአገሪቱ ላይ የአንድ ፓርቲ ብቸኛ የበላይነት በማያወላዳ መልኩ እንዲደላደል የሚያደርግና የመድብለ-ፓርቲ ሥርዓት ቅታው ጠፍቶ የአገሪቱ አጠቃላይ ዕድል በኢሕአዴግ አልፎም በአንድ ግለሰብ ብቻ እንዲወሰን የሚያደርግ ነው። ይኽ የአንድ ፓርቲን ሁለንተናዊ የበላይነት በአገሪቱ ላይ ለማስፈን የሚደረግ ከፍተኛ ጥረትም እውነተኛ የመድብለ-ፓርቲ ሥርዓት ግንባታ ዕድሉ በጣም እየጠበበ እንደሚሄድና ከናካቴው ለማክሰም አገዛዙ ለሚያደርገው ቁርጠኛ ጥረት ጠንካራ አመላካች ነው።

ከላይ በአጭሩ እንደተጠቀሰው ውድ አገራችን በዙሪያ-ጥምጥም የተዘበራረቀ ሁኔታ ውስጥ ትገኛለች። ይኽ የተዘበራረቀ ሁኔታም አገራችንን ከመቸውም ጊዜ በበለጠ እጅግ ፈታኝና ውጤቱ ሁሉንም በጣም ወደሚጎዳ የባሰ አደገኛ አዘቅት በሚገርም ፍጥነት እየወሰዳት ይገኛል። የሕወሓት/ኢሕአዴግ የአገዛዝ ሥርዓት የሕዝብን ድምፅ ከሻረበት ጊዜ ጀምሮ በሠራውና በሚሠራው የተደራረበ ስህተት ከሕዝብ ጋር ይበልጥ ተቀያይሞ ያለበትና ሥልጣን ላይ የሙጥኝ ማለትን እንደ ድርጅታዊ ብቻ ሳይሆን አካላዊ የኅልውናው ዋስትና አድርጎ እንደሚያይ በሚያስመስል ሁኔታ ውስጥ መገኘቱ፤ ይኸም ሕዝቡ በአገራችን ላይ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በሚያስተማምን መልኩ እውን እንዲሆን ያለውን ተስፋ እንዳቀጨጨበት አጠያያቂ አይሆንም። ይኽ አደገኛ ሁኔታ ቶሎ አስፈላጊው እርማት ካልተደረገለት የሕዝባችን ምሬት እየጨመረ፣ መካረሩና የባሰ ተስፋ እየቆረጠ መሄዱ አይቀሬ ነው። ይኽ የሕዝብ ምሬትና ተስፋ መቁረጥ እየጨመረ በሄደ ቁጥር ደግሞ ሕዝቡ አሜን ብሎ ከመገዛት ይልቅ በቻለው አቅምና መንገድ ሁሉ የሞት-ሽረት መተናነቅ ለማድረግ የባሰ መቁረጡ የግድ ይሆናል።

**ድርጅታችንን ይበልጥ የሚያሳስበውም አሁን በሰፈነው ሁኔታ ሕዝባችን እንደ አንድ አገር ሕዝብ በአገራችን ላይ እያንዣበበ ያለውን <u>ዓለም-አቀፍ ይዘት ያለውን ሁለ-ገብ ውጥረት</u> ለመቋቋም እንዳይችል ማድረግ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም ለበለጠ አደጋ እንዲጋለጥ ያደርገዋል የሚለው ከፍተኛ ስጋት ነው። የመንግሥት ሥልጣን በያዘው አካልም ይሁን በተቃዋሚው ክፍል በኩል የጉዳዩን አሳሳቢነት በተገቢ ተረድተው የሕዝባችንን የመልካም ሥርዓት ጥማት የሚያረካና ቋሚ ለሆኑ የፍትኅ እጦት፤ የአሳፋሪ ረሃብና ችግር አዙሪት መቀጠል፣ የተላላፊ በሽታዎች መበራከት፣ የተረጋጋ ሰላም አለመረጋገጥ፣ ወዘተ.. የአገር አንድነትን በጠበቀ መልኩ እንደ የአንዲት አገር ዜጎች የወል ብሔራዊ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ወደሚያስችል አቅጣጫ ማተኮር አለመታየቱ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም በተቃራኒው እየተፈራቀቁ የመሄዱ አስደንጋጭ ያፈጠጠ ሃቅ የዛሬውን ሥልጣንም ይሁን ማንኛውንም ጊዜያዊ ጥቅም ሳይሆን የነገን ተተኪ ትውልዶች ዕጣ-ፋንታ ከልብ የሚያስብን ዜጋ ሁሉ የምር ሊያሳስብ ይገባል። እንግዲህ ችግሩ ያለውና አደጋው እዚኽ ላይ ነው። ስለ ነገው ለማሰላሰል ፋታ የሌለው፣ በዕለት-ተለት ኑሮው እንዲባዝን የተገደደ፣ የታፈነ፣ የተማረረና ተስፋ የቆረጠ ሕዝብ ማንኛውንም ጽንፈኛ አመለካከትና ቅስቀሳ ለሚያራምድ ክፍልና እንቅስቃሴ በጣም የተጋለጠ እንደሚሆን የታመነ ነው። በመሆኑም ከተጋፈጠውና ከሚገኝበት ዕለታዊ ችግር የሚያላቅቀውን ወይም አላቅቅሃለው የሚለውን ማንኛውንም ኃይል መከተል ይገደዳል። "የሚሰጥም ገለባ ይጨብጣል" ነውና ሕዝቡም ያ ኃይል የቆመበትን ዓላማ ከመጠየቁ በፊት የሚያየው ለችግሩ ተጠያቂ ነው ብሎ የሚያስበውን ክፍል መቃወሙንና ሊያስወግድለት ወይም ሊያጠቃለት መዘጋጀቱን ብቻ ይሆናል። ስለሆነም አሁን በአገራችን የሚታየው ሁል-አቀፍ ችግርና ውጥረት ለማንኛውም ጽንፈኛ ኃይል መፈጠርና ማደግ አመች ሁኔታን ይፈጥራል የሚል ስጋት አለን። እንደዚህ ዓይነት ኃይሎችም በሕዝብ ዘንድ ዝም ብሎ ከማየት እስከ ቀጥተኛ ትብብር ሊያገኙ፣ ቢያንስ ጠንካራና የተደራጀ ተቃውሞ ላይገጥማቸው እንደሚችል መገመት አያዳግትም።**

*እንግዲህ የሕዝቡን ትግል የሚያስተባብርና የሚመራ መሠረተ-ሠፊና አገር-አቀፍ የአንድነት ኃይል እስከሌለ ድረስ እንደዚህ ዓይነት ኃይሎች የመስፋፋት ዕድል የሚኖራቸው በኢትዮጵያ፣ በኢትዮጵያዊነትና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መኖር ኪሳራ ነው ማለት ነው፡፡ ይኸ አንዱ የአገሪቱን አንድነት አጥብቆ አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ነው፡፡*

*በዚህ እረገድ "የወሰን" ጉዳይ አለኝ የሚለው የሸዓብያ መንግሥት ፀረ-አንድነትና ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎችን ማሰልጠንና ማሰማራትን በተቻለው አቅም ሁሉ ማጧጧፍ ብቻ ሳይሆን የውጥረት ሁኔታውን በማባባስና በመጠቀም አዲስ ወረራ ሊቆሰቁስ ወይም ውጥረቱን የሚያጠናክር ትንኮሳዎችን በተለያዩ መልኮች ሊቀጥል እንደሚችል መገመቱ ከባድ አይሆንም፡፡ ይኸ ደግሞ በተናጠል የሚወሰድ እርምጃ ሳይሆን በውጭ ኃይሎች ቀጥተኛ ድጋፍና ቀደም ሲል በአፍጋኒስታንና በቸቸኒያ፣ አሁን በኢራቅና ከአንድ ዓመት በፊት በሌባኖስ እንደታየው ሁሉ በእኛም አገር ኦጋዴንን ነፃ እናወጣለን ብለው በተሰለፉ ፀረ-አንድነት ኃይሎች አማካይነትና በሌሎችም ጭምር ተባባሪነት አክራሪ የ"ጀሃድ" ጦረኛ ሰርጎ-ገቦች በልዩ ልዩ መልክ ቢያንስ በአጋርነት ሊሰለፉበት በሚችል ሁኔታ በምሥራቁ የአገራችን ክፍል ብቻ ሳይሆን በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች፣ በብዙ በከተሞቻችን፣ ከአሁን በፊት በአገራችን ምድር ታይቶ በማይታወቅ በአጥፍቶ-ጠፊ ስልትም ይሁን በሌላ መልክ ዘግናኝ እልቂት የሚያስከትል ሁከት ሊፈጠር ይችላል፡፡ በአገሪቱ ላይ አጠቃላይ ውጥረት በሚፈጥር በዚህ እርብርብም በተለይ የመገንጠል ጥያቄ ያነሱ ጎላም አነስም ያሉ ኃይሎች ሕዝብን በማነሳሳት፣ የውስጥ ዘር-ምንጠራ* (ethnic cleansing) *እርምጃዎችን በመውሰድና አንዳንድ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ አገሪቱን አጠቃላይ ትርምስ ውስጥ የሚያስገባ ሁኔታ ሊከሰት ይችላል፡፡ አንዳንዶችም በሰላም አስጠባቂ ስም እንደ ተባበሩት መንግሥታት ዓይነት ዓለም-አቀፍ ኃይል በአገራችን ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ የሚጠይቁበት ሁኔታም ሊከሰትና ኢትዮጵያ በአዲስ የጅኦ-ፖለቲካ ቅኝት ውስጥ ልትገባ የምትችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ በሌላው አካባቢ ኢትዮጵያዊ ስም የያዙ በተግባር ግን የአካባቢ እንቅስቃሴዎች በዚህ የ"ከበህ ውጋው" እርምጃ አውቀውትም ይሁን ሳያውቁት አፍራሽ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡ በኛ እምነት "ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ" በሚል ስያሜ ተፈጥሮ የነበረው ስብስብ ተልእኮ ከዚህ የዘለለ አልነበረም፡፡ በአሁኑ ጊዜ ያለው አጠቃላይ የውጥረት ሁኔታ ሲታይ የአገራችን አንድነት ላይ መዝመት መደበኛ ተግባራቸው አድርገው የወሰዱ የቅርብም የሩቅም አገሮች፣ በተለይ እንደ ግብፅ የመሳሰሉ አንዳንድ የአረብ አገሮች፣ ከመቸውም ጊዜ የበለጠ በአገራችን ላይ በእጅ አዙር ለመዝመትና አንድነቷን አጥብቀው ለመፈታተን የሚያስችል አመች ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል ማለት ይቻላል፡፡*

*ሶማሊያ ማዕከላዊ መንግሥት አልባ ከሆነችበት ከ፹፫ ዓ/ም ጀምሮ በተፈጠረው ሥርዓት ያጣ የውስጥ ትርምስ ሳቢያ በእስልምና ስም ለተነሳው የዘመኑ የአክራሪዎች እንቅስቃሴ መነሃሪያና የመንቀሳቀሻ ማዕከል ለመሆን አመች እየሆነች የመጣችበት አደገኛ ሁኔታ መከሰቱ ይታወቃል፡፡ ይኸንን አጋጣሚ፣ ምንም እንኳ በአገራቸው ላይ የአክራሪ እንቅስቃሴ እንዳይኖር የሚችሉትን ሁሉ እያደረጉም እንኳ ቢሆን፣ ሳውዲ አረቢያ፣ ግብፅ፣ ኢራን፣ ሲሪያ፣ ሊቢያ፣ ወዘተ... በስመ ሐይማኖት በኢትዮጵያ ላይ ትርምስ ለመፍጠር ያነጣጠረ መረባረብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እያደረጉ ይገኛል፡፡ የዓባይን ውሃ ለእኛም፣ ለሱዳንም ሆነ ለግብፅ በመግባባትና በድርድር በሰላማዊ መንገድ መጠቀም ሲቻል በተለይ ግብፅ ሁል ጊዜ የዚኸ የውሃ ሃብትና ምንጭ ብቸኛ ባለቤትና ተቆጣጣሪ ለመሆን የቆየ ዓላማ እንዳላት የታወቀ ነው፡፡ ይኸ ስጋት የወለደው የግብፅ ትዕቢት ደግሞ በተዘዋዋሪ ኢትዮጵያን የማዳከም ተግባር ላይ እንድትሰማራ ማድረግ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊ ሲሆን ቀጥተኛና ሙሉ ወረራ ለማድረግም ተዘጋጅታ የተቀመጠች አገር መሆኗን ማንም ለአፍታ ሊዘነጋው አይገባም፡፡ በዚኸ ረገድ አዲስ የነዳጅ አምራችና ታዳጊ ሃብታም ለመሆን እየጣረች ያለችው ሱዳን በኢትዮጵያ የውሃ ባለቤትነት ላይ ያላት የቆየ ስጋትና ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ባትችል እንኳ ቢያንስ ጥላዋን ለማሳረፍና ሲቻልም ቅኝ ገዥዋ የነበረችው እንግሊዝ ኢትዮጵያን ለማዳከም በነበራት ያላቋረጠ ዓላማ በኬንያም፣ በሶማሌም ሆነ በሱዳን አዋሳኞች የሚገኙ የአገራችንን መሬቶች በተለመደ መሰሪ አሠራራቸው በራሳቸው ፈቃድ "ለማካለል" የተደረጉ ሙከራዎችን መሠረት በማድረግ አንዳንድ ቦታዎችን ይገቡኛል ለማለትና*

በእጃቸው ሥር ለማድረግ መሞከራቸው አይቀርም። በዚኽ ረገድ ሰሞኑን በጀኔራል አልበሽር የሚመራው የሱዳን መንግሥት በኢሕአዴግ ተለግሶኛል በሚል የወሰደውን እርምጃ ድርጅታችን አጥብቆ የሚኮንነው ብቻ ሳይሆን የሚታገለው ጉዳይ ነው። ይኽን በተመለከተ መወሰድ ይኖርበታል ብለን የምናምንበትን ምላሽ በቅርቡ ስለ ጉዳዩ ባወጣነው መግለጫ ላይ ገልጸናል። እየተበላሸ ሊሄድ የሚችለው የራሷ የውስጥ ሁኔታ፣ በተለይ በደቡብ፣ በምዕራብ (ዳርፉር)፣ በተወሰነ ደረጃ በምሥራቅ (በከሰላና ፖርት ሱዳን አቅጣጫ) ፋታ አሳጥቷት ገድቦ እስካልያዛት ድረስ ሱዳን እስካሁን ባላት ታሪክ በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ እጇን ከማስገባትና ከመተናኮል ወደ-ኋላ የምትልበት ብዙ ምክንያት አይኖርም።

የኒኩሊየር መሣሪያ ባለቤት ለመሆን እየተጣደፈች ያለችው ኢራን ምኞቷ ከተሳካላት፣ የዝንታለም ፀረ-ኢትዮጵያ አቋም አራማጇ አጠገባችን ያለችው ግብፅ በአሥር ዓመታት ውስጥ የባለ ኒኩሌር መሣሪያ ታጣቂ ለመሆን እንደምትገፋፋና ባለቤትም ለመሆን እንደምትችል አያጠራጥርም። እንዲሁ "አያድርስ" የሚል የሰነፍ ፈሊጥ እንከተል ካልተባለ፣ እንኳን ደካማና አንድነቷ የተናጋ ኢትዮጵያ "በደኅናም" ጊዜ ቢሆን እንደዚህ ዓይነቱን ሁኔታ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በቸልታ ሊያየው ወይም በቀላሉ ሊወስደው አይገባም እንላለን። በዚኽ ፀረ-ኢትዮጵያ እርብርብ ሌላው ቀርቶ በቅርብ የሚገኙ የሸዓብያዋ ኤርትራና ጅቡቲ ነገ እራሳቸውን ሊለበልብ የሚችል እሳት ቁስቆሳውን መያያዛቸውን በትዝብት እያየን ቢሆንም በቸልታ ሊታለፍ ግን አይገባውም እንላለን።

የአካባቢውን ሕዝብ በሙሉ አንድ ሐይማኖት እንዳይከተል እንቅፋት የሆነችው ኢትዮጵያ እንደሆነች የገመቱና ያመኑም ይሁኑ እንደ ግብፅ የውሃ ሃብታችንን ለመቆጣጠር በመፈለግ ወይም መሬት ይገባኛል ባዮቹ ሱዳንና ሶማሌ ወይም የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል ነውና በዚኽ መኻል የራሴን "ነፃ አገር" አቋቁማለሁ ብሎ የሚያልመው ተገንጣይ፣ ሁሉም በየፈርጁ የሚያደርገው ግፊት ኢትዮጵያን በማዳከሙ ዓላማ ላይ ፍላጎታቸው ይገናኛል። በአሁኑ ጊዜ በዚኽም በዚያም በየአቅጣጫው የሚታየውና ያለው የተወጣጠረ የውስጥ፣ የአካባቢና የዓለም-አቀፍ ሁኔታ አገራችን ለዚህ አልፎ አልፎ ሲያገረሽ ለኖረ ዙሪያ-ጥምጥም ችግርና ለበለጠ አደጋ እንድትመቻቸና እንድትጋለጥ እያደረጋት ይገኛል።

በዚኽ አደገኛ ሁኔታስ የዓለም-አቀፍ ኅብረተሰብ በተለይም እንደ የአሜሪካና የአውሮጳ ወይም የቻይና፣ የጃፓን፣ የሕንድ፣ ወዘተ... አቋም ምን ይሆናል? ብሎ መጠየቁም ተገቢ ይመስለናል። ይኽንን በአጭሩ መመለስ ይቻላል። ምን ጊዜም መረሳት የሌለበት እነዚኽ ኃይሎች የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጡት <u>የራሳቸውን ጥቅም ብቻ ነው።</u> አሜሪካኖች "ቋሚ ጥቅም እንጂ ቋሚ ወዳጅ የለም" እንዲሉ ዴሞክራሲ፣ የሰው ልጅ መብት፣ የሕግ የበላይነት፣ ወዘተ.... የሚባሉት ሁሉ ተቀጥላና ከጥቅማቸው አኳያ ሲታዩ የቅንጦት አባባሎች ናቸው። በዚኽ ላይ እኛ ደግሞ ያለነው አፍሪቃ ውስጥ ነው። በአሁኑ የዓለም-አቀፍም ሆነ የአካባቢ ሁኔታ እነሱ ቅድሚያ የሚሰጡት መረጋጋት (stability) ለሚሉት ጉዳይ ነው። በእርግጥ ማንኛውም የቀውጢ ሁኔታ ባለበት ቦታ ሁሉ መረጋጋት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ነገር ነው። በአሁኑም የአገራችን ሁኔታ እነዚህ የውጭ ኃይሎች ይበልጥ የሚያዩት በመስክ ላይ ያለውን የኃይል ሚዛን ነው። ምን ጊዜም ቢሆን በተለይ ደግሞ አሁን ባለው በሽብርተኞች ላይ ባለው ዓለም-አቀፍ ስጋት ሁሉም ወደ ውጭ ያንጋጠጡ የበለጸጉና በፍጥነት እያደጉ ያሉ አገሮች የውጭ ግንኙነት ፖሊሲያቸውን የቃኙትና እርዳታና ትብብራቸውን እያደረጉ የሚገኙት በአክራሪ አሸባሪዎች ላይ ካላቸው ከፍተኛ ስጋት አኳያና እያደገ የመጣውንና ተሻሚ የበዛበትን የጥሬ ሃብት (በተለይም ነዳጅ) ፍጆታቸውን በተመለከተ 'ማን የተሻለ ይጠቅመኛል' በሚለው አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ግልጽ ነው። ድጋፋቸውን የሚሰጡት ወገን አቋሙ፣ የሚከተለው ዕምነት ወይም በአገሩ ውስጥ በራሱ ሕዝብ ላይ የሚያራምደው ፖሊሲ ምን ይሁን ምን ብዙም አይገዳቸውም። ስለዚህ ማንኛውም ክፍል ከውጭ ደጋፊዎች የሚያገኘው እርዳታ በቅድሚያ አሁን ባለው ዓለማቀፋዊ የጥቅም ፍትጊያ (ግሎባላይዜሽን) የነዳጅና የሌሎች ጥሬ እቃዎቻ (ሃብቶች) ለማግኘት የሚደረገውና እንዲሁም የሽቀጥ ማራገፊያ ገበያ ሽሚያ ዓይነተኛ የውድድር ሁኔታ ይበልጥ

የሚጠቅማቸውንና ይኸንን ጥቅም የሚፃረር ክፍልን የተሻለ ሊቃወም (ሊመክት) የሚችልን ማንኛውም ኃይል ዓይናቸውን ጨፍነው ይደግፋሉ። ከዚኽ ስሊት በመነጨም ቀደም ሲል እንደቆየው የአንድ አገር አንድነት አደጋ ላይ ሲወድቅ አንድነቱ እንዲከበር የሚያደርጉት ነገር ብዙም አይኖርም፣ ይኸን ያኽልም የሚገዳቸው አይሆንም።
(አሜሪካዊው መሪ ከአሁን በፊት "ሰውየው የእንትን ልጅ ነው፣ ቢሆንም የእኔ የእንትን ልጅ ነው" ስለዚህ ግዴለኝም ... ብለው የለ። ብዙ እንቅስቃሴዎች ይኸንን ስሊት በሚገባ የተረዱት መሆኑን ቢያንስ በ"ኦጋዴን ነፃ አውጭ" ድርጅት ዙሪያ እየተደረገ ካለው ማየት ይቻላል። ሆኖም "የአንድነት" ኃይል ነኝ ከሚለው ክፍል ውስጥ ምን ያኽሉ ይኸንን እንደተገነዘበ የሚያጠያይቅ ነው።)

ወደፊት የዓለም ልዕለ-ኃይል ትሆናለች ተብላ የምትጠረጠረው የቻይና የጦፈ የኤኮኖሚ እድገት ያስከተለው እንደ ነዳጅ የመሳሰሉ ጥሬ ሃብቶችን ለማግኘት የሚደረግ የተራበ የቀን ጅብ ዓይነት ጥድፊያ የብዙ ተቀናቃኝ በተለይ የምዕራቡን ዓለም አገሮች ትኩረት እየሳበ ይገኛል። በቻይና በኩል የሚታየው ጥሬ ሃብትን ለማግኘት መስገብገብና መጣደፍ ብዙዎች በተለይም የምዕራቡ ዓለም ከጠበቁት በላይ ሥር እየሰደደና እየተጠናከረ ነው። ቻይና በአፍሪቃ ላይ የምትከተለው አካሄድ ጥሬ ሃብት (በተለይም ነዳጅ) ለማግኘትና ሸቀጦቿን ማራገፊያ ያልተነካ ገበያዋን ከማስፋቱ አኳያ የታለመ ነገር እንደሆነ ግልጽ ነው። ይኸንን ጥቅም ለረጅም ጊዜ በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስጠበቅ በአጭር ጊዜ ውስጥ በብዙ አሥር ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ቻይናውያን በአፍሪቃ እንደሚሰፍሩ ይገመታል። በዚኽ ረገድ ሕንድም የበኩሏን "ድርሻ" ለማግኘት እየተጣደፈች መሆኑ በጉልህ እየታየ ነው። ቻይና ብዙ አቅጣጫ ያለው ጥቅምና ፍላጎቷን ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ከአፍሪቃ አገሮች ጋር ያላትን የኤኮኖሚ ትስስር ለማጠናከር በተባበሩት መንግሥታት ያላትን ውሳኔ የመግታትና የመሻር አቅምና ሥልጣን (veto power) ጭምር ከመጠቀም ወደ-ኋላ እንደማትል ሱዳንና መሰል አገሮችን በተመለከተ እየወሰደችው ባለው አቋም እየታየ ነው። ቻይና ወደ-ፊት በአፍሪቃ ያላት ይዞታ እንዲሁ በቀላሉ የሚታይ ጉዳይ አይደለም። የዓለም ነባርና አዲስ ባለሃብቶች በአፍሪካ ጥሬ ሃብቶች ላይ የሚያደርጉትን መረባረብና መራኮት በቅርብ ለሚከታተል ምናልባትም የምዕራቡ ዓለምና ቻይና ወደ ወታደራዊ ግጭት (ፍልሚያ) ካመሩ በእስያ ወይም በፓሲፊክ ውቅያኖስ ላይ ከመደረጉ በፊት በአፍሪቃ ምድርና በኅዋ (space) ላይ እንደሚሆን መገመት ይቻላል።

## <u>III. የድርጅታችን መሠረታዊ እምነቶች፤</u>

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ (ኢዴኅአን) በፖለቲካ መርኃ-እቅዱ (ፕሮግራሙ) ላይ እንዳስቀመጠው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ አንድ ሕዝብ የመኖር፣ ኢትዮጵያም አገራዊ አንድነቷና ሉዓላዊነቷ የተከበረ አንድ አገር ሆና እንድትቀጥል እና በአገራችን የአምባ-ገነን አዙሪት ተሰብሮ ሕዝባችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት እንዲሆን ለማስቻል የበኩሉን ቁርጠኛ አስተዋጽዖ ለማድረግ አገር-አቀፍ ይዘት ባለው መልክ ሕዝባዊ ይዘት ያለው ሰላማዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ የተሰለፈ ድርጅት ነው። በአሁኑ ጊዜ ድርጅታችን በንቅናቄ ስም የተደራጀው ለፖለቲካ ሥልጣን ለመሮጥ ሳይሆን በአገራችንና በሕዝባችን ላይ የተደቀኑ አስጊ ሁኔታዎች ተወግደው የፖለቲካ ድርጅቶች የፖለቲካ ድርጅታዊ ሥራቸውን መሥራት የሚችሉበት ሁኔታ እንዲመቻች የበኩሉን ድርሻና አስተዋጽዖ ለማድረግ ነው። በቅድሚያ በሁሉም ዘንድ የአስተሳሰብ ለውጥን የሚጠይቀው ይኽ ትግል ቀላል እንዳልሆነም በሚገባ እንገነዘባለን።

ኢትዮጵያ በአፍሪቃ ነፃነቷን አስከብራ የኖረች ብቸኛዋ አገር መሆኗ፣ የምትገኝበት ስትራቴጅአዊ የመልክአ-ምድር አቀማመጥና ተፈጥሮ የለገሳት ሃብት፣ በተለይም የውሃ ሃብቷ፣ ብዙዎች እንዲያተኩሩባትና አንድነቷን አጥብቀው እንዲጠናወቱ አድርጓቸዋል። ወደፊት በአፍሪቃ ቀንድና በመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ ባሉ አገሮች መኻል የሚደረገው

ግጭትና ጦርነት በውሃ ሃብት ሽሚያና ቁጥጥር ምክንያት እንደሚሆን የሚያጠራጥር አይሆንም። በመሆኑም "የውሃ ጋን" የሆነችው አገራችን ላይ የትኩረት ትኩረት ቢደረግና አንድነቷና እድገቷ ላይ መረባረብ ቢደረግባት የሚጠበቅ ብቻ ሳይሆን አይቀሬ አድርጎ መውሰዱ ተገቢ ይሆናል። አንድነት የሌለው ሕዝብ ደግሞ አገሩን ለውጭ ጠላት ወረራና ቁጥጥር አመችና ጋባዥ ሁኔታን እንደሚፈጥር ግልጽ ነው። እንግዲህ የአገራችን ሁኔታ ይኸ ከሆነ ደግሞ ለኢትዮጵያውያን አንድነታችንን የመጠበቁ ጉዳይ ለጋራ ኅልውናችን ቁልፍ ጥያቄና አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል። ይኸ አንድነት ደግሞ ተፈታታኙ በዝቷል። መብዛት ብቻም ሳይሆን በአሁኑ ወቅት ደግሞ አመች ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ እምነት የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን መብቱን የሚጎናፀፈው በ'አንድ ሰው አንድ ድምፅ' መርኅ ዓለም-አቀፋዊ መስፈርቶችን ባሟላ የድምፅ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት መሠረት የሚፈልገውን መንግሥት ማቋቋም ሲችል ብቻ ነው። ይኸም እውን መሆን የሚችለው ደግሞ የሰከነ ሽግግር ለማድረግ እንዲቻል በእርቅና ሰላም የታጀበ ሁሉን ያቀፈ ዴሞክራሲያዊ የሽግግር ሂደት መከተል ሲቻል ብቻ ነው። በኛ እምነት ይኸ ደግሞ ቅድሚያ የሰፈነውን በልዩነት ላይ ያተኮረ አስተሳሰብና በዚኸም ላይ የተመሠረተ የኃይል አሰላለፍና ሁኔታ መቀየርን ይጠይቃል።

በዚህ የሽግግር ወቅት በአገራችን ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍኑ፣ አገራዊ አንድነት እንዲጠበቅ፣ ድርጅቶች በሙሉ ነፃነት እንዲንቀሳቀሱና የፖለቲካ ሥራቸውን እንዲያስፋፉ፣ ዜጎች በዴሞክራሲያዊ መብታቸው እንዲጠቀሙና የአገሪቱ እስር ቤቶች ከፖለቲካ እስረኞች ነፃ እንዲሆኑ መደረግ ይኖርበታል።

ድርጅታችን የአገራችን ሕገ-መንግሥት የሚከተሉት መሠረታዊ አሳቦች የሕገ-መንግሥቱ የማዕዘን ድንጋዮች መሆናቸውን መቀበል ይኖርበታል የሚል እምነት አለው።

1. የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና ብሔራዊ ሉዓላዊነት ማረጋገጥ፤
2. ሕገ-መንግሥቱ ከማንኛውም ሌላ ሕግ በላይ መሆኑንና በማንኛውም የመንግሥት አካል ተፈጻሚነት እንደሚኖረው ማረጋገጥ፤
3. የሕግ የበላይነት፣ እንዲሁም ማንም ሰው በሕግ ፊት እኩል መሆኑንና በዘር፣ በጎሣ፣ በሐይማኖት፣ በፆታ ወይም በመሳሰሉ ምክንያቶች በዜጎች መካከል አድልዖ እንደማይደረግ ማረጋገጥ፤
4. በዓለም-አቀፍ ሕግ እውቅና የተሰጡ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲረጋገጡ ማድረግ፤
5. የዳኝነት ነፃነትን ማረጋገጥ፣ እንዲሁም ዳኞች በሙያቸው ብቃት ያላቸውና ከፍርሃትና ከተፅዕኖ ነጻ የሚሆኑበትን ሁኔታ ማስከበር፤
6. የመንግሥት ሥልጣን ክምችትን ለመከላከል በሕግ አውጭው፣ በሕግ አስፈጻሚውና በሕግ ተርጓሚው መኻል ሊኖሩ የሚገቡ የሥራ ድርሻዎችን በውል መለየት፣ እንዲሁም በብሔራዊው መንግሥትና ወደፊት በሰከነ ውይይትና ብሔራዊ መግባባት ተመሥርቶ በአዲስ መልክ በየአካባቢው በሚቋቋሙ የአካባቢ አስተዳደሮች መኻል ሊኖር የሚገባውን ሥልጣን በሚገባ መደልደልና እያንዳንዱ የአካባቢ አስተዳደር በአገር ደረጃ ከሚገኘው ገቢ ፍትኀዊ የሆነ ድርሻ እንደሚኖረው በሕገ-መንግሥቱ ማረጋገጥ፤
(የድርሻው መጠን እንደአካባቢው የሕዝብ ብዛት መጠንና እንደልማት አስፈላጊነቱ፣ ወዘተ.....የመሳሰሉ መመዘኛዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ይወሰናል።)

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ በሚከተሉት መሠረታዊ እምነቶች ይገዛል።

ሀ) ውድ አገራችን ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ፣ የተለያዩ እምነቶችን የሚከተሉ፣ ዜጎችና ብሔረሰቦች ያሏት ጥንታዊት፣ ነፃና አንድነቷ የማይገሰስ አንዲት ሉዓላዊት አገር ናት።

ለ) የኢትዮጵያ ሕዝብ የተለያዩ ቋንቋዎችን ቢናገርም፣ የተለያዩ ሐይማኖቶችን ቢከተልም፣ በመሠረቱ አንድ ሕዝብ ነው። ሕዝባችን በአያሌ የታሪክ፣ የባህል፣ የጅኦግራፊና የጥቅም ገመዶች የተሳሰረ፣ የወደፊት ዕድሉም እንዲሁ የተቆላለፈ ነው። ሕዝባችን ለዘመናት በኋላ-ቀር አምባ-ገነን ሥርዓቶች ለመብቶች መታፈን፣ ለድህነት፣ ለመሃይምነት፣ ለአሳፋሪ ረሃብና ችግር ተዳርጎ ኖሯል። ስለሆነም የኢትዮጵያ ሕዝብ የወደፊት ዕድል አንድ በመሆኑ የቋንቋና የሐይማኖት ልዩነትና አድልዖ የሌለበት፣ ዜጎች ሁሉ በእኩልነት የሚሳተፉበት ፍትኃዊ ሥርዓት ያስፈልጋል። ቋንቋን መሠረት ባደረገ ሁኔታ ሕዝብ እንዲከፋፈል በተደረገ አገር ላይ በሁሉም ረገድ መኖር ያለበትን የዜጎች እኩልነት ማስገኘት የሚሆን አይደለም። በዚኽ ረገድ የጎሣ ፖለቲካ በአገራችን ላይ ያስከተለው ችግር በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ይኽንን ቋንቋን መሠረት ያደረገ የግዳጅ አደረጃጀት ሕዝቡ ለመብቱ መከበር አንድ ላይ እንዳይቆም አሁን ያለው ገዥ ፓርቲ ተጠቅሞበታል።
እንደሚታወቀው ሕዝብ በጎሣ ከተከፋፈለ በመኻሉ ጥርጣሬና አለመተማመን ይበረታሉ። በዚኽ ሁኔታ ደግሞ ሰላም፣ ዴሞክራሲ፣ ልማት ወዘተ... ሊስፋፉ አይችሉም። ሕዝባችንን ማስተባበርና የአገራችንን አንድነትና ሉዓላዊነት ማስጠበቅም እንዲሁ አስቸጋሪ እንደሚሆን ግልጽ ነው።

ስለሆነም ድርጅታችን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ የጎሠኝነትን ፍልስፍና አይቀበልም። ይኽንን የሕዝብ መከፋፈያ ዘይቤም በሁሉም መልኩ ይታገለዋል።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ በአባላቱም ሆነ በአጠቃላይ በአገሪቱ ዜጎች መኻል የቋንቋ፣ የቀለም፣ የአካባቢ፣ የፆታ፣ የሐይማኖት፣ ወዘተ... ልዩነት ፈጽሞ አያደርግም፤ እንደዚህ ዓይነት ኋላ-ቀር አስተሳሰቦችንም አጥብቆ ይታገላል።

ሐ) የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ምንጭና ባለቤት ነው። ስለሆነም "አንድ ሰው አንድ ድምፅ" በሚለው መርኅ መሠረት በነፃና ፍትኃዊ ምርጫ በሚሰጠው ድምፅ የሚፈቅደውን ሥርዓትና የመንግሥት ዓይነት የማቋቋምና የመሰየም ሥልጣን የሕዝብ ብቻ ነው። በአገራችን የመንግሥት ሥልጣን መያዝ የሚሻ ቡድን ወይም ቡድኖች የሕዝብን ይሁንታና ፈቃድ ያገኘ/ያገኙ ብቻ መሆን ይኖርበታል/ይኖርባቸዋል ብሎ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ ያምናል።

መ) የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ መመሪያ ኢትዮጵያዊ አንድነት፣ ክብርና ወንድማማችነት ነው።

በአሁኑ ጊዜ ድርጅታችን የሚታገለው ለተራ የመንግሥት ለውጥ ወይም ከአንድ ፓርቲ ወደ ሌላ ፓርቲ (ፓርቲዎች ጥምር) ለሚደረግ የሥልጣን ዝውውር ሳይሆን፣ ሕዝባችን የሙሉ ሥልጣኑ ባለቤት ለሚሆንበትና መሠረታዊ የሆኑና ሥር የሰደዱ የአገራችን ችግሮች ዘላቂ መፍትኄ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ለማመቻቸትና ለማስቻል ነው።

ትግላችን ስማችን እንደሚያመለክተው ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ነው። የሰከነ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ማድረግ ያልቻለ ሕዝብ ያለባቸውና የዜጎች ሁለንተናዊ መብቶች የታፈኑባቸው እንደ ኢትዮጵያ ብዙ ብሔር/ብሔረሰቦች ያሉባቸው አገሮች ላይ አንድነትም ሆነ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአንድ ወይም በተወሰኑ ቡድኖችና ድርጅቶች ፍላጎትና ጥረት ብቻ በአስተማማኝ ሁኔታ ማስገኘት እንደማይቻል ጠንቅቀን እናውቃለን።

ስለሆነም ነው ድርጅታችን ለሁል-አቀፍ ችግሮቻችን ሁል-አቀፍ ምላሽ ለመስጠት ለሕዝብና ለአገር የሚያስብ ሁሉ በአዲስ የአስተሳሰብ ለውጥ ላይ ተመሥርቶ የጋራ መፍትኄ ፍለጋው ላይ ማተኮርና መረባረብ ያስፈልጋል በሚል እምነት በንቅናቄነት የተደራጀው::

## IV. የአገራችን መሠረታዊ ችግሮች፤

የአገራችንን የፖለቲካ ችግሮች ቋሚ ሆነው ከቆዩ አምስት ገጽታዎች አንፃር ማውሳት ይቻላል:: እነሱም:-

ሀ) የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ሁሉ ምንጭ መሆኑ በተግባር ባለመረጋገጡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመንግሥት ሥልጣን ባለቤት መሆን አለመቻል ወይም ይኸንን መሠረታዊ መብት መነጠቅ፤

ይኸ ችግር የችግሮቻችን ሁሉ መንስዔ ነው:: ሕዝቡ በአገሩ መሠረታዊ ጉዳዮችና አንገብጋቢ ጥያቄዎች፣ በሚመራበት ሕገ-መንግሥት ይሁን በአስተዳደሩና በአመራሩ ጭምር፣ ውሳኔ የመስጠት መብት የለውም:: መሬት በማን እጅ ይሁን፣ በመንግሥት ወይስ በሕዝብ? የአገር ዳር ድንበር ይጠበቅ ወይስ በባዕዳን ሸንጎ ይወሰን? የሰላምንና የጦርነትን መሠረታዊ ጥያቄዎች ማን ይወስን? እነዚህን በመሳሰሉ ከፍተኛ ጉዳዮች ላይ እንኳ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ለመስጠትና ለመወሰን ሥልጣኑን ተነፍጎ በመቆየቱ ለዝንታለም የሰብአዊ መብት መረገጥና ለፍትኅ መጓደል ተዳርጎ ይገኛል::

በታሪካዊው የግንቦት ሰባት ዘጠና-ሰባት አጠቃላይ ምርጫ ገዥው ፓርቲ ሕወሓት/ ኢሕአዴግ በምርጫ ቢቸነፍም የሕዝብን ውሳኔ ተቀብሎና አክብሮ ሥልጣን በሰላም ላያስረክብ ይችላል የሚል ጥርጣሬውንና ስጋቱን እየገለጸም ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር-እስከ-ዳር ተንቀሳቅሶ በገዥው ላይ ብቻ ሳይሆን የቆየ የአምባ-ገነኖች በአመፅ ላይ የተመሠረተ የሥልጣን መነጣጠቅን አዙሪት በመስበር በእርግጥም የሥልጣኑ ምንጭ እንደሆነ አረጋግጧል:: ሆኖም ድል ድል የሚሆነው የተገኘው ድል ሲከበር ብቻ በመሆኑና የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ድሎቹን ሊያስጠብቅና ሊያስከብር የሚችልባቸው ድርጅታዊና መዋቅራዊ ዋስትናዎች ስላልነበሩት፤ እነሆ በአገራችን ረጅም ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የአምባ-ገነኖች የአገዛዝ ሥርዓቶች አዙሪት ተሰብሮ፣ ሕዝቡ በነፃ ድምፁ በመረጣቸው አስተዳዳሪዎቹ ብቻ እንዲተዳደርና ሁሉም (ተቃዋሚውም ሆነ ገዥው ፓርቲ) አትራፊና ተጠቃሚ ሊሆንበት የሚችል ሥርዓት መሠረት እንዲጣልና ሥር እንዲሰድ የሚያስችል መልካምና መሰል የሌለው አጋጣሚ በአጭር እንዲቀጭና እንዲቀለበስ መደረጉ ሁሉም በቁጭት የሚመለከተው ጉዳይ ነው::

ለ) የገዥዎች ተጠያቂነት አልባ መሆን፤

ሕዝቡ ብቸኛ የሥልጣን ምንጭ መሆኑ ባለመረጋገጡና እራሳቸውን በሥልጣን ላይ ጉብ የሚያደርጉት ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች ያለ ሕዝብ ይሁንታና ፈቃድ በመሆኑ በአገራችን መንግሥት የፈቀደውን ሁሉ ሲያደርግ የሚፈራው ቅጣት የለም:: ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሰፈነበት ሁኔታ ስህተት የፈጸመ ወይም በሥልጣን የባለገ መንግሥት ምርጫ ተደርጎ በሌላ ይተካል:: በኛ አገር ግን መንግሥት ግዛትን ያኸል ነገር ቆርጦ ለባዕድ ቢሰጥ ወይም ቢሸጥ እንኳ ጠያቂ የለውም:: በሥልጣን የባለጉና ወንጀል የሰሩ ባለሥልጣኖች በሥልጣን ላይ ሳሉ ሕዝብን የመበደልና የማሰቃየታቸው ጊዜ ሲያከትም የሕዝቡን ንብረት ዘርፈው ወደ ባዕድ አገር ይኮበልላሉ::

ሌላው ቢቀር በአሁኑ የቅርብ ታሪካችን የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ በታኅሣስ ወር ዘጠና-ስድስት ዓ/ም ጋምቤላ ውስጥ በአኙዋክ ዜጎቻችን ላይ፣ የግንቦት ሰባት ዘጠና-ሰባት ምርጫ ዙሪያ በተከሰተው የፖለቲካ ችግር በአዲስ አበባና በሌሎች ቦታዎች ሰላማዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ ድምፃቸው እንዲከበር በጠየቁ ዜጎች ላይ፣ ወዘተ… የንፁኀን ኢትዮጵያውያንን ደም ባፈሰሱ የመንግሥት ታጣቂዎች ላይ አንዳችም ተአማኒነት ያለው እርምጃ አለመወሰዱ፤ አሁን በሱዳን ድንበር በኩል እንደሚታየው የአገርን ድንበር ያኽል ነገር ሕዝብ በይፋ አውቆት፣ መክሮበትና በግልጽ ተወያይቶበት ሳይሆን በድብቅ በሚደረግ ዝግ ድርድር ለባዕድ አሳልፎ መስጠት፣ ወዘተ… እዚኽ ላይ በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ሐ) <u>የመሪዎች ከሕግ በላይ መሆን፤</u>

በታሪክ አጋጣሚ ሥልጣን ላይ የሚወጡ መሪዎች ከሕግ በላይ ለመሆን ያላቸው ዝንባሌና የመንግሥት ሥልጣንም ያለገደብ በአንድ ማዕከል ዙሪያ ወይም በአንድ ግለሰብ እጅ እንዲከማች የማድረግ ልማድ ሌላው ችግር ነው።

ይኽ የቆየ በሽታ አሁን በሥልጣን ላይ ያሉ ባለሥልጣኖችንም በጠና የተጠናዎታቸው መሆኑ አያጠያይቅም። በአገራችን እስካሁን የሚታየው በመንግሥት ብቻ ሳይሆን በብዙ ድርጅቶች ሳይቀር የሚንፀባረቀው ይኸው ሥልጣን ያለ ምንም ገደብ በአንድ ሰው እጅ ላይ ሲከማች ነው። ከታች የመንግሥት ክፍል እስከ ከፍተኛው የመንግሥት አካል ድረስ በኃላፊነት የሚቀመጡ ሰዎች ለሚወስዱት የጥፋት እርምጃ በሕግ ፊት ትርጉም ያለው ተጠያቂነት አይኖራቸውም። እራሳቸውን ከሕግ በላይ አድርገው ስለሚቆጥሩም እራሳቸው ለሚደነግጉት ሕግ እንኳ ሳይቀር እነሱ ተገዥ አይደሉም። በሚያደርጉትም ሁሉ በሕግ እንጠየቃለን የሚል ስጋት ስለሌላቸው በዜጎችና በአገር ላይ በበደል ላይ በደል ከመፈጸም አይቆጠቡም።
"ሥልጣን ሰውን ወደ ብልግናና ሙስና ይመራል፣ ፍጹም ሥልጣን ደግሞ ይበልጥ አሞሳኝና አባላጊ ነው" እንዲሉ ሥልጣን ሙሉ በሙሉ በአንድ ግለ-ሰብ እጅ ብቻ ሲሆን ደግሞ የሚያስከትለው ውድቀትን ብቻ ነው። የዚኽ ዓይነቱ ሁኔታ የሚያመጣው አደጋና ጠንቅ ይታወቃል። ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት ያልሆነባቸው ኅብረተሰቦች ለዚኽ አደጋ ይበልጥ የተጋለጡ ናቸው።

መ) <u>ተፎካካሪ የተቃዋሚ ድርጅቶች እንደልባቸው የሚንቀሳቀሱበት የፖለቲካ መድረክ አለመኖር ወይም ዝግ መሆን፤</u>

በአንድ አገር ላይ ይኽ ሁኔታ ሲከሰት <u>ጠያቂ የሌለበት አምባ-ገነናዊ አገዛዝን የግድ ይፈጥራል።</u> በአኳያው ተቃዋሚ ድርጅቶች በስመ ተቃዋሚነት ብቻ መኖራቸው የሕዝቡን የለውጥ ጥማት ለማርካትም ሆነ ለጥያቄዎቹ ምላሽ ሊያስገኙ አይችሉም። እንዲያውም የእንቅስቃሴአቸውና የኅልውናቸው ዋነኛ ባለቤት ቆመንለታል የሚሉት ዓላማም ይሁን ሕዝቡ ሳይሆን ገዥው ክፍል ስለሚሆን አገልግሎታቸው ለሕዝብ ሳይሆን ሥልጣን ላይ ላለው ቡድን ይሆናል። እራሳቸው ድርጅታዊ ነፃነት የሌላቸውና ኅልውናቸው በገዥው ክፍል በጎ ፈቃድ ላይ ብቻ የተመሠረተ ስለሆነ ለአገርና ለወገን ጠንክረው ለመቆም አይችሉም። እንዲሁም ከመንግሥት ወይም የመንግሥት ሥልጣን ከያዘው ክፍል ቁጥጥር ውጭ የሆኑ ተቃዋሚ ክፍሎች ቢኖሩ የእነኝህ ወገኖች ድርጅታዊ ጥንካሬ መጠነኛ ከሆነ የተዛባውን የፖለቲካ ሁኔታ ወደ ተሻለ ጎዳና ለማቃናት አይቻላቸውም። ከዚህም የተነሳ ለጊዜው በሥልጣን ላይ ያለን ፓርቲ (ኃይል) ከሚከተለው አምባ-ገነናዊ አሠራር እንዲታቀብ፣ ሕዝብን እንዲያዳምጥና የሕዝብን ፍላጎት እንዲያከብርም ሆነ የተቃዋሚውን ኃይል አክብሮ ትርጉም ወዳለው ውይይትና ድርድር ዓይኑን እንዲመልስ ለማድረግ ፈጽሞ አይችሉም።

ለሕዝብ ድምፅ የሚሆኑና ብሶቱን በትጋት የሚያስተጋቡ እንዲሁም እራሳቸውም የተጠያቂነት መንፈስን የተላበሱ የተቃዋሚ ድርጅቶች መኖር ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አስፈላጊ ነው:: ለአንድ አገር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሥር መስደድ ተለጣፊ፣ አጃቢና ጋሻ-ጃግሬ የሚሆን፣ ከአሁን በፊት አንድ የኢሕአዴግ ባለሥልጣን እንዳሉት "ገዥው ፓርቲ እራሱን የሚያይበት መስታዎት" ሆኖ የሚያገለግል 'ተቃዋሚ' ሳይሆን የሚያስፈልገው፣ በውስጣቸው ዴሞክራሲያዊ አሠራርን በተግባር የሚያሳዩና የሚከተሉ፣ የአገርንና የሕዝብን ጥቅም በሚያስቀድሙና ለጎሊናቸው ተገዥ በሆኑ መሪዎች የሚመሩ ሁነኛና እርባና ያላቸው ተቃዋሚዎች ሊኖሩ፣ ሊበረታቱና ሊደገፉ ይገባል::

ሠ) <u>የተቃዋሚው ክፍል ጠንካራ አንድነት አለመኖር</u> ፤

በአገራችን መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፉ ድርጅቶች የጋራ ትግላቸውን ለማስተባበር ብዙ የጋራ መድረኮችን አቋቁመዋል:: ኢዴኃቅ፣ ፓሪስ አንድ፣ አማራጭ ኃይሎች፣ ኢተፖድኅ (ፓሪስ ሁለት)፣ ኢዴኃኅ፣ ቅንጅት በሚል ጥረቶች ተደርገዋል:: አሁንም ኅብረቱ (ኢዴኃኅ)ና ሌሎችም በዚሁ መንፈስ የጋራ ጥረት ከማድረግ እንዳልተቆጠቡ ይታወቃል:: የተቃዋሚው ክፍል አንድ ሆኖ እስካልቆመ ድረስና በጋራ የአገር-አድንና የአስተባቆ-ሕዝብ የለውጥ አጀንዳ እስካልተንቀሳቀሰ ድረስ የአገሪቱን ሁኔታ መቀየር ያስቸግራል:: ይልቁንም የድርጅቶች አንድ አለመሆን ብቻ ሳይሆን በሚያሳዝን መልኩ በሚያግባቡ ዋና ዋና የጋራ አገራዊ ጉዳዮች ላይ እንኳን ተቀራርቦ መሥራት አለመቻል እንዲሁም የድርጅት መብዛት ተደራራቢ ችግሮችን አስከትሏል::

የመጠፋፋት አዙሪት አክትሞ፣ በእውነተኛ እርቅና ሰላም ላይ የተመሠረተ የሰከነ ሽግግር በማድረግ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአገራችን ላይ እውን እንዲሆን ከተፈለገ የተቃዋሚው ክፍል የውጭ - የውስጥ፣ አዲስ - የቆየ፣ የአንድነት ኃይል - ብሔረተኛ፣ እውነተኛ ተቃዋሚ - ተለጣፊ፣ ወዘተ.... በሚል ልዩ ልዩ ፍረጃ እራሱን መከፋፈልና የሽንፈት ፖለቲካን መከተል ማቆም የግድ ይሆናል:: በዚኸ የተቃዋሚው የተዘበራረቀ ይዞታ አቸናፊና ተቸናፊ የግድ የሚኖርበትና የጋራ ጠቀሜታ የማይገኝበት "ዞሮ ዞሮ ድምሩ ዜሮ" ሁኔታን ከመፍጠር የተለየ ውጤት ማምጣት አይቻልም:: ስለሆነም ጠንካራ፣ ተደማጭነትና ተአማኒት ያለው እንቅስቃሴ በማድረግ ሁሉም አትራፊ ሊሆንበት የሚችል የሁሉም ዜጎች እኩልነት የሚረጋገጥበት አዎንታዊ ለውጥ ለማስገኘት በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፉ ኃይሎች በኢትዮጵያ አገራዊ ማእቀብ ውስጥ ተከባብረው በጋራ ለመሥራት መቻል ይኖርባቸዋል:: ይኸ ሲሆን ብቻ ነው ትርጉም ያለውና አስገዳጅነት ያለው ድርድር ማድረግም ሆነ ሁሉን-አቀፍና አግላይነት የሌለው ለውጥ ማምጣት የሚቻለው::

ከአፄ ኃይለ-ሥላሴ ጊዜ ጀምሮ የሚታገለውም ይሁን ከደርግ ዘመን ጀምሮ ያለው እንዲሁም ባለፉት አሥራ-ሰባት ዓመታት ውስጥ በልዩ ልዩ ጊዜና መልክ ተደራጅቶ የሚታገለው ክፍል አመለካከቱን ከየድርጅቱ "ጥቅም" አንፃር ብቻ በተቃኘ ቀጭን የብቸኛ መሥመር ከመጓዝና 'እኔ ብቻ ነኝ ልክ፣ ከኔ ወዲያ ታጋይ ላሳር ' ከሚል የዞረበት አጉል አስተሳሰብ ተነስቶ ከመናናቅና አንድ ላይ የተሻለ መሠራት የሚችለውን ሁሉም በየፊናው በተበተነ መልክ ከሚኳትን ይልቅ ሁኔታዎችን የጋራ ከሆነችው አገራችን ዘለቄታዊ ጥቅም አንፃር በማየት ተከባብሮና ተባብሮ በጋራ መሥራቱ አንፃራዊ በሆነ መልኩ አጠር ባለ ጊዜ ውስጥ የተሻለ ውጤት እንደሚያስገኝ ሊታወቅ ይገባል:: ረዘም ላለ ጊዜ በትግሉ የቆየውና ሕይዎቱን ሙሉ የሰጠው ክፍልም በእምነቱ ጥናት ሊከበር ይገባዋል እንጂ እንደ አሮጌ ቁና ተወርወር ሊባል አይገባውም:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጀምሮ የተሰለፈውም ሆነ ገና ወደፊት የሚሰለፈውም ጭምር ለሕዝብና ለአገር ዓላማዎች መቆሙ ሊያስመሰግነውና እሰየው ሊያሰኘው እንጂ ለምን ቀደም ብለህ ከእኔ እኩል አልጀመርክም ሊባልና እንደ "መጤ" ሊቆጠር ከቶ አይገባም:: ስለዚህ ቀደም ሲል የጀመረውም አንፃራዊ "አዲስነት" ያለውን ዝቅ አድርጎ ማየት፣ በቅርቡ የተሰለፈውም ቀደም ሲል የነበረውን "ጊዜህ አልፎብሃል" ማለት፣ በአገር ውስጥ ሕጋዊ ሆኖ የሚንቀሳቀስው በውጭ ያለውን ወይም ለጊዜው በሁኔታዎች

አስገዳጅነት “ሕጋዊ” መሆን ያልቻለውን “ከሕዝብ የተለየ” አድርጎ ማየትና እኔን ብቻ ተከተሉኝ፣ “ስንቅ ብቻ አቀብሉኝ” ማለት፣ እንደገናም በሁኔታዎች አስገዳጅነትና በልዩ ልዩ ምክንያቶች ለጊዜው ልዩ ልዩ የትግል ስልት መከተል የተገደዱትን ወይም የመረጡት ድርጅቶችን የኔን መሥመር ካልተከተላችሁ በማለት በጠላትነት በመፈረጃጀት በእርስ-በርስ አጉል ሽኩቻ ጊዜንና አቅምን ከማባከንና የወደፊት ትብብርን በር ከመዝጋት ይልቅ አብሮ መሥራት እንዲቻል ሁኔታውን “ምቹ” ለማድረግ ሙከራ እየተደረገ ቢያንስ ሁሉም በመረጠው መንገድ መቀጠል እንደሚቻል አለመረዳት ትልቁን አገራዊ ሥዕል የሳተና የጋራ ጠቀሜታ የሌለው አመለካከት መሆኑን ሁሉም ሊገነዘበው ይገባል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ የአገሪቱ አሳሳቢ ሁኔታ አስፈላጊ የሆነው የጋራ እርብርብ ተደርጎበትም እንኳ ቀላል እንዳልሆነ ይገነዘቧል፡፡ ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ ላይ ለውጥ እንዲመጣ የሚፈልግና የሚታገል ሁሉ ትግሉን አንድ ላይ ማስተባበርና በአንድ የጋራ መሥመር ማቀናጀት እስኪቻል ድረስ ሁሉም እርስ በርስ መናቆሩን በመተው በየተሰለፈበት ሆኖ ሊናበብ ይገባል፡፡

ከዚኽ በላይ በአጭሩ የዘረዘርናቸውን በአገራችን የሰፈኑ መሠረታዊ የፖለቲካ ችግሮቻችንን በጥሞና መመርመርና የጋራ መፍትኄ መሻት አማራጭ የሌለውና ሁሉም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው ብለን እናምናለን፡፡ ስለሆነም በአገራችን ላይ ያንዣበቡ ችግሮችን ለማስወገድና ሕዝባችንን ዘላቂነት ወዳለው ሰላምና መረጋጋት ማሸጋገር ይቻል ዘንድ በገዥው ፓርቲ በኩልም ሆነ በተቃዋሚው ዘንድ የአንዱ መኖር የግድ በሌላው መቃብር ላይ መመሥረት እንደማይኖርበት ከልብ ተረድተው፣ እንደ አንዲት አገር ዜጎች በመቻቻልና በመከባበር ያለውን አሳሳቢ ሁኔታና የሕዝባችንን መስዋዕትነት የሚመጥን አዲስ አስተሳሰብና አሰላላፍ ለመከተል ድፍረቱ እንዲኖራቸው የማያቋርጥ ምኞታችና ጥሪያችን ነው፡፡ ይኸንን ታሪካዊ ተልእኮ መወጣት አለመቻል ተያይዞ መጠፋፋትን እንደመጋበዝ እንደሚቆጠር በፖለቲካው መድረክ ያለው ወገን ሁሉ ይስተዋል ብለን አንገምትም፡፡ ትግሉ ለቀደመው ትውልድም ሆነ ላለፈው ጊዜ ሳይሆን ለመጭ ትውልድና ትውልዶች እንዲሁም ለወደፊቱ የጋራ እጣ ነውና በተቃዋሚው ወገንም ሆነ በገዥው ክፍል በኩል በአገር ስም እየተማለ አንዱ ሌላውን በመረረ ጥላቻ ማየቱ በአዲስ የአስተሳሰብ ለውጥ እስካልተቀየረና በሁለቱም በኩል እንደ አንዲት አገር ዜጎች ተቻችሎ በልዩነት መኖርን እስካልተቀበሉ ድረስ ትርፉ የጋራ መጠፋፋትን ማረጋገጥ ወይም ለዚኽ ሂደት ብቻ መሥራት እንደሆነ፣ ይኽ ደግሞ ሁሉም ከኔ ወዲያ ለሚልላት አገርም ሆነ ቆምኩለት ለሚለው ሕዝብ ምንም ጠቀሜታ እንደማይኖረው ሊታወቅ ይገባል፡፡ የዚኽን ዓይነት በልዩነት ተቻችሎ የመኖር አባባልን ምናልባት አንዳንድ ወገኖች “እንዴት ከጠላት ጋር ተቻቻሉ ይባላል?” ሊሉና አለፍ ብለውም የዚኽን ዓይነት አስተሳሰብ ማስተናገድ እንዲያውም ለገዥው ፓርቲ “ማጎብደድና ዕድሜ መለመን ነው” ሊሉ የሚቃጣቸው አይጠፉም፡፡ ለነገሩ እርቅና ሰላም መደረግ የሚኖርበትና በልዩነት ተቻችሎ መኖር የሚያስፈልገው ወዳጅ ወዳጅ ነውና ከወዳጅ ጋር ሳይሆን በባላንጣነትም ይሁን በጠላትነት ከሚፈረጅ ጋር መሆኑን ያጤኗል፡፡ *

በተለይም ወደ አርባ ዓመታት ለሚሆን ጊዜ ተማሪው ትምሕርቱን፣ ሠራተኛው ሥራውን በመተውና ቤተሰቡን በትኖ ለመልካም ሥርዓት ግንባታ፣ ለእኩልነትና ለፍትኅ ለመታገል ውሳኔ ያደረገውና ቁርጠኝነቱን በተግባር ያሳየው ወገን የአሁኑ የአገራችን ሁኔታ ወደ አጉል አቅጣጫ እንዳይሄድ የማስቆምና ለተተኪው ትውልድ የተመቻቸ ሁኔታን የመፍጠርና አስረክቦ የማለፍ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ችሎታውም አለው፡፡ ቀጣዩ ትውልድ ያለፈውና እያለፈ ያለው ትውልድ ባለፈበት ጠመዝማዛ የችግር ሂደት እንዲጓዝ ወይም ተመሳሳይ የመከራ ገፈት ቀማሽ እንዲሆን እስካልፈለግን ድረስ ትግሉን በተደራጀ መልክ የሞከረውና መስዋዕት የሆነው ያ ታጋይ ትውልድ ቢያንስ ለተተኪው ትውልድ ሁኔታውን አዘበራርቆ መተው አይኖርበትም፡፡ ታሪካዊ ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን በታሪክ ተጠያቂ መሆንም

** (በአንዳንድ የተቃዋሚው ክፍል ወገኖች በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሲያወያይ በሚሰማው “ጠላት፣ ወዳጅ” የሚል ቀጭን አፈረጃጀት ዙሪያ ድርጅታችን ያለውን አስተሳሰብ በሌላ ጊዜ እንመለስበታለን፡፡)*

እንዳለ ልብ ይሏል፡፡ የወደፊቱን ባዬ መልኩ አቸናፊና ተቸናፊ በሌለበት ሁኔታ ሁሉም ተጠቃሚ የሚሆንበት ሥርዓት እውን እንዲሆን ከተፈለገ ያለፈው ታሪካችን በመጥፎውም ሆነ በበጎው በሁለንተናዊ መልኩ የጋራችን መሆኑን መቀበል ያስፈልጋል፡፡

አሁን በአገራችን ላለው አስቸጋሪና ፈታኝ ሁኔታ አንድን ወገን ተጠያቂና ብቸኛ ኃላፊ አድርጎ መውሰዱ ብዙ እሩቅ አይወስድም፣ የወል ኃላፊነትንና የግል ተጠያቂነትን የሚገድፍም ስለሆነም የጋራ ጥቅምን የሚያስጠብቅ ውጤት አይኖረውም፡፡

## V. ምን መደረግ አለበት?

ከዚኽ በላይ በአጭሩ ለመዳሰስ እንደተሞከረው የአገራችንን አንድነት በጠና የሚፈታተንና የሚከፋፍል፣ ሕዝባችንን ወደ አሰቃቂ ትርምስ የሚያስገባ አደገኛ ሁኔታ አፍጥጦ ከፊታችን ተደቅኗል፡፡ በአንፃሩ አገሪቱ የምትገኘው በራሱ ሕዝብ መብቶች ላይ በልዩ ልዩ መልክ በዘመተ፣ ከሥልጣኑና ሥልጣኑ ከሚያስገኛቸው ጥቅማ-ጥቅሞች ውጭ ስለ አገር አንድነትም ሆነ ስለ ብሔራዊ ክብርና የሕዝብ ልዕልና ብዙም የማይጨነቅ በሚመስለው ብቻ ሳይሆን እንዲያውም ፈጽሞ ደንታ-ቢስ የሚያሰኝ አቋምን በሚያራምደው የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ሥር ነው፡፡

የአገራችን የቅርብ ጊዜ ታሪክ እንደሚመሰክረው ሕዝባችን ለእድገትና ለብልጽግና እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆኑት የውስጥ ሰላምንና መረጋጋትን ለአንድ ትውልድ እንኳ የዘለቀ ጊዜ አግኝቶ አያውቅም፡፡ ከውጭ መስሪ ወራሪዎችና እብሪተኛ ተስፋፊዎች ጋር ከተደረጉ ጦርነቶች በተጨማሪ በውስጥ የተካሄደው ለረዥም ጊዜ የቀጠለ የርስ-በርስ ግጭት ሲደማመር የአገራችን ታሪክ የጦርነትና የፍልሚያ ታሪክ ነው ብሎ መናገር ያስደፍራል፡፡ በመሆኑም ሕዝባችን እፎይታን አግኝቶ ድህነትንና መሃይምነትን ለመዋጋት ሁኔታዎችና አቅሙ አልፈቀዱለትም፡፡ አንፃራዊ ሰላም ሲኖርም በእርቅና ሰላም ላይ የተመሠረተ ሳይሆን አቸናፊዎች በተቸናፊዎች ላይ የሚጭኑት ሰላም ስለሚሆን "በለስ የቀናው" ጉልበተኛ ብቻ እንዳሻው የሕዝብ ዕድል ወሳኝ የሚሆንበትና ውስጣዊ ሰላም ለሕዝባችን የሩቅ ህልም እየሆነበት፣ ዙሪያ ጥምጥም ችግሮች እየተባባሱና ውጥረት በየደረጃውና በየጊዜው እያገረሸ የሚቀጥልበት የአፈና፣ የችግርና የመከራ አዙሪት እነሆ ሳያባራ ቀጥሏል፡፡

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና ብዙ ለአዎንታዊ ለውጥ የቆሙ ኃይሎች ለአገራችን የተሻለ ሥርዓትን ለማስገኘት በልዩ ልዩ መልክና መንገድ የረዥም ጊዜ ያልተቋረጠ ትግል አካሂደዋል፡፡ በማድረግም ላይ ናቸው፡፡ ሕዝባችን ያለማቋረጥ የሥልጣኑና የመብቱ ምንጭና ባለቤት ለመሆን ያለው ይኽ የሰረፀ የሰላማዊ ለውጥ ፍላጎት፣ ቁርጠኝነትና ተጋድሎ የግንቦት ሰባት ዘጠና-ሰባትን ምርጫ ሂደትንና ውጤትን ወልዷል፡፡ ግንቦት ዘጠና-ሰባት ሕዝብ ለዘመናት የታገለለትን፣ እየታገለለት ያለውንና ወደፊትም የሚታገልለትን የጋለ የለውጥ ፍላጎቱን በውን የገለጠበት ከፍተኛ ደረጃ የሚሰጠው ታሪካዊ ክስተት ነበር፡፡

ጠንካራና የተባበረ ተቃዋሚ የሌለበት አገር በሥልጣን ላይ ያለ ፓርቲ (ፓርቲዎች) ለሕዝብና ለአገር የሚጠቅሙ መርኃ-እቅዶችን (ፖሊሲዎችን) እንዲከተል ለማስገደድ አለመቻል ብቻ ሳይሆን ለአምባ-ገነኖች ማቆጥቆጥና ተደላድሎ መቀጠል ቀጥተኛ የሆነ አስተዋጽዖ ያደርጋሉ፡፡ ለዚኽም ነው ማንኛውም ለአገርና ለሕዝብ የበለጠ ኃላፊነት የሚሰማው ድርጅትም ሆነ መሪ ሥልጣን በሚይዝበት ጊዜ ለሕዝብ የተሻለ አማራጭ በማቅረብም ይሁን ሥልጣን የያዘው ክፍል የሚሠራቸውን ስህተቶችና ግድፈቶች ያለ ምንም ስጋትና ፍራቻ በሕዝብ ፊት በማጋለጥ እንደልጓም ፈር የሚያስይዝ ተቃዋሚ መኖር የሚኖርበትና የሚያስፈልገው፡፡ እዚኽ ላይ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባው ጉዳይ እውነተኛ ተቃዋሚ የሚኖረውና በትክክል የተቃዋሚ ሚናን መጫዎት የሚቻለው ሕዝብን ማዕከል

**ባደረገ ትግል በሚፈጠር የሚያሠራ የፖለቲካ ሁኔታ እንጂ ሥልጣን የያዘው ክፍል በሚሰጠው ችሮታ ወይም ፈቃድ እንዳልሆነ ነው። ዴሞክራሲ ከአምባ-ገነኖች አይፈልቅም።**

በአሁኑ የአገሪቱ ሁኔታ ትክክለኛ ሕጋዊ ትግል ማድረግ አስቸጋሪ በመሆኑና ሁኔታዎች በእጅጉ እየተጣበቡ በመምጣታቸው ሕዝባችን ከሕጋዊ ብቻ ሳይሆን ከሰላማዊ ትግሉ ውጭ የሆኑ የመታገያ ስልቶችን እንዲከተል ወደ መገደዱ እየሄደ ነው ማለት ይቻላል። ችግሩ እንግዲህ አሁን አገራችን ካለችበት ቀውስን ያረገዘ ውጥረትና ከሚያንዣብብ የአገራዊ ኅልውና ማጣት አደጋ አንፃር የዚኽ ዓይነቱ ሁኔታ ከቀጠለና በአንድ በኩል ሕዝብ ወደደም ጠላም ሥልጣንን በይገባኛል ስሜት በብቸኝነት ሙጭጭ አድርጎ በያዘው ገዥ ፓርቲ ሕወሓት/ኢሕአዴግና በሌላ በኩል በተሰበጣጠረና በተበጣጠሰ መልክ በሚንቀሳቀሰው ተቃዋሚው መኻል ያለው ያልተገናኝቶም ትግል አሁን ካለበት በበለጠ ወደ መዛሪያ ፍልሚያ ከተሸጋገረ በጥብቅ መታየት ያለበትና ማንኛውንም ኃላፊነት የሚሰማው አገር-ወዳድ ኢትዮጵያዊ ከወዲሁ ሊያስብበትና ተገቢና ግልፅ መልስ መፈለግና መስጠት የሚገባው ዓቢይ ጉዳይ አለ። ይኸውም በዚኽ በሁሉም አቅጣጫ በሚደረግ የውጥረት ሂደትና በአለው ዓለም-አቀፍ ይዘት ያለው ውጥንቅጡ የወጣ የአካባቢና የውስጥ የተወሳሰበ ሁኔታ ማዕከላዊ መንግሥት ቁጥጥሩን ቢያጣ ቀጣዩ ምን ይሆናል? ሁሉን-አቅጣጫ-ያዬና በጥሞና ያገናዘበ ማነው? ከዚኽ አጠቃላይ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ሁሉን-አቀፍ የሆነ ዝግጅትስ አለ ወይ? ለሚለው የአገር አንድነትና የጋራ የኅልውና ጥያቄ ይሆናል።

ይኽ ቁልፍ ጥያቄ በጥልቅ ሊታሰብበት፣ በጥንቃቄ ሊታይና ምላሽ ሊሰጠው ይገባል። ድርጅታችን በተናጠልም ሆነ ከሌሎች አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች ጋር በሚያደርገው ሁሉን አቅጣጫ ባዬና ሕዝብን ማዕከል ባደረገ ሰላማዊ የለውጥ ትግል ይኽ ጉዳይ በጥንቃቄ ስሊት ውስጥ መግባት ይኖርበታል ብሎ ያምናል። በአገሪቱና በሕዝቧ ላይ ያሉ ችግሮችን አገዛዙን በምናይበት ዓይን ማየት ስህተት ይሆናል። ገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግ ኖረም አልኖረም አብዛኞቹ በአገሪቱ ላይ የተደቀኑ አደጋዎች ቀጣይ ናቸው። ለብዙዎቹ ችግሮች መፈጠርና መኖር አገዛዙ ተጠያቂ መሆኑ ግልጽ ነው። መገንዘብ የሚገባን ጉዳይ ግን የችግሮቹ ዕድሜ ችግሩን ከፈጠሩት ክፍሎች ዕድሜ እንደሚረዝም ነው። ስለሆነም በአገራችንና በሕዝባችን ላይ የተጫኑና የሚያንዣብቡ ችግሮችን እንደሌሉ መቁጠርም ሆነ ከአገዛዙ ዕድሜ ጋር ማያያዙ ብዙ ርቀት አይወስደንም። ለነኝህ ችግሮች የጋራ መፍትኄ ሊፈለግ ይገባል። <u>አሁን የሚታየው ሁሉም ነገር የአገዛዝ ሥርዓቱንና ፍልስፍናውን ሳይሆን አገዛዙንና ከአገዛዙም ነጥሎ ቁንጮዎቹ ላይ ብቻ ያነጣጠረ "ትግል" መሠረታዊ ችግሮቻችንን በቅጡ ያላገናዘበና ዘለቄታዊ መፍትኄም ማስገኘት የሚገደው አካሄድ ሆኖ እናገኘዋለን።</u> በአጭር አነጋገር በአብዛኛው የተቃዋሚ ክፍል የሚገፋው ዞሮ ዞሮ እስካሁን ባለ የጨዋታ ሕግ ተጫዋቾቹን የመቀየር አካሄድ ነው። በኛ እምነት በአዲስ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ አቀራረብ ሊኖረን ይገባል ስንል የአገራችንን ዙሪያ-ጥምጥም ችግሮች መፍታት የምንችለው <u>በአዲስ የጨዋታ ሕግ</u> ብቻ መሆኑን ለማመላከት ነው። ኢዴኅአን ለአገራችንና ለሕዝቧ የሚደረግ ትግል ከአቶ መለስ ኢሕአዴግ አሻግሮ ያየ መሆን ይኖርበታል ብሎ ያምናል። ድርጅታችን በዚኽ ረገድ አንዳንድ ርእሰ-ጉዳዮች ላይ ግልጽ የመወያያ ሰነዶችን በቅርቡ ለውይይት ያቀርባል።

አዳንዶች የዚኽን አስተሳሰብ ምንነት በደንብ ሳይመረምሩና ለተነሱና ለሚነሱ አገራዊ ጥያቄዎች ቅን ምላሽ ሳይሰጡ እንዲሁ በቁንጽልና በግልቡ ወስደው "ይኸማ አገዛዙ እንዳይወገድና እንዲያውም ዕድሜው እንዲራዘም ታስቦ የሚሰጥ ድጋፍ ነው፣ ማኅብደድ ነው...ወዘተ..." ሊሉ እንደሚከጅሉ እንገምታለን። የዚኽ ዓይነቱን ንዝንዝ የሚፈልጉ ተመፃዳቂ ክፍሎች እራሳቸውን እጅግ አግዝፎ በሚያሳይ የማጉያ መነጽር የሚያዩና ቅድሚያ የሚሰጡት አሁን በአገር ላይ ለተደቀነው አደጋና ለወደፊቱ የሁሉም ዜጎች የጋራ ዕድል ሳይሆን ለራሳቸው ብቻ የሆነ በጠባቡ የሚያስቡ ክፍሎች ናቸው። መቸም እንደዚኽ ዓይነት ስንኩል አስተሳሰብን የሚያራምዱ ወገኖች ካለፉ ስህተቶቻቸው መማር ያልቻሉ፣ ቆም ብለውም እራሳቸውን ያልመረመሩና ሕይዎት እንዳለው ፍጡር በራሳቸው ላይ ምንም

*ዓይነት ለውጥ ማድረግ ያልሞከሩ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ቆሞ የማይጠብቀው፣ በየጊዜው የሚያድገውና የሚለዋወጠው ሁኔታ ካላስተማራቸው በያዙት አቋም መቀጠል መብታቸው ነው፡፡ ሆኖም በእንደዚህ ዓይነት ቁንጽልና ወደ-ኋላ ያዬ አስተሳሰባቸው ለአገርም ሆነ ለሕዝብ የሚያደርጉት አንዳችም አዎንታዊ አስተዋጽዖ እንደማይኖር ሊገነዘቡት ይገባል፡፡*

*ያለውን የአገራችን አሳሳቢ ሁኔታ በማጤን ድርጅታችን በንቅናቄ መልክ በመደራጀቱ በአሁኑ ጊዜ ለፖለቲካ ሥልጣን እንደማይሮጥ ስንገልጽ "የፖለቲካ ድርጅት ሆኖ ለሥልጣን አይደለም የምንቀሳቀሰው ማለት የማይሆን ነው፣ ቀልዳችሁን አቁሙ" የሚል ትችት እንደሚቀርብ እናውቃለን፡፡ ይኸን የሚሉ ወገኖች ግን እንዲሁ በአጠቃላይ አንደምታ እንጂ አንድ የፖለቲካ ድርጅት መቸ፣ እንዴትና በምን ሁኔታ? ነው ለፖለቲካ ሥልጣን መሮጥ ያለበት የሚለውን ሳይጠይቁ እንደሆነ እንገምታለን፡፡ በእርግጥ ማንኛውም የፖለቲካ ስብስብ የሚደራጀውና የሚታገለው ለፖለቲካ ሥልጣን ነው፡፡* ***ቁም-ነገሩ ግን ለፖለቲካ ሥልጣን የሚያበቃ ሁኔታ አሁን በአገራችን አለ ወይ? የሚለው ይሆናል፡፡ በኛ እምነት ጉልቻ ለመቀያየር ካልሆነ በስተቀር እኛ በምናስበው ዓይነት አገራችን የሥርዓት ለውጥን በሚጠይቅ ብቻ ሳይሆን የጎልውና ፈተና ውስጥ የገባች አገር ስለሆነች ያ ሁኔታ የለም ባዮች ነን፡፡*** *አሁን በአገራችን ባለው የፖለቲካ ሁኔታ እንዴት ነው <u>አንድ ድርጅት ብቻውን</u> የፖለቲካ ሥልጣን ሊይዝ የሚችለው፤ በምርጫ? በጉልበት? በድርድር? ለሚለው ጥያቄ ሁሉም ድርጅቶች ቅን መልስ መስጠት ይኖርባቸዋል ብለን እናምናለን፡፡*

***በምርጫ*** *የሚል ወገን ካለ፤ በኢሕአዴግ አካሄድና ይዞታ እኛ በሚገባን ሕዝባችንን የሥልጣኑ ባለቤት ለማድረግ የሚያበቃ ነፃና ርቱኣዊ ምርጫ በአሁኑ ጊዜ የማይሆን ነገር ነው፡፡ ለምን እንደማይቻል ቀደም ሲል በመግቢያው ላይ ዘርዝረናል፡፡ በአጭሩ ኢሕአዴግ ከምርጫ ዘጠና-ሰባት የማይረሳ ትምሕርት ወስዷል፡፡ ሕዝቡ የሥልጣኑ ባለቤት መሆን እንደሚችል ያስመሰከረበትን ዳግም ግንቦትን የሚወልድ ሁኔታ ለመፍጠር ሌላ "የተሰላ አደጋን" መልሶ ይጋብዛል የሚል ግብዝ አመለካከት አይኖረንም፡፡ ይኸ ደግሞ በቅርቡ በተደረገ "ምርጫ" ተረጋግጧል፡፡*

***በጉልበት*** *የሚል ካለ፤ ጥያቄአችን ኢሕአዴግ የያዘውን ያኽል መሣሪያ ይዞ በአገሪቱ ላይ ሰላምና መረጋጋትን ማስገኘት ባልቻለበት ሁኔታ አንድ ድርጅት ብቻውን እንዴት በጉልበት ለሥልጣን እንደሚበቃ ብቻ ሳይሆን ኢሕአዴግ በእጅጉ የገደደውንና አሥራ-ሰባት ዓመት ሙሉ ያቃተውን ሙሉ የሕዝብ ተቀባይነትና ይሁንታ እንዴት አድርገው መጎናፀፍ እንደሚችሉ በአሳማኝ መልክ አስረዱን የሚል ይሆናል፡፡ የለም በተናጠል ሳይሆን ይኸንን ተሰባስበን ማድረግ ይቻላል የሚል ምላሽ ካለም ፈጽሞ አይቻልም የሚል አቋም ባይኖረንም፣ የምንጠይቀው ግን ለምን ዓይነት ዘለቄታዊ ዓላማና ልዕለ-ግብ? የሚል ይሆናል፡፡ በተጨማሪም አገራዊ አንድነት እንዳይናጋ ያለው ዋስትና ቢያንስ ቢያንስ የተደረገው ዝግጅት ምንድን ነው? ይኸን አመለካከት የሚገፉ ወገኖች ጥረታቸው 'ቀድደን እንስፋ' ወደሚል ግብዝ አስተሳሰብ እንዳይወስደን ስጋት አለን፡፡ በዚኸ ረገድ ሌላው ሊታሰብበት ይገባል የምንለው ጥያቄ ይኸ የጉልበት አካሄድ ልዩነትን በአመፅ የመፍታት የቆየ ልማድና ከሱም ተከትሎ የሚመጣውን የአቸናፌዎችን "ሰላም" የማስፈኝና የጠገበን ጉልበተኛ በአዲስ የተራብ ጉልበተኛ የመተካት፣ ድል አድራጊን ወደ ቤተ-መንግሥት ተቸናፊን ወደ እስርና ስደት የሚወስድ አዙሪት እንዲቀጥል አያደፋፍርም ወይ? ማለቂያውስ መቸ ነው? ይኸ እንዳይሆን ያለው ዋስትና ምንድን ነው? የሚለው ይሆናል፡፡ በኛ በኩል ማሳሰብ የምንወደው አሁን ያለው አገዛዝ በፈጠረው የምሬት ምክንያትና ከሱም ተነስተን ዘለዓለማዊነት የሌለውን አገዛዝ በምናይበት ዓይን አገራችንን እንዳናይ ነው፡፡ በተጨማሪም ወደ ጉልበትና የመሣሪያ ፍልሚያ መዞሩ ወይም ለዚኸ የመታገያ ስልት ቅድሚያ ከመስጠቱ በፊት ሕዝባችንን ከዳር-እስከ-ዳር በልዩ ልዩ መልክና ጠንካራ አደረጃጀት ማንቀሳቀስ መቻል አለመቻሉ ላይ በበቂ ታይቷል ወይ? ጥቅምና ጉዳቱስ ተመዝኗል ወይ? ከእንደዚኸ ዓይነት አሰላለፍ ተጠቃሚው ማነው? የሚሉትን በተገቢና በጥሞና መመርመሩ አስፈላጊ ይመስለናል፡፡*

***በኛ እምነት ማንኛውም የትግል ስልት፣ ምርጫም ይሁን ሌላ፣ ለሕዝባችን ዘለቄታዊነት ያለውና አስተማማኝ ውጤትን ማስገኘት የሚቻለው በአነዳደፍም ይሁን በተለይ በአፈጻጸም ደረጃ ብሔራዊ ይዘት ሲኖረው ብቻ ነው:: በተናጠል የሚደረግም ይሁን 'አትድረስብኝ አልደርስብህም፣ ለጊዜው ጎን ለጎን የጋራው ጠላት ላይ እንዝመት' በሚል ዓይነት አካሄድ የሚደረግ ትግል አገራችን እንደ አንድ አገር እንድትቀጥል የሚያደርግ ብሔራዊ መግባባትን ሊያስገኝ አይችልም::***

*አገዛዙ በሚከተላቸው የአፈናና ልዩ ልዩ አረመኔአዊ እርምጃዎችን በመመልከት አንዳንድ በተቃዋሚው ወገን የተሰለፉ ክፍሎች በአገራችን የሰላም ትግል ስላከተመለትና አገዛዙም "የሚገባው ቋንቋ" ጉልበት ብቻ ስለሆነ ትግላችን ወደ ትጥቅ ፍልሚያ መቀየር ይኖርበታል ሲሉ ይሰማል:: በኛ እምነት በአገራችን ለውጥ ለማምጣጥ ምን ዓይነት የትግል ስልት ወይም ስልቶች እንከተል ከሚለው ቀጭን የመከራከሪያ ነጥብ ላይ ጊዜ ከመጥፋቱ በፊት ዘለቄታዊነት ካለው ሰላምና መረጋጋት የሚፈልቅ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአገራችን እውን መሆን የሁላችንም ልዕለ-ግብ ነወይ? ለሚለው ጥያቄ በቅድሚያ መልስ መስጠት አግባብ ያለው ይመስለናል::*

*በድርድር የሚል ካለ፣ ምን ዓይነት ድርድር፣ ለምን ዓላማ? የሚሉ ተያያዥ ጥያቄዎች ይኖሩናል:: በዚህ ጉዳይ ላይ ያለንን አመለካከት ዘርዘር አድርገን እንመለስበታለን:: በአጭሩ ግን እኛ ድርድር ስንል **ትርጉም ያለው ድርድር** ማለታችን ነው:: ድርድር በምንልበት ጊዜ በድርጅት ወይም በግለሰብ ደረጃ በድብቅ ከሕዝብ ጀርባ ከገዥው ፓርቲ ጋር ሥልጣንን ለመጋራት ወይም ለመደላደል ስለሚደረግ ንግግርና ስምምነት ጉዳይ አይደለም:: የዚኽ ዓይነት በአገር-በቀልም ይሁን በውጭ ኃይሎች አማካይነት የሚደረግ የጓዳ ድርድር የሥልጣን ቅርምት እንጂ አስተማማኝና ዘለቄታዊነት ያለው ሰላምንና የሕዝብን ጥቅም የሚያስጠብቅ ፍትኃዊ ሥርዓትን ለማስገኘት ይችላል የሚል እምነት የለንም:: ድርድር ስንል ሕዝብ እያወቀው፣ እየመከረበትና በልዩ ልዩ መልክ ተሳትፎ የሚያደርግበት ድርድር ማለታችን ነው:: **ሕዝብ በሚመክርበትና በሚሳተፍበት ሂደት ተፈጻሚ የሚሆን ድርድር** በግለሰቦችና በድርጅቶች መኻል የሚደረግ የሥልጣን ዝውውርን ሳይሆን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እውን በማድረጉ ረገድ አስተማማኝነትና የተሻለ ዘላቂነት ይኖረዋል:: ስለሆነም በኛ እምነት ይኸ ተፈጻሚ የመሆን ዕድል የሚኖረው ደግሞ በተናጠል ድርጅት በሚደረግ ሂደትና ጥረት ሳይሆን ሁሉን-አቀፍ በሆነ መልክና በተቀናበረ ሁኔታ **ሕዝብን ማዕከል ያደረገ ትግል** ማድረግ ሲቻል ብቻ ነው::*

*በአገራችን ዘለቄታዊነት ያለውና አንፃራዊ አስተማማኝነት ያለው ለውጥ ማምጣት የሚቻለው **የዴሞክራሲ ሂደቱ** ላይ ይበልጥ ትኩረት ከተደረገ ብቻ እንደሆነ ድርጅታችን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ (ኢዴኅአን) ያምናል:: የምንፈልገው ለውጥ ምን ዓይነት ለውጥ እንደሆነ ግልጽ እስከሆነ ድረስ ስለ ምርጫም ሆነ ስለ ድርድር ያሉን አሳቦች ይኸው ሂደት በምንለው ላይ ያተኮረ ይሆናል:: ሂደት ላይ የምናተኩረው የምንፈልገውና የምንመኘው **የሥርዓት ለውጥ** አስተማማኝነት ሊመሠረትበት ስለሚገባ ነው:: ሂደቱ የሰመረ ከሆነ የሕዝቡ ድሎች በባለ ጊዜዎች ወይም ጉልበተኞች እንዲህ እንደዋዛ አይቀሙም፣ አይቀለበሱም:: ለዚህም ነው ስለ ግንቦት ዘጠና-ሰባት ምርጫም የተቃዋሚው ክፍል በዚያ ምርጫ ለመሳተፍ ሲወስን ሊይዝ የሚገባው ስሌት እንዲሁ በነጣላው ከዚያ ምርጫ ምን ያኽል የፓርላማ ወንበር አገኛለሁ? የሚል ሳይሆን ምን ያኽል ሕዝብ ማደራጀት እችላለሁ? የሚለው ላይ እንዲሆንና በተቃዋሚው ክፍል የተሰለፈው ኃይል መምጣት ይኖርበታል በሚለው ለውጥ ላይ ምን ያኽል የጠራ ግንዛቤ፣ የአስተሳሰብ አንድነትና መግባባት አለው? ለዴሞክራሲ ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት እንዲጎለብቱና የሲቪክና የሙያ ድርጅቶች ለለውጡ አብረው እንዲቆሙ ብቻ ሳይሆን አካል እንዲሆኑ ምን ያኽል ጥረት ተደርጓል? የምርጫው ውጤት በኋላ እንደታየው በገዥው ፓርቲ እንደፈለገውና ባሻው ከሕዝቡ የመነጠቅ አደጋ ቢደርስ ያለው ዝግጅትስ ምንድነው? ለሚሉት የግብ (የስትራቴጂ) ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ መስጠቱ ላይ መሆን እንደነበረበት*

ቢያንስ በኅብረቱ (ኢዴኃኅ) ዙሪያ የነበርን አንዳንድ አባል ድርጅቶች ማንሳታችን ይታወቃል፡፡ ለዚኽ ነው አሁንም በአገራችን ላይ ለውጥ ያስፈልጋል ስንል ምን ዓይነት ለውጥ? እና እንዴት? ለሚሉት ጥያቄዎች አጥጋቢና እሩቁን-ያየ መልስ መስጠት ያስፈልጋል የምንለው፡፡

እንግዲህ የኃይሎች መሰባሰብና በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ማድረግ ያስፈልጋል ስንል አሁን ባለው ሕዝብንና አገርን ባላስቀደመ መልኩ የሚደረገው የፍናጅራ ጉዞ በቀጠለበት፤ በአንድ በኩል የገዥው ፓርቲ መሪዎች የሚከተሉት በቅንነትና በእኩልነት ከተቃዋሚው ጋር ለመደራደር ፈቃደኛ አለመሆንና እምቢተኛነት እንዲሁም አንድ ፓርቲን ብቻ ያስቀደመ የብቸኛ ጉዞ ቅኝትን በሚያቀነቅንበት፣ በሌላ በኩል በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፈው ክፍል በሚያሳዝን መልኩ መተክላዊ በሆነ መልክ በመከባበር ላይ የተመሠረተ የጋራ አቋምና ይዞታ እጦት ላይ በምንገኝበት ውጥንቅጡ የወጣ የኃይሎች አሰላለፍ ይኽ እንዴት ይቻላል? የሚል ይሆናል፡፡

በኛ አመለካከት የተቃዋሚው ክፍል በተለይም የአንድነት ኃይሉ ከሁሉ በፊት የሚፈልገውን ስትራቴጂያዊ ግብ ጠንቅቆ ማወቅና ቅደም ተከተሉን ማስተካከል አለበት ብለን እናምናለን፡፡ በድርጅቶች መኻል ብቻ ሳይሆን በተናጠል ድርጅቶች ውስጥ ሳይቀር አሁን የሚታየው ቅጥ ያጣና የሚያሳዝን ፍትጊያና ሽኩቻ እንኳን የሚታገሉላቸውን የሕዝብና የአገር ዓላማዎች እራሳቸውን ድርጅቶቹንና ቡድኖቹን ይጠቅማል የሚል እምነት የለንም፡፡ አሁን የሚታየው በድርጅቶች መኻል ያለው ፉክክር መሥመሩን ስቷል ባዮች ነን፡፡ በአሁኑ ጊዜ ድርጅቶች እንኳን በቡድን እርስ በርስ የሚያፎካክራቸው ጉዳይ ሊገባን አይችልም፡፡ ወቅቱ "አሁን ትብብር፣ ነገ ውድድር" እንዲሉ የመተባበሪያ እንጂ የመፎካከሪያ እንዳልሆነ በተገቢ ሊጤን ይገባል፡፡

በኛ እምነት አገርና ሕዝብን እንታደግ ካልን መዋጎድ እንኳ ባይቻል እያንዳንዱ ድርጅት የየራሱን ፕሮግራም ይዞ እታገልለታለሁ በሚለው ሕዝብ ፊት መወዳደር የሚችልበት ሁኔታ እስከሚፈጠርና እንዲፈጠር የየግል አጀንዳችንን በይደር ይዘን ጠንከር ባሉ የትግል ጥምረቶችና ቢያንስ መተክላዊ የሆኑ ስብስቦች ዙሪያ መደራጀት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ተቃዋሚው አሁን ከሚከተለው የሽንፈት ፖለቲካ ብለን ከምንጠራው እርባና-የለሽ፣ የተሟዘዘና የጋራ ኃላፊነት ስሜት ያጠረው ይዞታ በአስቸኳይ መላቀቅ ይኖርበታል፡፡

አሁን ያለው ፈታኝ ሁኔታ በአስቸኳይና ሁሉን-አቀፍ በሆነ መልክ ታይቶ በጋራ ጥረት እንዲከስም ካልተደረገ በአገራችንና በሕዝባችን ላይ የተከሰተው የችግር ክምርና የሚያንዣብበው አደጋ በፀፀት የሚመለስ አይሆንም፡፡ ይኽን ያንዣበበ የትርምስ ዳመና የጥፋት ዶፍ ከማዝነቡ በፊት እንዲበተንና አደጋው እንዲከስም ማድረግ የሁሉም ኃላፊነት ነው፡፡ 'ግመል ሰርቆ አጎንብሶ' ዓይነት አፍጥጦ ያለን ሁኔታ እንደሌለ መቁጠር አይቻልም፡፡ ሁኔታን ባለማጤንና አስፈላጊውን የጋራ እርምጃ መውሰድ ካለመቻል የተነሳ በወገንና በአገር ላይ ለሚደርስ አደጋ ደረጃው ይባስም ይደግ እንጅ ማንም ከተጠያቂነት አያመልጥም፡፡ ሆኖም ግን ጉዳቱ ከደረሰ በኋላ ተጠያቂ መፈለጉ ለማንም ጠቀሜታ አይኖረውም፡፡ 'ቀድሞ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ' እንዲሉ 'አደጋን ሳይደርስ፣ ውሃን ሳይፈስ' ነውና የሚበጀውን አስቀድሞ ማድረግ ኃላፊነት ከሚሰማው ወገን ሁሉ የሚጠበቅ ነው፡፡ የተቃዋሚው ጎራ ያጠረው ጠንካራ ድርጅታዊ ይዞታ መሆኑ አጠያያቂ አይመስለንም፡፡ ይኽን ስንል የድርጅት ቁጥር ማነስ ማለታችን ሳይሆን የጠራ ራእይ ያለውና በደንብ የታሰበበት ስትራቴጂን የሚከተል፣ ሕዝብን ሲመች ብቻ እንዲሳተፍ የሚጠይቅ ሳይሆን መሠረተ-ሰፊ፣ ሕዝብን ማዕከል ያደረገ ትግል የሚያደርግና ጠንካራ አመራር የሚሰጥ ማለታችን ነው፡፡

ጥያቄው አሁንም እንደዚህ ሕዝባችንን ለማያባራ አጠቃላይ ትርምስ፣ አገራችንን ማለቂያ ለሌለው ክፍፍል የሚዳርግ ውጥረት በተፈጠረበት የአገራችን አሳሳቢ ሁኔታ

የመንግሥት ሥልጣን የጨበጠው ኢሕአዴግም ይሁን ተቃዋሚው ክፍል አልፎም ሕዝባችን ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል? ይኖርባቸዋልስ? የሚለው ይሆናል፡፡

ይኸን በተመለከተ በተቃዋሚው ክፍል ቢደረግ ይበጃል የምንለውን ትንሽ ዘርዘር አድርገን ለማቅረብ እንሞክራለን፡፡ ኢሕአዴግን በተመለከተ የምንለው አጭር ነው፡፡ ይኸውም ለዝንታለም የቆዩና ኢሕአዴግ ሥልጣን ከጨበጠ ጀምሮ እንዲባባሱና ሥር እንዲሰዱ የተደረጉ እጅግ ብዙ መሠረታዊ ችግሮች ያሉባትን ኢትዮጵያን የምታክል ጥንታዊት አገር በኢሕአዴግ፣ ከኢሕአዴግም በተወሰኑ ክፍሎች ብቻ ዘላቂ መፍትኄ ማስገኘት እንደማይቻል የኢሕአዴግ መሪዎች በተለይና አባላቱ በአጠቃላይ ሊገነዘቡት ይገባል፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ባለ ዥጉርጉርና ችግረ-ብዙ አገር በአንድ ድርጅት አቅም ብቻ ሁከትን ለመፍጠርና አፍራሽ ሥራን ለመሥራት (ብጥበጣ ለማካሄድ) ካልሆነ በስተቀር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሥር እንዲሰድ ለማድረግም ሆነ አገር ሊገነባ ፈጽሞ አይችልም፡፡ ስለሆነም ነገ እንደ ጉም ለሚተን ሥልጣንም ይሁን እሱን ተከትለው ለሚመጡ ጥቅማ-ጥቅሞች ሳይሆን፣ ይች በሁሉም የአገሪቱ ማዕዘናት ባሉ ዜጎች ክቡር መስዋዕትነት የተገነባችና የቆየች አገር እና ለዝንት-ዓለም እንግልት የተዳረገ ሕዝቧ ከባሰ ችግርና ትርምስ መዳናቸው ስለሚበልጥ፣ ካለፈው "መበዳደል" እና ቅሬታ የወደፊቱ የጋራ ሕይዎትና ዕድል በእጅጉ ስለሚያመዝን ወደ ኋላ ሳይሆን ወደፊት የሚያይ አዎንታዊ ፖለቲካን እንዲከተሉና ከአንዴም ሁለት ሦስት ጊዜ እንደ ዋዛ እንዲከስም የተደረገው ሁሉን-አቀፍ አገራዊ የእርቅና ሰላም ጉባዔ ተካሂዶ አዲስ የሰከነ ሽግግር በአገሪቱ እውን እንዲሆን የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ማድረግ ጥቅሙ ከሁሉም በላይ ለነሱ እንደሆነ ሊረዱ ይገባል፡፡

ሕዝብን በጉልበት መግዛት ምናልባት መፈራትን እንጂ በምንም መልኩ መከበርንም ሆነ ከልብ ተቀባይነትን አያስገኝም፡፡ ተፈርቶ የሚኖር ደግሞ መጨረሻው አያምርም፡፡ በሕዝብ ላይ ጉልበትን መፈተሽ ከፍተኛ የደካማነት ምልክት ብቻ ነው፡፡ የሕአዴግ ቅጥ-ያጣ እብሪት ያማረራቸው አንዳንድ ወገኖች ከኢሕአዴግ ጋር መነጋገርም ሆነ ከሱ ጋር ስለ ሰላም መደራደር ፈጽሞ አይቻልም ብለው እንደደመደሙ ግልጽ ነው፡፡ አይገርምም፡፡ ይኸ ደግሞ አንዳንድ የአገዛዙ ደጋፊዎች እንደሚሉት ከጥሬ ጥላቻ ተነስቶ አይደለም፡፡ አዎን እስካሁን ድረስ የአገራችንን የጋራ ችግሮች በተመለከተ የጋራ መፍትኄ መፈለግ ይቻል ዘንድ በተቃዋሚው በኩል በበጎ መንፈስ፣ በቅንነትና በግልጽ የተደረጉ የመነጋገርና የመደራደር ጥሪዎችና አሳቦች ሁሉ በኢሕአዴግ ዘንድ ተገቢው ዋጋና ክብደት አልተሰጣቸውም፡፡ ኢሕአዴግ የኢትዮጵያ ዜጎችን ያቀፈ ድርጅት ነው እስካልን ድረስ ግን ቱባ ቱባ ሹማምንቱን እንኳን ባይሆን የኢሕአዴግ አባላትም ሆኑ ቤተሰቦቻቸውና ዘመድ አዝማዳቸው በየቀኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚደርስበት ሰቆቃ፣ እንግልትና ችግር ይደርስባቸዋል፣ ይሰማቸዋል፡፡ እንዲያውም ለደረሰውና እየደረሰ ላለው ብሶት፣ ችግርና አበሳ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ውሎ አድሮ ተጠያቂነት እንደሚኖር የሚገነዘቡም ብዙዎች እንደሆኑና በግልጽ ለመወያየት ሁኔታው እንዲፈቅድ ከተደረገ በጋራ መፍትኄ ፍለጋው ከሕዝብ ጎን አብሮ መሰለፍ (የደረሰውን ጥፋት "በማካካስ" መንፈስ ጭምር) እንደሚመርጡ እናምናለን፡፡ ኢሕአዴግአውያን በተለይም በመሪነት ደረጃ ያሉት ይህን አደጋ አቃለው አሁን በያዙት ሁኔታ ሕዝብን ገፍተው ገፍተው ወደ አጉል አቅጣጫ በመውሰዱ ከገፉበት ሕዝብ የአልሞት-ባይ-ተጋዳይ ትንንቅ መጀመሩ አይቀሬ ይሆናል፡፡ ከዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ግን ማንም ተጠቃሚ አይሆንም፡፡

የመሣሪያ ጦርነት የሚያደርሰውን ጉዳት አቃልሎ ማየት ወይም መገመት አይቻልም፡፡ ሆኖም እራስን ለሰላምና በሕዝብ ፈቃድ ለማስገዛት የሚጠይቀው ግን በሰዎች ዘንድ ከባድ ሆኖ ይታያል፡፡ ሰላም በራስ ከመተማመን የመነጨ መከባበርን፣ ሁሉም የየራሱ አሳብ እንዳለው ማወቅንና እኔ ብቻ ያልኩት ካልሆነ ከሚል የትዕቢት አመለካከት መፅዳትን፣ እኔ የምፈልገውንና ለኔ የሚያስፈልገኝ ለእያንዳንዱ ዜጋ ሁሉ ያስፈልገዋል ብሎ አስፍቶ ማሰብን፣ ወዘተ... ይጠይቃል፡፡ ከማንም በላይና ይበልጥ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎችና

አባላት ብሔራዊ መግባባትን ከሚያስገኝ የብሔራዊ እርቅ ፖለቲካ ጋር እራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ ያስፈልጋል::

ችግሮችን በሰላም መፍታት ሳይቻል ሲቀር፣ ብሶቱን የሚያሰማበት ሕጋዊ መድረክ ሲገደው፣ በወደፊት ዕድሉ ላይ ድምፅ ሳይኖረው ሲቀርና ተስፋው ሲጨልም ሕዝብ መብቱን ለማስከበር ሌሎች መንገዶችን እንዲከተል ይገደዳል:: ከነኝህ መንገዶች አንዱና በአንዳንዶች ዘንድ ብቸኛውና አቋራጭ መንገድ ሆኖ የሚወሰደው የትጥቅ ፍልሚያ ይሆናል:: እራስን ከአጥቂ መከላከል መሠረታዊ <u>የተፈጥሮ መብት</u> መሆኑ የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይደለም:: ሆኖም ችግሮችን በመሣሪያ ኃይል ለመፍታት መሞከሩ የሚያስከትለውን ሁሉ አስቀድሞና ጠንቅቆ ማወቁ ተገቢ ይሆናል:: እንደ ኢዴኀአን የመሳሰሉ በአገራችን የተረጋጋና ዘላቂነት ያለው የሥርዓት ለውጥ እንዲመጣ የሚታገሉ ኃላፊነት የሚሰማቸው የአዎንታዊ ለውጥ ኃይሎች እንደዚህ ዓይነቱን ውሳኔ ወይም የትግል አቅጣጫ ከግብታዊነትና ከስሜታዊነት በራቀ ሁኔታ ጊዜ ወስደው ሊያስቡበት የሚገባ ጉዳይ ነው:: ጦርነት አውዳሚ ሂደት ነው:: ጦርነት ክቡር የሆነውን የሰው ሕይዎት የሚያጠፋና ንብረትን የሚያወድም ብቻ ሳይሆን በአገር የተፈጥሮ ሃብትና የአየር ጠባይ ላይ ከፍተኛ ብክለትና መዛባት የሚያስከትል፣ በሕዝብ ግንኙነትና ትስስር ላይ አሉታዊ የሥነ-ልቡና ጠባሳ የሚቀርጽ ድርጊት ነው:: በመሆኑም እንኳን እንደ ኢትዮጵያ ላለ በምጣኔ ሃብት እጅግ የደቀቀ፣ ሁለንተናዊ ማኀበረሰባዊ ውጥረት ለተጠናወተው አገር ለማንም አገርና ሕዝብ ጦርነት የሚፈለግ ነገር አይሆንም:: ይሁንናም ጦርነትን ስላልፈለግነው ብቻ አይቀርም::

በአሁኑ ጊዜ ከሕወሓት/ኢሕአዴግ ጋር የሚደረገው የመብት ማስከበር ትግል በረዥሙም ለሚጠብቀን የአንድነታችን መጠበቅ አሳሳቢ ጉዳይ አጋዥና የተሳሰረ እንደሚሆን ተደርጎ እንጂ በነጠላው ሊታይ እንደማይገባው ከወዲሁ ማስላቱ ተገቢ ይሆናል:: አንዳንድ ድርጅቶች የአገሪቱን ዘለቄታዊ አንድነትና ጥቅም ሳይሆን አገዛዙን በመጥላት፣ አንዳንዶችም በአገራችን በቶሎ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን የሚችለው በቅድሚያ የኢሕአዴግን አገዛዝ ከሥልጣን በማውረድ ሲቻል <u>ብቻ</u> እንደሆነ በነጠላው በማየት አንዳንድ የኃይል አሰላለፍ ስህተት ውስጥ ሲገቡ መታዘባችን አልቀረም::

ሁሉም ሊገነዘበው የሚገባ ቁም-ነገር ግን የኢትዮጵያን ችግሮች አንዱ ሌላውን በመግፋትና አንዱ ሥልጣንን ከሌላው በጉልበት በመንጠቅ ብቻ የሚፈታ አለመሆኑን ነው:: ለዚህም ነው ችግሮቻችንን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመፍታት የሚደረገው ጥረት ሁሉን-አቀፍና የሁሉንም ትብብርና እርብርብ የሚጠይቅ ነው የምንለው:: የድርጅታችን እምነትና የትግል ቅኝት ከዚኽ ስትራቴጅአዊ እይታ አኳያ የተቀመጠ ነው::

ይኸ ምን ማለት ነው?

በእኛ እምነት ሁሉም ለውጥ ፈላጊ ኃይል ኢትዮጵያ ነገ የተንኮታኮተች አገር (failed state) ከመሆን ዕጣ ድና፣ አሁን ከምትገኝበት ፈታኝ ሁኔታና አጣብቂኝ ይዞታ ወጥታ ነገ አይደለም የዛሬ ሃያና ሰላሣ ዓመት ምን ዓይነት አገር እንድትሆን እንፈልጋለን? ቁጥራቸው እየጨመረ የሚሄደው ዜጎቻችንስ እየተጣበበ በመጣ ምድር፣ እየኮሰመነ በሚሄድ የሕይዎት ማቆያ (መኖሪያ) ምንጭ፣ ተሻሚው እየበዛ በመጣ ጥሬ ሃብት፣ በእውቀትና በሃብት እየተለወጠና እየዳበረ ካለ የዓለም ኅብረተሰብ ጋር በዚህ ዓለም-አቀፋዊ የጥቅምና የግንኙነት መረብ (ግሎባላይዜሽን) አውላላ የፉክክር መድረክ መወዳደር ብቁ እንዲሆኑ የሚያስችል ሁኔታ እየተፈጠረላቸው ነወይ? ዋነኞቹ የሕዝባችን ፍላጎቶችና ጥያቄዎች ምንድን ናቸው? ለሚሉትና ለሌሎችም ተመሳሳይ ክብደት ላላቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች ከስሜታዊነት በራቀና በሰከነ መልክ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል::

በሕግ ፊት የሁሉም እኩልነት የሚረጋገጥበት ፍትኀ መኖር፣ የሰብአዊ መብት መከበር፣ መሐይምነትን ማጥፋት፣ ተላላፊ ተውሳኮችን ማስወገድ፣ በቂ ምግብና ንፁህ የመጠጥ ውሃ

ማግኘት፣ የትምህርት ዕድል ለሁሉም እንዲኖር ማረጋገጥ፣ የተፈጥሮ ሃብቶቻችንን በአግባቡ መጠበቅና መንከባከብ፣ ፍትኃዊ የኤኮኖሚ ስሪት መዘርጋት፣ ወዘተ... የመሳሰሉ በአገራችን ያሉ ዋና ዋና መሠረታዊና አሳሳቢ የጋራ ችግሮቻችን በአንድ ድርጅት በጎ ፈቃድ ወይም በተወሰኑ ክፍሎች ትግል ብቻ በአስተማማኝ ሁኔታ የሚፈቱና እውን የሚሆኑ አይደሉም።

በኛ በኩል ለእነኝኽ መሠረታዊ እሴቶች አስተማማኝ ግኝትና እውንነት አስፈላጊ የሚሆኑት እርምጃዎች የሚከተሉት ናቸው ብለን እናምናለን።

## 1. መሠረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ማድረግ፤

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አሁን እየሰፈነ ካለው ከጎሰኝነት፣ ከጠባብ ወገንተኝነት፣ ከእርስ በርስ አለመተማመንና ከመጠራጠር፣ ከተስፋ መጨለም፣ ከግለኝነት፣ በራስ ካለመተማመን ወይም እራስን ዝቅ አድርጎ ከማየት፣ ካለመከባበር፣ ከጥላቻ፣ ጥፋትን አምኖ ካለመቀበል፣ ቂምና በቀል አዝሎ ከመኖር፣ ወዘተ... ከመሳሰሉ አሉታዊ አስተሳሰቦች እራሱን (እራሷን) መለወጥና ማጽዳት ያስፈልገዋል (ያስፈልጋታል)።

በድርጅትም ይሁን በቡድን ደረጃ ለጋራ ችግሮቻችን የጋራ መፍትኄ ለመፈለግ ከመኳተናችን በፊት በግለሰብ ደረጃ እያንዳንዳችን ከላይ ከተጠቀሱት ሥነ-ልቦናዊና ሥነ-አእምሮአዊ ሸክሞች እራሳችንን ነፃ ማውጣት የመጀመሪያውና ተቀዳሚው ተግባር ሊሆን ይገባል። በራሳችን ላይ የባህልና የአመለካከት ለውጥ ማድረግን (አብዮት ማካሄድን) ቅድሚያ ልንሰጠው የግድ ይላል። ዞሮ ዞሮ ድርጅቶች የግለሰቦች ስብስቦች ስለሆኑ ምንም ዓይነት የተዋበ ፕሮግራም ቢኖራቸው የድርጅቶች አባላት እራሳቸውን ነፃ ያላደረጉ እስከሆነ ድረስ ድርጅቶች መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት ይቸገራሉ። አሁን በየድርጅቱ የሚታየው የሻከረ ግንኙነት፣ የእርስ በርስ መዘነጣጠልና አለመከባበር ከዚሁ የግለሰቦች አስተሳሰብ ካለመቀየር (ባህልን ከመልቀቅ) የመነጨ እንደሆነ እንገምታለን። **እራሳችንን ነፃ ሳናደርግ ለሌላው ወገንም ሆነ ለአገር ነፃነትና ለዜጎች እኩልነት ለመታገል መሞከሩ ትርጉም አይኖረውም።** ስለሆነም ዜጎች በዚህ ረገድ እራሳቸውን እንዲመረምሩ ማድረግ ያስፈልጋል።

በአገራችን ረጅም ታሪክ ውስጥ ታይቶም ተሰምቶም በማይታወቅ መልክ አሁን የሚታየው ዜጎች አገራቸውን እንደ ሲያል ቆጥረው ባመቻቸው መንገድ ሁሉ ጥለው ለመውጣት የሚያደርጉት ጥረትና መሟሟት ችግራችን ምን ያኽል አስቀያሚ ደረጃ ላይ እንደደረሰ ያሳያል። ይኽ ደግሞ ዝም ብሎ የመጣ እንዳልሆነ የታወቀ ነው። ዜጎቻችን በራሳቸውና በአገራቸው ተስፋ ቆርጠዋል ማለት ነው። ለአንድ ሰው አገሩ ከተወለደ ጀምሮ ችግር እንጂ ተስፋ የማይታይባት ምድር ስትሆንበት፣ ወደ-ፊትም የሚኖረው ተስፋ ጨርሶ ጨለማ ሲሆንበት፣ ቀደም ሲል የነበሩ ባህላዊ መተሳሰቦች፣ ትስስሮችና የቆዩ የቤተሰብና ማኅበረሰባዊ የግንኙነት መረቦች በልዩ ልዩ ጊዜ-ወለድ ጫናዎች እንዳልነበሩ ሲሆኑበት፣ የበይ ተመልካች ሲሆን፣ እሱነቱን በአገሪቱ ዜጋነት ሳይሆን በአካባቢው እንዲወሰን ሲደረግበት፣ በአገሩ ጉዳይም ሆነ በወደፊት ዕድሉ ድምፅ እንደሌለው ሲመለከት ከአገሩ ጋር የሚኖረው ቁርኝት ምን እንደሚሆን መገመቱ ቀላል ነው። በዚህ መልክ ከሚገኝ ዜጋ በአገሩ ኩራትንና በራስ መተማመንን መጠበቅ አስቸጋሪ ነው። ስለሆነም ኢትዮጵያ አገራችን ልጆቿ ፊታቸውን እንዲያዞሩባትና እንዲርቋት ሳይሆን ኮርተውባት፣ ጓጉተውና ሳስተው እንዲይዟት ለልጆቿ ምቹ እንድትሆን የማድረግ አጣዳፊነትን ሁሉም ሊረዳው ይገባል እንላለን።

ወደፊት ማንም መንግሥት ይምጣ ማ አገራችን አሁን ከምትገኝበት አሳፋሪና አሳሳቢ ደረጃ ወጥታ እራሷን በምግብ እንድትችልና ሕዝባችን የዕድሉ ወሳኝ በሆነበትና መብቶቹ በተከበሩበት ሁኔታ አስተማማኝ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠረት ይዞ በሱነቱ ተማምኖ የልማት ጎዳናን እንዲያያዝ ሕዝብ አምኖበት እስከ አምስት ዓመት ሊዘልቅ የሚችል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን የሚጠይቅ አገር-አቀፍ እንቅስቃሴ እንደሚያስፈልግ የድርጅታችን እምነት ነው።

ስለሆነም ከዚህ የአስተሳሰብ ለውጥ አስፈላጊነት አኳያ በአገራችን ላይ በማያዳግም መልክ ዘለቄታዊነት ያለው መሠረታዊ ለውጥ እንዲመጣ የምር የሚፈልግ ሁሉ፣ በተለይ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሥልጣን ላይ ቢወጡ የፖለቲካ ሥልጣን ለመበልጸጊያና ሃብት ማካበቻ መንገድ ሳይሆን ለተወሰኑ ዓመታት፣ ቢያንስ ሕዝባችን በምግብ እራሱን እስኪችልና ከአሳፋሪ የዓለም ተመጽዋችነት እስኪላቀቅ ድረስ፣ ቢቻል ያለ ደሞዝ ቢበዛ <u>ለኑሮ በሚበቃ ድጎማ ብቻ</u> አገርንና ሕዝብን ለማገልገል ቁርጠኝነቱና ዝግጁነቱ እንዲኖራቸውና ይኽንኑ አስቀድመው ለሕዝብ ቃል እንዲገቡ ያስፈልጋል የሚል እምነት አለን።

## <u>2. የድርጅቶች ትብብር መፈጠር አስፈላጊነት፤</u>

ትብብር ለምን ዓይነት ትግልና ዓላማ?

በአገራች ለኅብረተሰባችን ለውጥ ለማምጣት ብዙ ድርጅቶች ለረጅም ጊዜ በተለያዩ መልኮችና መንገዶች ታግለዋል፣ እየታገሉም ነው። ሆኖም ግን ሕዝባችንን የመብቶቹ ባለቤት የሚያደርግ ሥርዓትን እስካሁን ማስገኘት አልተቻለም። ይኽ የሆነው ደግሞ የሚከፈለው መስዋዕትነት አንሶ ወይም ሕዝባችን ለተሻለ ሥርዓት ያለው ፍላጎት ስለከሰመና ጨርሶ ተስፋ ስለቆረጠ አይደለም። ለፍትኃዊ ሥርዓት፣ ለእኩልነትና ለአንድነት የሚታገሉና መስዋእት እየከፈሉ ያሉ እልፍ አእላፍ ታጋዮች አሁንም አሉ፣ ወደፊትም ይኖራሉ። ሆኖም <u>ድርጅቶች በጋራ ለመሥራት ቁርጠኝነቱ እስከሌላቸውና ተነጣጥለው በየፊናቸው በስንጥር መጓዝን እስከመረጡ ድረስ የፈለገውን ያኽል አንፃራዊ የተናጠል ጥንካሬ ቢኖራቸውም እንኳ የወል ጠቀሜታና ሁሉም አትራፊ የሚሆንበት ውጤትን ማስገኘት አይችሉም።</u>

ቀደም ሲል በተደጋጋሚ እንደገለጽነው የአገራችንን የወል ችግሮች ለመፍታት የጋራ ጥረትን ይጠይቃል። ይኽ የጋራ ትግል ደግሞ ግቡ ምን እንደሆነ ለሁሉም ግልጽ ሊሆን ይገባል። በኢዴኅአን እምነት በአገራችን ዘላቂ ሰላና መረጋጋት ከሌለ የጋራ ችግሮቻችንን በአጥጋቢና በአግባቡ መፍታት አይቻልም። ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት ደግሞ ብሔራዊ መግባባትን ይጠይቃል። ብሔራዊ መግባባት የሚመጣው ዴሞክራሲያዊ የሽግግር ሂደትን መከተል ሲቻል ብቻ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ላለ የተወሳሰበ የችግሮች ክምር ላለበት አገር ይኽ አማራጭ የሌለው አካሄድ ነው። (ከዚህ አርቆ ያየ እምነት በመነጨ አስተሳሰብ ነበር ምርጫ ዘጠና-ሰባትን ተከትሎ የታየውን ውጥረት ለመፍታትና አዲስ የሽግግር ሂደት ለመጀመር "ብሔራዊ የአንድነት መንግሥት" የማቋቋም አሳብ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) የቀረበውና ቅንጅትም ወደ መጨረሻ ተስማምቶበት ይፋ የተደረገው። ያ አሳብ በምንም መንገድ ጥሬ ሥልጣን ከኢሕአዴግ ለመጋራት በመፈለግ እንዳልነበር የታወቀ ነው። ባለመታደል የቀረበውን አሳብ ገዥው ፓርቲ ውድቅ አደረገው)።

በተናጠል ለመታገል የመረጡ ድርጅቶች ግልጽ እንዲያደርጉ የሚያስፈልገው ትግላቸው ሕወሓት/ኢሕአዴግን ለመተካት ነወይ? ከሆነ ዕድሉ ቢኖር እንዴትና በምን ሁኔታ የኢትዮጵያን ሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄዎች መፍታት ይችላሉ? በምርጫ ሆነ በምን አሁን ያለውን ገዥ ፓርቲ መተካት ከሆነ ዋና ዓላማቸው ብሔራዊ መግባባትን ለሚጠይቁ መሠረታዊ ችግሮቻችን በምን መልክ ምላሽ ለማስገኘት ይቻላቸዋል? ሕወሓት/ኢሕአዴግ በሕዝብ ዘንድ ያጣውን ብሔራዊ ተቀባይነትና አመኔታ እንዴት ማግኘት ይችላሉ? እንደሚታወቀው በጎ ፈቃድ ወይም ፍላጎት ብቻ አይበቃም። ብሔራዊ መግባባት በአዋጅ ማስገኘትም አይሆንም። አሁን ባለው የአገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ በተናጠል የሚታገሉ ድርጅቶች ለእነኝህ ጥያቄዎች የየራሳቸው ልዩ ልዩ መልሶች እንደሚኖሯቸው እናምናለን። እነኝህ ልዩ ልዩ ዓላማና ግብ ያነገቡና ልዩ ልዩ ስልትን የሚከተሉ ኃይሎች ቢያንስ ከመነሻቸው የተደራጁበትን መልክና የሚከተሉትን ስልት እንዲይዙ ያደረጋቸው በአገሪቱ የሰፈነው የፖለቲካ ሁኔታ መሆኑና የዚያም ውልድና ነፀብራቅ መሆናቸው ሊታመን ይገባል። እያንዳንዱ ድርጅት የተነሳበት ምክንያት ሊለያይ መቻሉ ባያጠያይቅም የወደፊቱ የጋራ ዕጣ ፋንታ ግን ሁሉንም የሚመለከት መሆኑ በተገቢ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል።

በተናጠልም ይሁን በጋራ ለአዎንታዊ ለውጥ በሚታገሉ ኃይሎች መኻል **የአገራችን መሠረታዊ ጥያቄዎች አፈታት ብሔራዊ መግባባትን በመጠየቁ** ዙሪያ ከወዲሁ መግባባት እንዲኖር ካልተደረገ መነሻውም መድረሻውም የመንግሥት ለውጥ ላይ ብቻ ያለመ ትግል ለአገርና ለሕዝብ ዘለቄታዊ ጥቅም ያስገኛል ብለን አናምንም። እዚኽ ላይ ነጥባችን በዚህም በዚያ ብሎ መንግሥትን መለወጥ አይቻልም የሚል የየዋህ ክርክር አይደለም። ጥያቄአችን ልዕለ-ግባችን እሱ ነወይ? የሚል ነው። **የኛ ምርጫና እምነት የመንግሥት ለውጥ የሥርዓት ለውጥን ባለመ ሂደት ውስጥ የሚካተት መሆን አለበት የሚል ነ**ው። **የሥርዓት ለውጥን ያለመ ትግል ሕዝብን ያቀፈና የራሱ የሕዝቡ ትግል ስለሚሆን ውጤቱና አስተማማኝነቱ ዘለቄታዊነት የሚኖረው ይሆናል።**

በተቃዋሚው በኩል አንዱ ከፍተኛ ድክመት ሆኖ የቀየውና አሁንም አንዳንድ ድርጅቶችን ያለቀቃቸው ጥንውት የሚከተሉት ስልት በተቃውሞ ፖለቲካ ላይ ብቻ የተንጠለጠለ መሆኑ ነው። የዚኽን ዓይነት የአስተሳሰብ ቅኝት የሚከተሉ ድርጅቶች ምንም ይሁን ምን፣ ማንም ሥልጣን ይያዝ ማን እነሱ በዋናነት እስከሌሉበት ድረስ በጎ ሊሠራ ይችላል ወይም ለውጥ ሊመጣና በሂደት ለነሱም የፖለቲካ እንቅስቃሴ የተሻለ ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል ጨርሶ የዘነጋ፣ ባብዛኛው ሥልጣን የያዘው ክፍል የሚያደርገውን ስህተት ከሥር ከሥር እየተከተሉ በማውገዝና በመርገም ላይ ባተኮረ አካሄድ ጊዜአቸውንና ጉልበታቸውን ያጠፋሉ። የዚኽን ዓይነት አስተሳሰብ የሚከተሉ ድርጅቶች የዘነጉት መሠረታዊ ነገር የትግል አጀንዳቸውን ሙሉ በሙሉ እንቃወመዋለን የሚሉት ክፍል እንዲቆጣጠር ዕድል የሰጡና ቅድሚያን የለቀቁ መሆናቸውን ነው። ማንም ድርጅት **የትግሉን አጀንዳ መቆጣጠር ካልቻለና ቅድሚያን ከተነጠቀ** ደግሞ የሚያደርገው ትግል ኀሉፋዊ (passive) ስለሚሆን የቆመለት ዓላማ ምንም ቅዱስ ቢሆን ግቡን በሮስግባቡ መምታት አይቻለውም። ስለሆነም የተቃዋሚው ክፍል አሁንም ሆነ ወደፊት በመስክ ላይ ያለውን ሚዛን የሚደፋ ትግል ማድረግ ከፈለገ **ቅድሚያን በጨበጠና ባለቀቀ መልኩ የትግሉን አጀንዳ መቆጣጠር ይኖርበታል።**

እንግዲህ ድርጅቶች ከወዲሁ መሠረታዊ ችግሮቻችንን ዘላቂታዊነት ባለው መንገድ ለመፍታት ከተስማሙ ይኽን እውን ለማድረግ መከተል አስፈላጊ ወደሆነው ወደ ቀጣዩ ነጥባችን ማለትም ወደ ዴሞክራሲያዊና ሁሉን-አቀፍ የሽግግር ሂደት ጉዳይ ይመራናል።

## 3. ለአዲስ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ሂደት መታገል፤

### ሽግግር ለምን እና እንዴት?

#### ሀ) ተቃዋሚው ክፍል ምን ማድረግ ይኖርበታል?

የአገራችን ሁኔታ ከልብ ያሳሰባቸው ድርጅቶች ለበርካታ ዓመታት መሠረታዊ ለምንላቸው ሥር የሰደዱና ክብደት ያላቸው ውጥንቅጥ የጋራ ችግሮቻችን ዘለቄታዊነት ያለው መፍትኄ እውን የሚሆነው በአዲስ መንፈስ ሁሉን-አቀፍ የሽግግር ሂደትን መከተል ስንችል ነው የሚለውን አሳብ ሕወሓት/ኢሕአዴግን በዋናነት ጨምሮ አንዳንድ ድርጅቶች ሲነቅፉት፣ ሲቃዎሙትና አልፎም ሲያፌዙበት ተስተውሏል። በዚኽ አስተሳሰብ የሚያ-ፌዙትም ይሁኑ የሚቃወሙት ክፍሎች አንድም የችግሮቻችንን ልክ፣ መጠንና ክብደት አቃልሎ ከማየት፣ አንድም ሽግግር ሲባል የመንግሥት ሥልጣን ዝውውር ስለሚመስላቸው ባመቸ መንገድና እንደምንም (በምርጫ ይሁን በጉልበት) የመንግሥትን ሥልጣን ከሌላው መንጠቅ ከተቻለና ከተያዘ ወይም አገዛዙ በሆነ ተአምር ከተወገደ ችግር አይኖርም፣ ለሕዝቡ መብትም ሆነ ሌላው ሁሉ ከላይ በችሮታ መልክ ሊንቆረቆርለትና እንዳስፈላጊነቱ በመቅኑን ሊሰጠው ይችላል ከሚል ሁኔታን ካላገናዘበና ከተዛባ አመለካከት በመነሳት የሚወሰድ አቋም ሲሆን፤ ለኢሕአዴግ ደግሞ ሽግግር ማለት እሱ ደርግን ተክቶ ከሽግግር መንግሥትነት ወደ

ቋሚ መንግሥትነት የተቀየረበት ሂደት ስለተከናወነ ሌላ ሁሉን-አቀፍ ሽግግር የሚሉት ነገር አያስፈልግም ከሚል በጣም የተሳሳተ አቋም የመነጨ እንደሆነ የታወቀ ነው፡፡ ችግሩ እንግዲህ በሁሉም በኩል አዲስ የሽግግር ሂደት የድርጅቶች መቀያየርን ሳይሆን ኅብረተሰባችንን በሞላ የማሸጋገር ያኽልን ከባድ ጉዳይ እንደሚጠይቅ ካለመረዳት የመጣ የአስተሳሰብ ዝንፈት ነው ማለት ነው፡፡ በሁሉም ዘንድ የተሳተው ይኸ ቁልፍ ነገር ነው፡፡
በኛ እምነት በአገራችን አስተማማኝ ሰላም እንዲኖርና የመልሶ ግንባታ ሥራን መሥራት እንዲቻል ከድርጅቶችም ይሁን ከግለሰቦች ባለፈ መልኩ ኅብረተሰባችን አሁን ለሚገኝበት ላለመተማመንም ይሁን ለአጠቃላይ ምስቅልቅል ሁኔታዎች ያበቁት መሠረታዊ ምክንያቶች፣ ሰበቦችና ጠንቆች ምን እንደሆኑና ለምንስ እንደተፈጠሩ በግልጽና በቀና መንፈስ ተነጋግሮ ለመማማርና እነዚህ ጠንቆች እንዳይመለሱ የሚያስችል ሁኔታን ለመፍጠር በቅድሚያ ፍትኅ ሰፍኖ፣ ጥላቻ፣ መፈራራት፣ ቂም ቋጥሮ በጠላትነት መተያየት፣ ወዘተ... ተወግደው የወንድማማች/እህትማማች፣ የመከባበርና የመደጋገፍ መንፈስ እንዲፈጠር ነው ሁሉን-አቀፍ ብሔራዊ የእርቅና ሰላም ጉባዔ መካሄድ የሚኖርበት፡፡ ይኸም ሕዝባዊና ሰላማዊ ሂደቱን አጠናክሮ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት የሚወስደን የሰከነ ሽግግር ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታን ለመፍጠር ለሚደረገው ጥረት ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው፡፡ ለዚኽ ሁሉ ደግሞ የዴሞክራሲን መስፈን ይጠይቃል፡፡ በብሔራዊ እርቅ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር በማድረግ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት መመሥረትና አገራችን የተረጋጋ ኅብረተሰብ አገር እንድትሆን ለማድረግ ግን በሽግግር ሂደቱ ላይ የሁሉም ኃይሎች አመኔታና ተሳትፎ ያስፈልጋል፡፡

ዴሞክራሲያዊ የሽግግር ሂደት እንከተል ስንልም የተሰባሰቡት ድርጅቶች ሽግግሩን መርተው ጻር እንዲያደርሱት ወይም የደርግንና የኢሕአዴግን ፈለግ ተከትለው እራሳቸውን ከሽግግር መንግሥትነት ወደ ቋሚ መንግሥትነት እንዲቀይሩ አይደለም፡፡ ያ ዋነኛና አይነታ ተልዕኮ ሙሉ በሙሉ ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር አካል (ኮሚሽን) የሚተው ተግባር ነው ብለን እናምናለን፡፡ በኛ በኩል ሽግግር የምንለው የጉልቻ መቀያየር ዓይነት ሥልጣን ከአንድ ድርጅት ወደ ሌላ ድርጅት ወይም የድርጅቶች ጥምር የሚደረግ የሥልጣን ቅብብል ወይም ዝውውር ሳይሆን፣ ሕዝባችን ከአንድ ኢ-ዴሞክራሲያዊ የአገዛዝ ሥርዓት ወደ ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚያደርገው የሰከነ ሽግግር ነው፡፡ ይኸም ሂደት ሕዝባችንን ሙጭጭ አድርገው ከያዙት የአምባ-ገነኖች የሥልጣን ዝውውርና መቀማማት ዑደትና እሱም ከሚወልዳቸው የዕድሉ ወሳኝ አለመሆንና የመብት እጦት፣ የረሃብና የልዩ ልዩ ችግሮች መቀጠል፣ የአስተማማኝ ሰላምና መረጋጋጥ እጦት፣ የአገራዊ አንድነት መናጋት፣ ወዘተ... በአስተማማኝ መልክ ለአንዴና ለመጨረሻ የሚገላገልበትና ሰላማዊ የተረጋጋ ሕይዎቱን መምራት የሚያስችለውን ጎዳና መያዝ ያስችለዋል ብለን እናምናለን፡፡

የዴሞክራሲ መብቱን የተነፈገ ሕዝብ ሰላሟ የመንግሥት ልውውጥ ቢደረግ አቸናፊዎች በተቸናፊዎች ላይ በሚጭኑት ውስጡ ሰላም የሌለው ግልብ ሰላም ስለሚሆን፣ አንዱ ዘመናይ በሌላው ጉልበተኛ እየተለዋወጠ አልፎም "የቀናው" ወደ ቤተ-መንግሥት የተረታውና "ቀን የጣለው" እንደ ዜጋ በሰላም መኖር ሳይሆን ወደ እስር ቤት መውረድ ወይም ወደ ስደት መሄድ ምርጫ የሆነበት፣ የአንዱ ሰው (ቡድን) ሥልጣን ላይ መውጣት በሌላው ሰው (ቡድን) መቃብር ላይ እንዲሆን የማድረጉ የመጠፋፋት አዙሪት እንዲቀጥል ከማድረግና ዜጎች የዕድላቸው ወሳኝ ሌሎች ሆነው በአገራቸው ጉዳይ ባይተዋር እንዲሆኑ የሚያደርግ ብልሹ ሁኔታን ከማመቻቸትና የሕዝብ ሰቆቃ እንዲቀጥል፣ ዜጎች አንገታቸውን እንደሰበሩ እንዲኖሩ፣ አስተማማኝ ሰላም እንዳይኖር፣ በሽታ፣ ሰው-ሠራሽ ችግር እንዲበራከት፣ ወዘተ.. ከማድረግ የተለየ ውጤት ሊኖረው አይችልም፡፡ "በመቃብር ላይ" የሚሠራ ሥራ አለ ከተባለ አዲስ ሥርዓት በአሮጌ ጨቋኝና አፋኝ ሥርዓት መቃብር ላይ እንዲገነባ ማድረግ ብቻ ነው፡፡

የኛ እምነት ዜጎችን ከሕግ ውጭና በጥሬ ጉልበት ማስወገድና መጠፋፋት ለሕዝብና ለአገር እርባና ያለው የሰከነ ሽግግርን አያስገኝም የሚል ነው፡፡ ለሕግ የበላይነት እታገላለሁ የሚል ማንኛውም ድርጅት ያ የሚታገልለት ፍትኅና የሕግ የበላይነት ሁሉም ላይ፣

*የሚጠላውና የሚታገለውም ላይ ጭምር፣ እኩል የሚሠራ እንጂ ለሱና ለደጋፊዎቹ ብቻ እንዳልሆነ መገንዘብ ይኖርበታል። ለኮሎኔል መንግሥቱም ይሁን ለአቶ መለስ ወይም ለሌላው የማይሠራ የፍትኅ ሥርዓት፣ በገዥዎችና በተገዥዎች ላይ እኩል የማይውል የሕግ የበላይነት ለአገራችንም ሆነ ለአጠቃላይ ሕዝባችን እርባና የለውም፣ አይጠቅምም።*

*የአገራችንን ሁኔታ መለወጥ የሚቻለው ቀደም ሲል እንደጠቆምነው አግላይነት በሌለበትና የሁሉን ተሳትፎ በሚጠይቅ እርብርብ እና ይኸ እርብርብም ዴሞክራሲያዊ ሽግግር በማድረግ ሕዝባችንን የመብቶቹ ባለቤት እንዲሆን በማስቻል መሆን ይኖርበታል። ይኸ ደግሞ የድርጅቶችን መተባበር እንደሚሻ ግልጽ ነው። የዴሞክራሲ ፖለቲካ ደግሞ ተቻችሎና ተከባብሮ በልዩነት መሥራት መቻልን የግድ ይላል። አሉ በሚባሉ ልዩነቶች የበለጠ መራራቅ፣ መፈራረቅና አልፎም በጥላቻ መተያየትና በጠላትነት መፈራረጅ ባለበት ሁኔታ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር የሚቻል አይሆንም። ጉዳዩ የግል ሳይሆን የአገርንና የሕዝብን የወደፊት ዕድል መወሰንን ያኽል ከባድ ቁም-ነገር ስለሆነ ልዩነቶችን ተቀብሎ ብቻ ሳይሆን አክብሮ በሚያግባቡ አገራዊና ሕዝባዊ የጋራ ጉዳዮች ላይ መሥራት የግድ ይሆናል። ያ ደግሞ ኃላፊነትን የላቀ ኃላፊነት በተሞላው መንፈስ መወጣት ሆኖ ይቆጠራል።*

*ስለዚህ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር እውን እንዲሆን በቅድሚያ እያንዳንዱ ለውጥ ፈላጊ ኃይል ከራሱና ከቡድኑ (ከድርጅቱ) በላይ ለሆኑ ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም እራሱን ለማስገዛት ፈቃደኝነትና በተግባር የሚገለጽ ዝግጁነት እንዲኖረው ያሻል። ለምንታገልለት ዓላማ ቅደም ተከል እንድንሰጠው ያስፈልጋል። እያንዳንዱ ድርጅት በሥልጣን ላይ ያለውን ክፍል ጥፋትና ወንጀል ከመጠቆምና ከመኮንን ውጭ ከሌሎች መሰል ድርጅቶች ጋር የሚኖረውን ትብብርና የአገሪቱ ሁለ-ገብ ችግሮች ከሚፈቱበት አንፃር የትግሉ ግብ መምቻ ሂደት (ስትራቴጂ) ቅደም-ተከተል ላይ በሃቅ ለመስማማትና በተግባር ለመተርጎም ዝግጁነት ሊኖረው ይገባል።*

*ሁሉም ለአዎንታዊ ለውጥ የቆሙ ድርጅቶች ሊገነዘቡት የሚገባው በአሁኑ የአገራችን ሁኔታ ሊደረግ የሚገባው ትግል ምን ዓይነት ትግል እንደሆነ በማያሻማ መንገድ መግባባት ላይ መድረስ የመጀመሪያው ኃላፊነት ይሆናል። በአገሪቱ ውስጥ የሚታገሉ ኃይሎች ሁሉ በጋራ መሥራት ይኖርባቸዋል ስንል ሁሉም አትራፊ ሊሆንበት የሚችል አስተማማኝ ውጤትን ለማስገኘት ይቻላል ከሚል እምነት በመነሳት ነው። ይኸንን አስተሳሰብ አንዳንዶች "የድርጅት ነፃነትን" የሚጋፋ አድርገው ሊቆጥሩት ይችላሉ። በኛ እምነት የአገር አንድነት ሳይረጋገጥ ስለ ድርጅት መንገብገብ መቀመጫ ገልቦ ክንንብ ይሆናል።*

*ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደሞከርነው እኛ የምንለው ድርጅቶች ሙሉ ድርጅታዊ ነፃነታቸው ተጠብቆላቸው እንዲሠሩ ሁኔታው ይመቻችላቸው ነው። ከእንክርዳድ ክምር ስንዴ ለማምረት መሞከር ወይም "ከብት ባክልዋለበት ኩበት ለቀማ" አይቻልምና፣ በቅድሚያ የፖለቲካ ድርጅት ውድድር ማድረግ የሚቻልበትን ሁኔታ ለመፍጠር እንሞክር ነው የምንለው። ለነገሩ አሁን ያለው ቅጥ ያጣ የድርጅት መበርከት ለፖለቲካ ሂደቱ የሚያደርገው እርባና ያለው አዎንታዊ አስተዋጽዖ እንደሌለ እምነታችን ነው። በአንድ አገር ውስጥ የድርጅቶች መብዛት የግድ የዴሞክራሲ መኖርን አያመላክትም። በተቻለ መጠን ተመሳሳይ ዓላማና ግብ ያላቸው እየተዋኀዱ የድርጅቶች ቁጥር ቢቀንስ፣ ቢያንስ ግን ከውኅደት መለስ ባለ ጠንካራ የመተባበሪያ መድረክ ተሰባስቦ መታገል የሚደረገውን የአገር ማዳንና የዴሞክራሲ ግንባታ ተልእኮ በማሳካቱ ረገድ በእጅጉ እንደሚረዳ አንጠራጠርም።*

*እስካሁን ድረስ ድርጅቶች አብረው መሥራት አለባቸው፣ መተባበር ይኖርባቸዋል የሚለውን አሳብ ሁሉም ድርጅቶች በአደባባይ ሲገልጹ ይደመጣል። በዚኽ ረገድ የየድርጅቶቹ መግለጫዎች ሁሉ ይኽንን ሳይሉ የሚያልፉበት ጊዜ የለም። የሚገርመው ግን ይኽንን አሳብ በተጨባጭ ተግባራዊ ለማድረግ እና እንዴትና መቸ ቢሆን እንደሚሻል ለምክክር እራሱን አዘጋጅቶ የቀረበና ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታ ግልጽ ውይይት እንዲደረግ*

የጠየቀና ተደጋጋሚ ሙከራ ያደረገ ምናልባት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ብቻ ነው ማለት ይቻላል። የሁሉም መግለጫ የጋራ ትግልን አስፈላጊነት ከመግለጽ በተጨማሪ ኑና "በኔ ዙሪያ" ተሰባሰቡ፣ ተከተሉኝ ዓይነት ጥሪን በማስተጋባቱ ረገድ አንድነት አላቸው ማለት ይቻላል።

ባለፉት አሥራ-ሰባት ዓመታት ያየናቸው የድርጅቶች የመሰባሰብ ሙከራዎች በአገር አንድነት ዙሪያ ይሁን በአገራችን የዴሞክራሲ ሂደት ረገድ በርካታ አስተዋጽያዎችን እንዳደረጉ እሙን ነው። ካለፉት ልምዶች በመነሳት ድርጅታችን በአሁኑ ጊዜ የተቃዋሚ ኃይሎች መሰባሰብ ወቅታዊ አጀንዳዎች ሁለት ናቸው ብሎ ያምናል።
እነሱም፤

ሀ) ኢትዮጵያ ተንኮታኳች አገር (failed state) ለመሆን አፋፍ ላይ ስለሆነች፣ ይኽ ሁኔታ ሲከሰት የሚያስከትለውን የጋራ ኅልውና እጦትና የትርምስ አደጋ ከአገራችን በአስቸኳይ ለማስወገድና ፈር እየለቀቀ ያለውን የዴሞክራሲ ሂደት መልክ ማስያዝ ስለሚቻልበት ሁኔታ ለመምከር፤

ለ) በእንደዚህ ያለ ስብስብ የድርጅቶች ሁሉ የጋራ መጨረሻ ግብ ሆኖ ሊወሰድ ስለሚገባው በአገራችን ሁሉን-አቀፍና አግላይነት የሌለው የዴሞክራሲያዊ የሽግግር ሂደት እውን ስለሚሆንበት አዲስ ትልም ማውጣት፤
ናቸው።

ስለሆነም ለነዚህ የጋራ አሳሳቢ ጉዳዮች የሚደረግ መሰባሰብ የፖለቲካ ድርጅቶችን ብቻ ሳይሆን የሲቪክና የሙያ ማኅበራት፣ የኅብረተሰቡን ልዩ ልዩ ጥቅሞችና እምነቶች ለማስጠበቅ የቆሙ ስብስቦች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ ምሁራን፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ገበሬዎች፣ ወታደሮች፣ የሐይማኖት ተቋማት፣ ወዘተ... የሚወከሉበትና ሙሉ ተሳትፎ የሚያደርጉበት ጉባዔ እንዲሆን ያስፈልጋል። በዚኽ ረገድ በአንዳንድ ድርጅቶች (ድርጅታችንን ጨምሮ) ብዙ ጥረት ቢደረግም እስካሁን በተደረጉ የጋራ መድረክ ፈጠራ ሙከራዎች ምናልባትም አማራጭ ኃይሎችን ከፈጠረው የግዮን ሆቴል ስብሰባ በስተቀር እነኝኽን ክፍሎች ሙሉ ተሳታፊ ያደረገ ስብሰባም ሆነ ጉባዔ አልተደረገም።

ይኽን በተግባር ለመፈጸም በአስቸኳይ የጎንዮሽ ምክክር ተደርጎ አንድ ከሁሉም የተውጣጣ አስተናባሪና አሰባሳቢ <u>የጋራ አካል</u> (ኮሚቴ) መቋቋም ይኖርበታል። ስለዚህ ጉዳይ ድርጅታችን ከአንዳዶች ጋር ምክክር ሲያደርግ ቆይቷል፤ ቶሎ ተፈጻሚ እንደሚሆንም እምነታችን ነው። የዚኽን አካል ተግባርና ተልዕኮ በሚመለከት ያለንን አሳብ በጽሑፍ እናስተላልፋለን።

ለ) <u>ኢሕአዴግና አጠቃላይ የአገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች ምን ማድረግ ይኖርባቸዋል (ይጠበቅባቸዋል)?</u>

ከላይ በተጠቀሰው መንፈስ የተቃዋሚው ክፍል ተሰባስቦ በአገራችን የሰከነ ሽግግር እንዲደረግ ከወሰነ፣ ገዥው ፓርቲ በዚኽ አገራችንን ወደ አስተማማኝ የዴሞክራሲ ሥርዓት ምሥረታና የልማት አቅጣጫ የሚያስይዝ የጋራ ጥረት ከጅምሩ አካል እንዲሆን ጥሪ ሊቀርብለትና <u>ትርጉም ያለው ድርድር</u> ሊደረግ ይገባል። በእርግጥ በኢሕአዴግ በኩል እስካሁን ለእንደዚህ ዓይነት በጎና ገንቢ አቀራረብ ካለው አሉታዊ አመለካከትና የቆየ ግትር አቋም ታሪኩ በመነሳት አሁንም ተመሳሳይ የእምቢተኝነት መልስ ስለሚሰጥ ጨርሶ አያስፈልግም የሚል ክርክርና ተቃውሞ ከብዙ ድርጅቶች ሊቀርብ ይችላል። በኛ በኩል ይኽንን ነጥብ በተመለከተ ለምንና እንዴት እንደሚቻል በስብሰባው ላይ በምናቀርበው ሰነድና በሚደረገው የፊት-ለፊት ውይይት ለማሳመን እንችላለን የሚል እምነት አለን።

ከወዲሁ ግን አንድ ነገር ማለት እንችላለን፡፡ የመጀመሪያው እንደታሰበው ተግባራዊ ከሆነ ለሁለተኛው ከሚታሰበው በላይ በር ከፋች እንደሚሆንና እንዲሆንም ማድረግ ይቻላል ብለን እናምናለን፡፡

*ትርጉም ያለው ድርድር ስንል ምን ማለታችን ነው?*

እስካሁን ድረስ በኢሕአዴግና በተቃዋሚው የተደረጉ ድርድሮች እኛ በምናስበው መልክ ትርጉም ያላቸው ናቸው ብለን አናምንም፡፡ ይኸም የሆነበት ምክንያት በአብዛኛው በኢሕአዴግ ግትር አቋም ቢሆንም የተቃዋሚው ክፍል ባሳየው አጠቃላይ ድክመት እንደሆነ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ድርድር ለመደራደር ያኽል ብቻ የሚደረግ ይስሙላዊ እርምጃ መሆን የለበትም፡፡ ትርጉም ያለው ድርድርም ሆነ በእሱ አማካይነት የሚመጣ ሰላም የሚገኘው ሁሉም ሰላም ፈላጊ ሲሆን ብቻ እንደሆነ የታወቀ ነው፡፡ ለዚኽ ደግሞ በተፃራሪ ኃይሎች መኻል ተከባብሮ የመፈላለግና ለመቻቻል ፈቃደኛ መሆንን ይጠይቃል፡፡ ይኽ "መፈቃቀድ"፣ "በቋንቋ መግባባት" እና ሰላምን የመፈለግ አዝማሚያ በሁሉም ዘንድ የተሻለ ትኩረት የሚሰጠው በተፃራሪ (በተፋላሚ) ኃይሎች መኻል ያለው አሰላለፍ ሚዛናዊነት ሲስተካከል ብቻ እንደሆነም ግልጽ ነው፡፡ ሁሉም የሚፈልገውን ሰላም በማምጣቱ ላይ በአቻነት መደራደር ወሳኝነት አለው፡፡ አሁን በአለው ሁኔታም ሆነ በአጠቃላይ አምባ-ገነኖች ጋር የሚደረግ ፍልሚያ ደግሞ ይኽ "መፈላለግ"ና አስተሳሰብ በበጎ ፈቃድ የሚገኝ ሳይሆን የ<u>አስገዳጅነት</u> ሁኔታ ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ የኢሕአዴግ መሪዎችም በድርድር ስለሚመጣ ሰላም ሊያስቡ የሚችሉት <u>አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠር ብቻ ነው፡፡</u> ከላይና በበጎው መንገድ ሲታይ የሁላችንም የሆነችው ውድ አገራችን ያለችበት አደጋ ሁሉም ክፍሎች (ተቃዋሚውም ሆነ ገዥው ፓርቲ) በጉዳዩ አብረው እንዲመክሩና የጋራ መፍትኄ እንዲፈልጉ በቂ አስገዳጅነት አለው አይደለም ወይ፣ ከዚኽ የበለጠ የሁሉንም የጋራ ኀልውና በቀጥታ የሚነካ  ምን ሌላ አስገዳጅነት ያለው ነገር ሊኖር ይገባል? ሊባል ይችላል፡፡ አዎን በበጎ ከታየ ትክክል ነው ሁሉም ተጎጅ የሚሆንበት አገርና ሕዝብን ወደ አጉል አቅጣጫ የሚወስድን ሁኔታ ሁሉም በጋራ ተረባርቦ ከማዳን የበለጠ አስገዳጅ ሁኔታ አይኖርም፡፡ ሆኖም ይኽ በጎ እይታ በሁሉም ዘንድ ስለሌለ ነው አደጋውን ሁሉም እንዲያይ ተጨማሪ አስገዳጅነትን ያስፈለገው፡፡ ይኽን ለማድረግ አለመድፈር ደግሞ አገርን ወደ መንኮታኮትና ሕዝብን ወደ ትርምስና የባሰ ሰቆቃ የሚጨምር ሁኔታን መጎተትና በዚኽም የጋራ ተያይዞ ጥፋትን ብቻ መጋበዝ እንደሆነ ሁሉም ሊገነዘበውና ከኅሊናው ጋር ሊሟገትበት ይገባል፡፡ ነገሩ እንዲህ ቀላል አለመሆኑ ነው ሁሉም ከልብና ከምር ሊያስብበት ይገባል የምንለው፡፡ ያለው በሕባችንና በአገር ላይ ያፈጠጠ ችግር ለሁሉም ልቦና ሰጥቶ ትርጉም ወዳለው ድርድር ካላመራ ሕዝብን ማዕከል ያደረገ በሚገባ የተደራጀ፣ የተቀናጀና ቀጣይነት ያለው ሰላማዊ እንቅስቃሴ በማድረግ የሚያሳምን <u>አስገዳጅ ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል፡፡</u>
በእርግጥ አንዱ ጎን ብቻ ገዳይ፣ ሌላው ሟች፤ አንዱ ውሃ፣ ሌላው እሳት፤ አንዱ ለማኝ፣ ሌላው ተለማኝ፤ አንዱ ሰላም ፈላጊ፣ ሌላው የማይፈልግና ነፋጊ፤ ወዘተ... በሆነበት ያልተማዘነ አሰላለፍ በመከባበርና በእኩልነት መንፈስ እርባና ያለው ድርድር ማድረግና ዘለቄታዊነት የሚኖረው ሰላም ለማስገኘት ቀላል ነው ከሚል ግብዝ አስተሳሰብ ተነስተን በቀቢፀ-ተስፋ አይደለም ይኽንን አሳብ የምንገፋው፡፡ ቁም ነገሩ የእልህና የተያይዞ-ጥፋት መንገድን ለመያያዝ ከመታሰቡና ከመደገሳችን በፊት ከአሁን በፊት ባልተደረገ መልክ ጠንካራ ሙከራ ማድረግ ይቻላል ከሚል እምነት ነው፡፡ ጥረቱ ሁሉ ይኽንን <u>በመከባበር ላይና አገርንና ሕዝብን ቅድሚያ የሰጠ</u> የእኩልነት (የአቻነት) ትርጉም ያለው የድርድር ሁኔታ ለመፍጠር ነው፡፡ ይኸም ጥረት ሁል-አቀፍ መሆን የሚገባው ለዚኽ ነው፡፡ አሁን ለጊዜው ለአንዳንዶች፣ በተለይም በአንፃራዊ ምቾት ላይ ለሚገኙና ከአደጋው የራቁ መስሎ ለሚሰማቸው በገዥው ፓርቲ በኩል ላሉ ወገኖች፣ ያለው ችግር እነሱን እንደማይመለከት አድርገው ሊቆጥሩት ይችላሉ፡፡ ሆኖም ሁሉም ልብ ሊለው የሚገባ ጉዳይ በአገራችን ላይ ያንዣበበው ችግር የተቃዋሚውን ወይም የኢሕአዴግን አባላት ብቻ እየነጠለ የሚያጠቃ አይሆንም፡፡ ሁኔታው ከቁጥጥር ውጭ ከሆነ ሁሉንም የሚለበልብ የቋያ ሰደድ እሳት

እንደሆነ ይገነዘቧል፡፡ ደግሞስ የሕዝብ ትርምስ የተከሰተባቸው አገሮች ውስጥ ተጠቃሚ የሆነ ክፍል፣ ቢያንስ ጉዳት ያልደረሰበት ወገን ኖሮ ያውቃል ወይ?

ስለሆነም በተቃዋሚው ወገን ሲገፋና ያላቋረጠ ጥረት የተደረገበትንና እየተደረገበት ያለውን፣ ለሕዝባችን አስተማማኝ ሰላምና ለአገራችን ዘለቄታዊ መረጋጋት ለማስገኘት አስፈላጊ የሆነው የእርቅና የሰላም ሂደት እውን እንዲሆን የሚያስችል ጋባዥ ሁኔታን ለመፍጠርና ለማመቻቸት በሚደረግ ጥረት የሁሉም መተባበር የሚያስገኘው የጋራ ጥቅም የሚያጠያይቅ አይሆንም፡፡ ለውጥ ለማምጣት የሚታገሉ ወገኖች ይኽንን ሃቅ ተረድተው ተከባብረውና ተግባብተው አገራችን በእርቅና ሰላም ላይ የተመሠረተ የመልካም ሥርዓት ባለቤት እንድትሆን አጠቃላይ ውድቀት ከመድረሱ በፊት ከወዲሁና በአስቸኳይ ሰፊ ምክክር ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

በተቃዋሚው ወገን በተሰለፍን ኃይሎች በኩል ካሉብን ድክመቶች አንዱ የምንቃ-ወመው ክፍል የሚሠራው ትክክል አይደለም፣ ፀረ-ሕዝብ ነው፣ ፀረ-አገር ነው፣ ወዘተ.... ከሚለው የተለመደ ፍረጃ አለፍ ብለን የምንቃወመው ክፍል በተለይ መሪዎቹ አገርንና ሕዝብን አይጠቅምም፣ ትክክል አይደለም ብለን የምንቃወመውን የሚሠሩት ከምን ፍልሥፍና ተነስተው ነው? ለሚለው ጥያቄ ጥናት ላይ የተመሠረተ በቂ ምላሽ ያለን አይመስለንም፡፡ መቸም አንድ ሰው ወይም ቡድን ዝም ብሎ ተነስቶ አንድን አገር ያውም አስተዳድራለሁ የሚለውን አገርና ሕዝብ የሚጎዳ ሥራ ለመሥራት ሣይንሳዊ ምክንያት ሊኖረው ይገባል፡፡ በተጨማሪም ትኩረትን በየወቅቱ በሚከሰቱ አናሳ ጉዳዮች ላይ እንጂ ለሕዝባችንና ለአገራችን ዘለቄታዊነት ባላቸው ዓይነታ ጉዳዮች ላይ አለማድረግ፣ ትግሉን ያዝ-ለቀቅ ባለ ይዞታ ማስተናገድና <u>የአጀንዳ ቀጣይነት እጥረት</u> ተቃዋሚውን ያለ ቅጥ ተጠናውተውታል፡፡ ይኽም ተቃዋሚው ክፍል ከተሟዘዘ ተከላካይነት እንዳይወጣ አድርጓል፡፡

ያለፈውን መርሳትም ባይሆን ያለፈ የቅርብም ይሁን የሩቅ በደልና ቅሬታ ይቅር ማለት መቻል ለግል ሕይወት ከሚሰጠው የኅሊና እርካታ በላይ የወደፊት ትውልዶችን ሕይወት አሁን ያለው ትውልድ በሚገኝበትም ይሁን ቀደም ሲል የነበሩ ትውልዶች በሄዱበት አሉታዊ አስተሳሰብ ከሚወልደው ከርስ በርስ አለመተማመን፣ አለመከባበር፣ በበጎ ካለመተያየትና እንደ አንድ አገር ዜጋ ካለመተሳሰብ ኅፀጽ የፀዳ መሆን እንደሚያስችል ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ ቂምን አዝሎና በግልጽም ባይሆን በውስጥ በጠላትነት እየተያዩ ለመቀጠል መሞከር እሳት በጉያ ዓይነት ውሎ አድሮ እራስንና ኅብረተሰብ ጊዜንና ሁኔታን እየጠበቀ ለሚከሰት አሰቃቂ አደጋ እንደማመቻቸት ይቆጠራል፡፡ በቂም-በቀል ተመርቶ በዳይ በሆነው ሰው ወይም ክፍል ላይ ከሕግ ውጭ በሆነ መንገድ አፀፋ ለመመለስ ማሰብ ምናልባት ለአፀፋ መላሹ ቢበዛ ጊዚያዊ እርካታን ሊሰጥ ይችል ይሆናል፡፡ <u>ያ የሚሆነው ግን በወደፊት ትውልዶች ተሳስቦና ተከባብሮ አብሮ የመኖር የጋራ ሕይወት ከፍተኛ ኪሳራ እንደሆነ ምን ጊዜም ሊረሳ አይገባውም፡፡</u>

ቂምን አዝሎ መኖር የመበቃቀል አባዜ አዙሪቱ እየተደራረበ እንዲቀጥልና የኅብረተሰብ የተረጋጋ ሰላምና እድገት ዓይነታ እንቅፋት እንደሆነ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም ወደፊት ኅብረተሰባችን ዘላቂነት ያለው ሰላምና የተደላደለ ሕይወት እንዲኖረው የፈለገ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከፍ ሲል እንደጠቀስነው በራሱ ላይ መሠረታዊ የሆነ ለውጥ ማምጣትና እራሱን ከቂም-በቀል ማጽዳት ያስፈልገዋል፡፡ <u>ኅብረተሰብን ወደ-ተሻለ ሥርዓት ለመቀየር የሚደረገው ትግል ቅድሚያ በራስ ላይ በሚደረግ አብዮት መጀመር ይኖርበታል፡፡ ይቅር ባይነት ታላቅነትንና ብስለትን እንጂ ድክመትን አያሳይም፡፡</u> የኅሊና ነፃነትን ስለሚያጎናጽፍም የሚጠቅመው ከማንም በላይ እራስን ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ለአገርና ለቀጣይ ትውልዶች ሲባል የሚደረግ ይቅርታ ውጤቱ የበለጠ እንደሚያረካ አጠራጣሪ አይመስለንም፡፡

## **VI. ማጠቃለያ፤**

*ብሔራዊና ሕዝባዊ ዓላማ ያለው ድርጅታችን ሕዝባችን ለዘመናት አይከፍሉ መስዋዕትነት የከፈለበትና እየከፈለበት ያለውን የአንድነት፣ የፍትኅ፣ የዴሞክራሲና የእኩልነት ትግል በአስተማማኝ እውን እንዲሆን የበኩሉን ታሪካዊ ድርሻ ለመወጣትና አስተዋጽዖ ለማድረግ ይታገላል። በተገቢና በእርግጠኝነት ያለመው ግብ ላይ ለመድረስ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ እምነቱም ሆነ አሠራሩ በአባላቱ የአንድነትና የፍትኅ የጋራ ራዕይ ላይ የተመሠረተ ነው። ድርጅታችን በንቅናቄ ደረጃ የሚታገለው ለድርጅታዊ የፖለቲካ ሥልጣን የሚደረግ አዘቦታዊ የፖለቲካ ድርጅት አካሄድን በመከተል የአገራችን ሁለንተናዊና ዙሪያ-ጥምጥም ችግሮችን በቀላሉ መፍታት ይቻላል የሚል እምነት ስለሌለን ነው። የዚያ ዓይነት የፖለቲካ ድርጅት አካሄድ የሚጠይቀው ሁኔታ በአገራችን አለ ብለን አናምንም። ያ ማለት ግን በአሁኑ ጊዜ የፖለቲካ ሥልጣንን ዓላማቸው በማድረግ የተደራጁትን ለመንቀፍ እንዳልሆነ ግልጽ ማድረግ እንፈልጋለን። የኛ ትግል አገራዊ አንድነትን፣ ፍትኅንና እኩልነትን ማዕከል ባደረገ መልኩ አገራችንን ካንዣበበባት አደጋ ለማዳንና ዘለቄታዊነት ያለው ሰላምና መረጋጋት ኖሮ ለዚያ የፖለቲካ ድርጅቶች የሥልጣን ፉክክር አመች ሁኔታ እንዲፈጠር ለማድረግ ነው።*

*ከተማሪው እንቅስቃሴ ወዲህ አነሳሱ በቀና መንፈስ ቢሆንም እንዲሁ ደፈናዊ በሆነ መልኩና ያለምንም ማጠየቂያ "የብሔር/ብሔረ-ሰብ ጥያቄ የዴሞክራሲ ጥያቄ ነው" በሚል አመለካከት የተቀነቀነውን አስተሳሰብ በተለይም ወጣቱና ትምሕርት የቀሰመው ክፍል እንደ ተራማጅነት ፈሊጥ እንዲሁ በሌጣው መቀበሉ በሕዝባችን አንድነታዊ ትስስር ላይ ያደረሰው የሰመመ ሥነ-ልቦናዊ ሰለባ የበርካቶች ትኩረትና ቅድሚያ ለአጠቃላዩ ሳይሆን "የኔ" ለሚሉት ብቻ እንዲሆን አድርጓል። ከዚኽም አንደምታዊ እምነት በመነጨ የተደራጁ የየአካባቢ እንቅስቃሴዎች፣ እነዚኽ እንቅስቃሴዎችም በመደብ ሳይቀር በአገር ደረጃ ለአንድነት በተሰለፉ ድርጅቶች ላይ የነበራቸው (ያላቸው) አቋምና የወሰዱት እርምጃ ሲታይ ዜጎች እንደ አንድ አገር ሕዝብ ለጋራ ችግሮቻቸው በጋራ መታገል ላይ ቀጥተኛ ጫና ማሳደሩ ግልጽ ነው። ይኽም ለአገራችን መሠረታዊ የጋራ ችግሮች መፍትኄ ፍለጋ ላይ እስካሁን የዘለቀና ወደ-ፊትም የሚቀጥል ችግር ፈጥሯል። እዚኽ ላይ ግልጽ እንዲሆን የምንፈልገው ነገር ልዩ ልዩ ግፎችን ለመቃወምና በአገራዊ አንድነት ማእቀፍ ሥር ለእኩልነት የተደረጉ ትግሎችን በጅምላ ለመኮነን ሳይሆን በተለይ ጎሣን፣ ቋንቋን፣ ወዘተ... መሠረት ባደረገ መልኩ ከሌላው ተለይቶ መደራጀት ሕዝባችን ለጋራ ችግሮቹ እንደ አንድ አገር ሕዝብ በአንድ ላይ ቆሞ እንዳይታገል ያደረሰውንና የሚያደርሰውን አሉታዊ ጫና፣ ይኽም ለአምባ-ገነንና የከፋፍለህ ግዛ መሰሪ የአገዛዝ ሥርዓቶች ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ለማመላከት ነው። ያ ዓይነት አሰላለፍ የአገራዊ አንድነቱን እምነት እጅጉን ሸርሽሮታል፣ እስከቀጠለ ድረስም ሕዝባችንን የበለጠ ያራርቀዋል ማለት ይቻላል።*

*ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ብሔረሰቦችና ልዩ ልዩ እምነቶችን የሚከተሉ ዜጎች ያሏት አንድ አገር መሆኗንና የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ሕዝብ መሆኑን ሃቅ በማያሻማ መንገድና በግልጽ አስቀምጦ ትግሉ የጋራ ጠቀሜታ ላለው የተሻለ ፍትኃዊና ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እንደሆነ አለመቀመጡ ወይም በዚህ መልክ የተደራጀ ኃይል ለሕዝባችን በአማራጭነት አለመቅረቡ፣ ያሉትም ቢሆኑ የአንድነት ዓላማን ያራመዱት ደፈር ባለ መልኩ ሳይሆን በተቅለሰለሰና አገም-ጠቀም ባለ መልኩ በመሆኑ የአገራዊ አንድነት ትግሉን በእጅጉ ጎድቷል። ይኽም በመሆኑ አብዛኞቹ ኅብረ-ብሔረሰብ ድርጅቶች የአካባቢም ይሁን የጎሣ ጥያቄ ያነሱ ድርጅቶችን አጋርነት ለመፈለግ የሽንገላ ፖለቲካን እንዲከተሉ አድርጓል። የሽንገላና የማባበሉ ፖለቲካም በአንድ በኩል የጎሣም ይሁን የአካባቢ እስከ መገንጠል የደረሰ ጥያቄ ያነገቡ ክፍሎች በዚሁ መሥመር ደፍረው እንዲገፉበት በተዘዋዋሪ ሲያበረታታ ወይም እነዚህ ክፍሎች ቆምንልህ ለሚሉት ወገናችን ጠንካራ አማራጭ ሆነው መቅረብ ባለመቻላቸው የአንድነት ኃይሉ ትግል እንዲሸረሸርና*

እንዲሽመደመድ በማድረግ ጣምራና ተደጋጋፊ ጉዳቶችን አስከትሏል፡፡ በእርግጥ የቅርብ ሆኑ የሩቅ ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች እንዲሁም አንዳንድ ጥራዝ-ነጠቅ "ተራማጅ" ነን ባይ ተመፃዳቂዎች ጭምር እንደዚህ ዓይነቱን ብሔረተኛ ሕዝባዊ ኃይል በበጎ ዓይን ሳይመለከቱት ቆይቷል፡፡ አጥብቀው ይፈሩታል፣ ብቅ ሲል ትምክህተኛ፣ የድሮ ሥርዓት ናፋቂ፣ ወዘተ… በማለት ቶሎ ጭንቅላት ጭንቅላቱን ይሉታል፡፡ የወታደራዊ ደርግ አገዛዝም በአብዛኛው በተከተለው ርዕዮት ምክንያት እንደ ኢዴኅ ዓይነቱን አገራዊ አቋም ያለው ድርጅት በዋና "የመደብ" ጠላትነት ማየቱና ማተኮሩ የፀረ-አንድነት ኃይሎች እንዲጎለብቱ በተዘዋዋሪ መንገድ አግዟል፡፡

ኢትዮጵያዊ መሆን ኩራት፣ ክብርና ፀጋ እንደሆነ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በእኩልነት መኖር የሚችልና የሚገባው እንደሆነ፣ ኢትዮጵያችን በፋብሪካ እንደተሠራ እቃ የምትፈታታ ሳትሆን በአንድ ክር እንደተሠራ ሹራብ የተሳሰረ ሕዝብ ያላት አገር እንደሆነች፣ አገራችን የማንም ተናጠል ጎሣም ሆነ ብሔረሰብ የግል ንብረት ሳትሆን የሁሉም ዜጎቿ የጋራ መስዋዕትነት፣ ተጋድሎና ተስፋ ድምር ውጤት እንደሆነች፣ ለዚች አገር አንድነት መቆም የግለሰብ ዜጎችንም ይሁን በአገራዊ አንድነት ማእቀፍ ውስጥ የወል መብቶችን የተሻለ የሚያጠናክር እንጅ የሚፃረር እንዳልሆነ በተገቢ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ የኢትዮጵያ አገራዊ አንድነት ለሕዝባችን ችግር፣ መከራና ድህነት ምክንያት ሊሆንም ሆነ ተጠያቂ ሆኖ ሊቀርብ ፈጽሞ አይችልም፡፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር የሆነችው ኢትዮጵያ ሳትሆን አድልዖአዊና የችግር ቋት የሆኑ አምባ-ገነን ሥርዓቶች ናቸው፡፡ ማንም ኢትዮጵያዊ በአገሩ አንድነት አቋሙ ሊኮራ እንጅ ሊሸማቀቅም ሆነ በስመ ተራማጅነትም ይሁን በጋራ ትግል ስም አንድነትን ለሚፈታተኑ ሌሎች ኃይሎች ሊያጎበድድ ወይም አቋሙን ሊያለሳልስ አይገባውም፡፡ የኦሮሞውም ሆነ የአማራው፣ የትግሬውም ሆነ የሶማሌው፣ የጋምቤላውም ሆነ የጉራጌው፣ የሃድያውም ሆነ የወላይታው፣ ወዘተ… ሙሉ መብት ያልተከበረባት፤ ጎሣን፣ ቋንቋን፣ ወዘተ.. መሠረት ባደረገ ይዞታ አንዱ የበላይ ሌላው የበታች፣ አንዱ ዓይነታ ሌላው ሁለተኛ ዜጋ ሆኖ የሚታይባት ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ልትሆን አትችልም፡፡ ለትግሬው መብት መከበር መታገልና መሰዋት ያለበት ትግሬ፣ ለኦሮሞው መብት መከበር መታገል ያለበት ኦሮሞ፣ ወዘተ… ብቻ መሆን አያስፈልግም፡፡ የለበትምም፡፡ ኦሮሞውም ሆነ ሌላው ኢትዮጵያዊ፣ ለኦሮሞው መብት መከበር አማራው ሆነ ሌላው፣ ለጉራጌው መብት መከበር ትግሬው ሆነ ሌላው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ለሌላው ወገኑ መታገልና መስዋዕት መሆን <u>መደበኛ እምነት</u> መሆን ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም የትግሬው መብት ካልተከበረ፣ የሶማሌው ኢትዮጵያዊ፣ የሃድያው፣ <u>የማንኛውም ጎሣ አባል ወይም የሌላው ቋንቋ ተናጋሪ ኢትዮጵያዊ መብት ካልተከበረ የማንም መብት ሊከበር አይችልም፡፡</u> የአንዱ መብት መጣስ የሁሉም፣ የአንዱ ብሶት በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል ለሚገኝ ዜጋ ሁሉ እንደሆነ ግልጽ ሊሆን ይገባል፡፡ ኢትዮጵያውያን በአንድነትና በጋራ በከፈሉት መስዋዕትነት አገራችንን ከኤርትራ በስተቀር ከቅኝ ገዥዎች ቅርምትና ባርነት አትርፈው የነፃነት አምባ እንድትሆን አስችለዋል፡፡ ይኸ የውጭ ቅኝ ገዥን አሳፍሮ የመለሰና የአገሪቱን ነፃነት ጠብቆ ያቆየ የሕዝብ አንድነት፣ በተመሳሳይ ትብብሩና በተለመደው አንድነቱ፣ ለዘመናት በጫንቃው ላይ ያንሰራፉ የፍትኅ መጉደልን፣ እርሃብን፣ መሃይምነትን፣ ድህነትን፣ አምባ-ገነን ሥርዓትንና ኋላ-ቀርነትን የማያስወግድበት ምንም ዓይነት ምክንያት አይኖርም፡፡

በወል መብት ስም ጀምሮ ተስፈንጥሮ የመገንጠል ጥያቄ ካቀረበውም ይሁን የዜጎችን እኩልነት በሃቅ ሳይቀበል በተድበሰበሰ መልክ በስም አንድነትን ሆኖም ግን በተግባር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሕዝባችንንና የአገራችንን ዘለቄታዊ ሰላምና አንድነት ከሚፃረሩ ኃይሎች ጎራ ከቆሙ ክፍሎች ጋር ሊሰለፍ የማይችለውና የማይፈልገው በቁጥሩ እጅግ አብላጫ የሆነውና በልዩ ልዩ ምክንያቶች ታፍኖ ያለው በማዕከል የሚገኘው አገር-ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሊሰባሰብና ሊታገልበት የሚችል፣ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ቤቴ ሊለውና የእኔ ነው ብሎ ሊቀበለው የሚችል ሚዛኑን የጠበቀ የማዕከል ኃይል መኖር ለአገራችን አስፈላጊ ነው፡፡ በአለው የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ብዙ ኅብረ-ብሔረሰብና አገራዊ አቋም ያላቸው ድርጅቶች ነበሩ፣ አሁንም አሉ፡፡ ሆኖም ግን አንዳቸውም በግልጽና ነጥሮ በወጣ

ሁኔታ አገራዊ አንድነትን ዋና እምነታቸውና መመሪያቸው ያደረጉና ይኸ የአገር አንድነት አቋም ተግባራዊ እንዲሆን በሁለንተናዊ መልኩ የሚታገሉ ናቸው ማለት አያስደፍርም፡፡ አንድም በሰከነና በተደላደለ የአገር ሁኔታ ሊካሄድ በሚገባ ሥልጣንን ብቻ አንጋጥጦ በሚመለከት የፓርቲ ፖለቲካ የተጠመዱ ናቸው ወይም አገራዊ አንድነት ላይ ያላቸው አቋም በሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ "የዚኸ አካባቢ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን መብት አለው፣ በአገሪቱ ያለው ዓብይ ቅራኔ በብሔር/ብሔረሰብ መኻል ያለው ነው፣ የእኛ ጥያቄ ካልተፈታ ጉድ ይፈላል፣ ወዘተ..." ሲባል በአንዳንድ ወገኖች በኩል ይሰማል፡፡ ሃቁ የት ላይ ነው? ለመሆኑ መገንጠል መብት ነው ብሎ በደፈናው ማሰብና መቀበል ትክክል ነወይ? በአገሪቱ አንድ አካባቢ ያለ ሕዝብ ስለ ወደፊት ዕድሉ ሕዝበ-ውሳኔ ይስጥ ሲባል አጠቃላዩ የአገሪቱ ሕዝብስ ስለጠቅላላ አንድነቱ ሕዝበ-ውሳኔ የመስጠት መብት የለውም?

ከልዩ ልዩ እራሳቸውን የቻሉ አገሮች በግድም ይሁን በውድ ተዋኀደው የተፈጠረ አዲስ አገር ለምሳሌ እንደ ቀውድሞ የሶቪየት ኀብረት፣ እንደ ቼኮዝሎቫኪያ፣ ወዘተ.. ዓይነት አገሮች ይኸ "የየአካባቢው" ውሳኔ ምናልባት ተገቢነት ሊኖረው ይችላል፡፡ እንደ አዲስ እንፍጠረው ካላልን በስተቀር ይኸ ሁኔታ በእኛ አገር የለም፡፡ ሌላው ቀርቶ የኢትዮጵያ መሠረት የሆነችው ኤርትራ ከእናት አገሯ ከኢትዮጵያ ተለይታ በባዕድ እጅ የቆየችው ከረዥሙ የአገራችን ታሪክ አንፃር ሲታይ በጣም ለአጭር ጊዜ ነው፡፡ ኢትዮጵያ አሁን የታሪክ ከላሾች እንደሚሉት የዛሬ መቶ ዓመት ተጠፍጥፋ የተሠራች አገር አይደለችም፡፡ ታሪክ መጠቀስ ሲኖርበት ደግሞ በቁንጽልና ባልሆነ መንገድ መሆን የለበትም፡፡ ታሪክ ትላንት አልጀመረም፡፡ ስለዚህ ስለ ትላንትና ካወራን ትላንት ደግሞ የራሱ ትላንት አለውና ያንንም ማገናዘብ ይገባል፡፡ በአንዳንድ የአገሪቱ ክፍሎች እንደየአካቢው ሁኔታ የየራሳቸው አውራም ንጉሥም የነበራቸውና እነዚህ ግን ለማእከላዊም መንግሥት (ንጉሠ-ነገሥት) ታማኝነት የነበራቸው ነበሩ፡፡ በተለይ በአፍሪቃ ምድር የመጀመሪያው የጀሃድ ጦርነት የሆነውን የግራኝ መሐመድ የአሥራ-አምስት ዓመት ተኩል አውዳሚ ዘመቻ ተከትሎ አገራዊ ማዕከላዊነት ሲላላ፣ ኢትዮጵያውያን በየአካባቢያቸው ተለያይተው እንዲያድጉና ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን የየራሳቸውን መንገድ ተከትለው እንዲቆዩ መደረጉ ይታወቃል፡፡ ያ ታሪካዊ ክስተት ባስከተለው ሁኔታ ምክንያትም ከአገራችን የረዥም ዘመን ታሪክ አንፃር ለአጭር ጊዜ ማዕከላዊ መንግሥት በተወሰኑ የአገሪቱ ክፍሎች በተለይም በመኻሉና በሰሜኑ በኩል ተወስኖ እንዲቆይ ሆኗል፡፡ ይኸ የትላንትና ክስተት ግን በምንም መንገድ ሕዝባችን ከትላንትና ወዲያ የነበረውን ትስስርም ሆነ አገራዊ አንድነታችን በቅርቡ በተለይም በአፄ ምኒልክ ዘመን የተጀመረ ተደርጎ እንዲታይ ሊያደርገው አይችልም፡፡

ሕዝባችን ከጥንት ጀምሮ በየአካባቢው የተለያዩ ቋንቋዎችን ሲናገር የኖረና ልዩ ልዩ ባህሎችንና ልማዶችን የሚከተል ሕዝብ እንደሆነ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ በአንድ አካባቢ ብቻ ሳይሆን በአንድ አውራጃ ወረድ ብሎም በአንድ ወረዳ ከአንድ በላይ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ዜጎች መኖር ለአገራችን አዲስ አይደለም፡፡ በጭልጋ፣ በወልቃይት፣ በጠለምት፣ በዋግ፣ በየጁ፣ በሰላሌ፣ በሐረር፣ ወዘተ... ፡፡ ለነገሩ የአንድ አገር ዜጎች አንድ ዓይነት ቋንቋ ተናጋሪዎች መሆን አለባቸው ከተባለ በዓለም ላይ ከሽሕ በላይ አገሮች ሊኖሩ በቻለ ነበር፡፡ አገራዊ አንድነት እያንዳንዱ የቋንቋ ቡድን መክሮና ዘክሮ "በፈቃዱ" መሆን አለበት ከተባለም እንዲሁ አሁን በዓለም ላይ ካሉ አገሮች መኻል በዚህ ዓይነት የተቋቋመ አገር አይገኝም፡፡ ይኸ አስተሳሰብ ሁለት መሠረታዊ ችግሮች አሉት፡፡ አንደኛ በዚኸ ስሊት ከአንድ በላይ ኀብረ-ብሔረሰብ ያለው ወይም ብዙ ቋንቋ የሚናገሩ ዜጎች ያሉት አገር ላይኖር ነው፡፡ ሁለተኛ የግለሰብ ነፃነትን ፈጽሞ የሚፃረርና ለወል ፍላጎትና ፈቃድ ተገዥ የሚያደርግ አምባ-ገነናዊ አስተሳሰብ ነው፡፡ የግለሰብ ሙሉ ነፃነት የተከበረበትና መብትና ፍላጎት የተጠበቀበት ሥርዓት በአንድ አገር እንዲሰፍን ከተደረገ እያንዳንዱ ዜጋ የመሰለውን ቋንቋ የመናገርም ሆነ ያሻውን ባህል የመከተል መብቱ የተረጋገጠና የተጠበቀ ይሆናል፡፡

ስለዚህ በግለሰብ መብቶች መከበር ላይ የተመሠረተ አገራዊ አንድነት አንዳንድ የወል (የቡድን) መብት ቆመናል በሚሉ ክፍሎች እንደሚነገረው በግለሰብ መብት መከበር አልፎ

የሚሄድንና የሚገለጸውን የቡድን መብት <u>የጠና መሠረቱ</u> ይሆነዋል እንጂ በምንም መልኩ ሊሽረው ወይም ሊያደበዝዘው አይችልም።

በመሠረቱ የዜጎች የግለሰብ መብቶች በታፈኑባቸውና በተጣሱባቸው አገሮች፣ ይበልጥም በደሉ ቋንቋና ሐይማኖትን በተመረኮዘ ሁኔታ ሲከሰት የመገንጠል ጥያቄ የሕዝብ ጥያቄ ሆኖ ይንፀባረቃል። በአገራችን በኢትዮጵያ ሁኔታ ጭቆናውም ሆነ የመብት እረገጣው የተወሰኑ ቋንቋ ተናጋሪዎችን እየለየ ሆን ተብሎ በስሊት የተደረገ ነው ማለት አይቻልም። የግለሰብ መብቶች በደፈናው በመላ የአገሪቱ ዜጎች ላይ ተፈጽሟል። እየተፈጸመም ነው። በእርግጥ እኩልነት ያልነበረበትና ብዙ በደሎች የተፈጸሙበት፤ የሁሉም ባህሎች፣ ቋንቋዎችና ልማዶች እንዲያድጉ ዕድል ያልተሰጠበት፣ ወዘተ.. ሁኔታ እንደነበር ማንም ሊሸፋፍን ወይም እንዳልነበር ሊቀጥር አይችልም። ያ ግን በኋላ-ቀር የአገዛዝ ሥርዓቶች በመላ ሕዝቧ ላይ የተፈጸመ ድርጊት ነው። ያ በሕዝብ ላይ የተፈጸመ በደልና የዜጎች እኩልነት አለመጠበቅ ግን በምንም መልኩ የኢትዮጵያን ሕዝብ አብሮ እንዳይኖር ሊያደርግና አገር እንድትገነጣጠል ሊያደርስ አይገባም። ምክንያቱም ከሁሉም በፊት ሕዝባችን እንደዚህ ዓይነት ውሳኔን በገዛ ፈቃዱና በሙሉ ነፃነት ሊያስተናግድ የሚችልበት የሥልጣኑ ባለቤትና የዕድሉ ወሳኝ መሆን የሚችልበት ሥርዓትን የመጎናጸፍ ዕድል ገና አላገኘም።

አሁን በ"መብት" ስም ይገነጣጠልና ሌላ ጊዜ ዘንቦ ተባርቆ ደስ ካለው ተመልሶ አንድ ይሆናል የሚለው ቀዶ ለመስፋት የሚሞክር የዞረበት አስተሳሰብ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም። አገር እንደዚህ አይገነባም። ተባይ ያፈራ ቤት ሁሉ ደግሞ አይቃጠልም ወይም ተባይን ለማጥፋት የሚወሰድ እርምጃ ባለቤቱን የሚጎዳ መሆን አይኖርበትም።
ስለ አገራዊ አንድነት ሲወሳ ጉዳዩ ስለ ሰው ልጅ እንጅ በፈለጉት ጊዜ ከተቀመጠበት ቦታ ስለሚገኝ የማይንቀሳቀስ ግዑዝ ተፈጥሮ አይደለም። ስለዚህ የኢትዮጵያ አገራዊ አንድነት መከበር አለበት ስንል ዜጎቿን ባስቀደመ መልኩ እንደሆነ ይገነዘቧል። በኛ እምነት ያ ሕዝብን ማስቀደም ደግሞ የበለጠና የተሻለ የሚረጋገጠው የአገር አንድነት ሲከበር ብቻ ነው። ለኛ ዋናው ጥያቄ የዚች ቅዱስ አገር ዜጎች እንዴትና በምን ፍጥነት እኩልነታቸው የሚከበርበትና የሥልጣን ባለቤት የሚሆኑበት ሥርዓት እውን ይሁን የሚለው ነው። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ የአገሩን አንድነት የሚያየው በከፍተኛ ቀናኢነትና ለዜጎች መብትና ክብር መጠበቅ የሚያደርገውን ትግልም የተያያዘው በትጋትና በፍጹም ቁርጠኝነት ነው።

ኢትዮጵያ ከማንም የተናጠል ድርጅት በላይ ናት። ማንም ኢትዮጵያዊ ደግሞ አሁን አባል የሆነበት ድርጅት አባል ሆኖ አልተወለደም። በማንኛውም ድርጅት የተሠራ በጎም ሆነ መጥፎ ነገር ሁሉ የጋራ ታሪካችን ነው። ከተሠሩ ስህተቶች ተምረን፣ መልካሙን ይዘን ለመጓዝ ዝግጅቱና ቁርጠኝነቱ እስከሌለ ድረስ ምንም ዓይነት ብሩኅ ተስፋ ሊኖር አይችልም። ከሁሉም በላይ አሁን አገራችንን ወጥሮ የያዛት ሁል-አቀፍ የችግር ክምር ከማንም የተናጠል ድርጅት አቅም በላይ እንደሆነ፣ የአገራችንንና የሁላችንም የወደፊት የወል ፍላጎት የጋራ ዕድል ቀደም ሲል ካሉን የርስ በርስ አለመግባባትም ይሁን ቅጥ ያጣ ጥላቻ እጅጉን የላቁና ሚዛን ውስጥ የማይገቡ መሆናቸውን አጥብቆ መረዳት ያስፈልጋል።

በአገራችን ዘለቄታዊነት ያለው ሰላም እንዲኖር የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክና የሙያ ማኅበራት፣ የኅብረተሰቡን ልዩ ልዩ ጥቅሞችና እምነቶች ለማስጠበቅ የቆሙ ስብስቦች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ ምሁራን፣ ወዘተ... የሚወከሉበትና የሚሳተፉበት አገር-አቀፍ የእርቅና የሰላም ጉባዔ ተካሂዶ አዲስ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ማድረግ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን፣ አገራችንን ከመከፋፈል፣ ሕዝባችንን ከቀጣይ ሰቆቃና ትርምስ እናድን ብለን ከልብ ካመንን፣ ግዴታ የማይሆንበት ምክንያት አይታንም።

ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን እንዲሆን በእርቅና ሰላም ላይ የተመሠረተ የሰከነ ሽግግር የሚደረግበት ሂደት እንዲጀመር ሁኔታዎች እንዲመቻቹና ለሁሉም መድረኩ ክፍት እንዲሆን ድርጅታችን የበኩሉን ድርሻና የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል፡፡ በዚኽ ረገድ ቀደም ሲል እንደጠቀስነው ሁሉ ምን ዓይነት ሂደትን ብንከተል በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ማድረግ እንደሚቻል ያለንን አሳብ በተለይ እናቀርባለን፡፡

**አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵያውያን በቅድሚያ በራሳቸው ላይ የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ አምጥተው፣ አገራቸው ያለችበትን ይኽ ነው የማይባል አደጋ ተገንዝበውና ውድ አገራችንም ከዜጎቿ ሌላ መድኅን እንደሌላት አበክረው አጢነው ለዚኽ አገር-አድን የድረሱልኝ ጥሪ ሊተባበሩ ይገባል፡፡**

አንድን ነገር መጀመር ቀላል ሊሆን ይችላል፡፡ የተጀመረውን የመጨረሻው ግብ ላይ ማድረስ ግን ቻይነትን፣ ቆራጥነትን፣ አስተዋይነትንና እራስን ከራስ በላይ ላለ ዓላማ ተገዥ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ በተለይም የፖለቲካ ድርጅትና ስብስብ ከአገራዊና ከሕዝባዊ ዓላማ የላቀ ወይም ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ሊኖር ይገባል ወይም ይኖራል ብለን አናስብም፡፡

ታጋሹና አስተዋዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለመደው ቆራጥነቱ የተደቀኑበትን ፈተናዎች ሁሉ ተቋቁሞ የግንቦት ድሎቹን ዳግም በእጁ አስገብቶ የዕድሉ ባለቤት እንደሚሆንና አንድነቱን ጠብቆ እንደሚኖር የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ የአንድነት ንቅናቄ (ኢዴኅአን) የጠና እምነት ነው፡፡

አዲስ የአስተሳሰብ ለውጥ ለአዲስ ሥርዓት ግንባታ!
አንድነት ኃይል ነው!!
አንድነታችን የጋራ ኅልውናችን መሠረት ነው!!!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!!

ኢዴኅአን (ኢዴኅአን)
ሰኔ፣ ፱ ሽህ ዓ/ም